# የህብረተሰብ ትምህርት የ8ኛ ክፍል

## የተማሪዎች መፅሐፍ


**አዘጋጆች :**

ጀማል ሙስጠፋ (M.A.)

ነጋሽ ሄቦ (M.A.)

ነጌሶ እስሞ (M.A.)

**አርታኢዎች:**

በላቸዉ አበራ (M.A)

ግርማ ፀጋየ (M.A.)

**ገምጋሚዎች:**

በቀለ ቀነአ (M.A.)

አበራ ከበበዉ (B.A.)

**ተርጓሚዎች:**

በቀለ ቀነአ (M.A.)

ቤኪ ቶለሣ (M.A.)

አበራ ከበበዉ (B.A.)

ከተማ ፀጋ (M.A.)

ዘዉዴ ረጋሣ (M.A.)

**ግራፊክስ:**

ታደሰ ድነቁ (M.A.)

© የኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ፣ 2014/2021

ይህ መጽሐፍ በኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ እና በሮቤ መምህራን ትምህርት ኮሌጅ ትብብር በ2014/2021 ተዘጋጀ፡፡

የዚህ መጽሐፍ የባለቤትነት መብት በህግ የተጠበቀ ነው፡፡ ከኦሮሚያ ትምህርት ቢሮ ፈቃድ ውጪ በሙሉም ሆነ በከፊል ማሳተምም ሆነ አባዝተው ማሰራጨት በህግ ያስጠይቃል፡፡

## ማውጫ

ምዕራፍ 1: የመሬት አፈጣጠር ሁኔታ.........................................1

1.1 የመሬት አፈጣጠር እና ስርአተ ፀሀይ .........................................2

1.2 በመሬት ላይ እና በመሬት ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች .....................10

1.3. ቅርፈተ መሬት የተሠራባቸው ነገሮች .......................................17

1.4. የአለቶች ሥርጭት እና በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ .............................22

ምዕራፍ 2: የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ እና የአለም ህዝብ ውስጥ ያላቸው ጠቀሜታ ..........................................................22

2.1 የሰው ልጅ ዝግመታዊ ለውጥ ...................................................30

ምዕራፍ 3: ከምዕራፍ የሚጠበቅ የመማር ውጤት ..................71

3.1. የሰው ልጅ እና የተፈጥሮአዊ አከባቢ ግንኙት .............................72

3.2 የሰው ልጅ እና የተፈጥሮ ሀብት ግንኙነት ..................................73

3.3. የተፈጥሮ ሀብት አይነቶች .......................................................75

ምዕራፍ 4 ቀደምት የአለም ስልጣኔ ከጥንት እሰከ መካከለኛው ክፍል ዘመን ...........................................................................81

4.1.ጥንታዊ የአለም ስልጣኔ .........................................................82

4.2.የመካከለኛ ክፍለ ዘመን የአለም ታሪክ .......................................98

ጥንታዊ የአፍሪካ ታሪክ ...........................................................108

ምዕራፍ 5 ..........................................................................108

5.1 ጥንታዊት የግብፅ ስልጣኔ ......................................................109

5.2 ጥንታዊት የኑቢያ ስልጣኔ ......................................................115

5.3 የጥንታዊት ሜሮኤ ስልጣኔ ....................................................117

ምዕራፍ 6 ጥንታዊና የመካከለኛ ዘመን የኢትዮጵያ መንግሥታትና ህዝቦች ታሪክ ........................................................124

6.1. ጥንታዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ...............................................125

6.2 የኢትዮጲያ ሙስሊም ሱልጣኔቶች ..........................................133

6.3 የህዝቦች እንቅስቃሴ ፣ ግንኙነት እና ትስስር ..............................135

ምዕራፍ 7 ......................................................................................148

ትኩረት የምሹ ወቅታዊ ዓለም ጉዳዮች ..........................................148

7.1. የምንኖርበት አከባብ ...............................................................149

7.2. የህዝብ ቁጥር መጨመር .......................................................157

7.3. ሽብርተኝነት ..........................................................................157

7.4. ህገ-ወጥ የሰዎች ዝዉዉር ....................................................159

የቃላት ፍችዎች ..........................................................................160

# ምዕራፍ 1

# የመሬት አፈጣጠር ባህሪያት

## ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች

ተማሪዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት አካሄድና መጨረሻ በኃላ:

- ✓ የተለያዩ ተፈጥሮአዊ የመሬት አቀማመጥ ሁኔታዎችን ትለያለህ/ሽ
- ✓ በመሬት ውስጣዊ እና ውጫዊ ሀይሎች ምክንያት የተፈጠሩ የተለያዩ የመሬት አቀማመጥን ትዘረዝራለህ/ሽ
- ✓ የመሬት ውስጣዊ እና ውጫዊ ሀይሎች በሰዉ ልጅ ላይ ምን አይነት ተፅዕኖ እንደምያደርሱ ትለያለህ/ሽ
- ✓ በአየር ንብረት እና በአየር ሁኔታ መካከል ያለውን ልዩነት ትለያለህ/ሽ
- ✓ የአየር ንብረት ይዘቶችና የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ትዘረዚራለህ/ሽ
- ✓ በደጋ፣ በወይን ደጋና በቆላማ  አካባቢዎች የሚፈጠሩ የዝናብ እና የሙቀት ልዩነት መፈጠር ምክንያቶችን በማነጻፀር ትገልጻለህ/ሽ

### መግብያ

በ7ኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ የመሬት አፈጣጠር ባህርያት እና ስርአተ ፀሀይን፣ የላይኛው የመሬት ይዘቶች እና በመሬት ውስጥ የምገኙ መዋቅሮች፣ መሬት እና ላይኛው የመሬት ክፍል መረጃ ምንጭ፣ ውስጣዊ የመሬት ክፍል እና ዕምብርተ መሬት፣ አለቶች እና  ምጣኔ ሀብት ውስጥ ያላቸውን ጠቀሜታ በስፋት ተምራችኋል፡፡ በዚህ ክፍል ውስጥ ደግሞ የመሬት አፈጣጠር ባህርያት፣ የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሀይሎች የመሬት አቀማመጥን የሚቀይሩ፣ የመሬት መዋቅር እና በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኙ ይዘቶች እንደዝሁም የአየር ሁኔታ እና አየር ንብረትን የሚቆጣጠሩ ነገሮችን ትማራለህ/ሽ፡፡

## ብያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃቶች፤

- ✓ የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ውስጣዊና ውጫዊ ሀይሎችን ትለያለህ/ሽ፡፡
- ✓ በመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሀይሎች ምክንያት የተፈጠሩትን የመሬት አቀማመጦችን ትለያለህ/ሽ፡፡
- ✓ የመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሀይሎች በሰው ልጅ ላይ የሚያደርሱት ተፅዕኖዎች ትገለጻለህ/ሽ፡፡
- ✓ የከባቢ አየር ንብርብሮች አይነቶችን ትዘረዚራለህ/ሽ፡፡
- ✓ የአየር ሁኔታና አየር ንብረት ልዩነትን ትለያለህ/ሽ፡፡
- ✓ በአየር ንብረት ይዘቶችን ትዘረዚራለህ/ሽ፡፡
- ✓ አየር ንብረትን የሚቆጣጠሩትን ትዘረዚራለህ/ሽ፡፡

በደጋ፣ በወይን ደጋና በቆላማ አካባቢዎች የሚፈጠሩ የዝናብ እና የሙቀት ልዩነት መፈጠር ምክንያቶችን በማነጻፀር ትገልጻለህ/ሽ፡፡

## 1.1. የመሬት አቀማመጥን የሚቀይሩ ሀይሎች

የግምገማ ጥያቄዎች 1.1

1. የመሬት አቀማመጥን የሚቀይሩ ሀይሎች ምንድናቸው?
2. በሚትኖርበት አካባቢ የሚታወቁ የመሬት አቀማመጥ አይነቶችን ዘርዝር/ሪ?
3. የመሬት ውጫዊና ውስጣዊ ሀይሎች ልዩነት ግለፅ/ጭ?

የመሬት አቀማመጥ ማለት በውጫዊ የመሬት ገፅታ ላይ የተለያዩ የመሬት አቀማመጥ ተሰራጭቶ የሚገኝ ማለት ነዉ፡፡ በሁሉም ቦታ የመሬት አቀማመጥ ተመሳሳይነት የለውም፡፡ የመሬት አቀማመጥ ማለት በመሬት ገፅታ ላይ የሚታዩ የመሬት አቀማመጥ ወይም ቅርፅ ማለት ነው፡፡ እነርሱም፤ተራራማ፣ ፐላቶዎች፣ ሸለቆዎችና ዝቅተኛ ቦታዎች ናቸው፡፡ እነዚህም በመሬት ውስጣዊና ውጫዊ ሀይሎች ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው፡፡ በመሬት ውጫዊ ክፍል ላይ ለውጥ የሚያመጡ ሀይሎች እንደ ፤ንፋስ፣ የውሃ ጎርፍ፣ በበረዶ መንሸራተት ፣ የመሬት መተጣጠፍ፣ የመሬት መሰነጣጠቅና የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሂደት ናቸው፡፡




ሥዕል1.1የተለያዩ የመሬት አቀማመጦች

የመሬት አቀማመጥ ከቦታ ቦታ ልዩነት አለው፡፡ የዚህ የመሬት አቀማመጥ ልዩነት የተፈጠሩት በመሬት ውጫዊና ውስጣዊ ሀይሎች ምክንያት የተነሳ ነው፡ ፡ የመሬት አቀማመጥ ለውጥ የማያቋርጥ ሂደት ነው፡፡

## 1.1.1. የመሬት አቀማመጥን የሚቀይሩ ውስጣዊ ሀይሎች

**የግምገማ ጥያቄ**

1. የመሬት አቀማመጥን የሚለዋጡ ውስጣዊ ሀይሎች ምን ምን ናቸው?
2. በመሬት ውስጣዊ ሀይሎች ምክንያት የተፈጠሩትን የመሬት አቀማመጦችን ዘርዝር/ሪ፡፡

የመሬት ውስጣዊ ሀይሎች በመሬት ውስጥ የሚፈጠሩና በውጫዊ መሬት አካል ላይ ለውጥ የሚያመጡ ናቸዉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ፣ የመሬት መተጣጠፍ፣ የመሬት መንቀጥቀጥና የመሬት መሰነጣጠቅ ናቸው፡፡ በመሬት ውስጣዊ ሀይሎች ምክንያት የተለያዩ የመሬት አቀማመጦች ተፈጥረዋል፡፡ ይህ አካሄድ የማያቋርጥና ተከታታይ ነዉ፡፡ በዚህ ሁኔታ የተፈጠሩ የመሬት አቀማመጥ በአይን ከማይታዩ እስከ ትልልቅ የመሬት አካላት እንደ ተራራዎች፣ ፕላቶዎች፣ ሸለቆዎች፣ ሜዳዎችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡ ለዚህ ጥሩ ምሳሌ ከሚሆኑት ውስጥ በዓለም ላይ ከፍተኛ ጥልቀት ያለው ዴድሲ

(በእስራኤልና ፍልስጤም ሀገሮች መካከል የሚገኝ) ሲሆን በዓለም ላይ ከፍተኛ ቦታ ደግሞ በሂማሊያ ከሚገኙ ተራሮች ውስጥ የእቬረስት ተራራ ነው።

በሌላ በኩል የሀገራችን የመሬት አቀማመጥ ብንወስድ ከፍተኛ ልዩነት አላቸው፡ ፡ ለምሳሌ፤ በጣም ከፍተኛ ቦታ በሰሜን ከምገኙ የሀገርቱ ተራሮች ውስጥ የራስ ዳሸን ተራራ 4620 ሜትር ከባህር ወለል በላይ ነው። ዝቅተኛ ቦታ የሚገኘው በአፋር ክልላዊ መንግስት ዳሎል ተብሎ የሚጠራ ቦታ ሲሆን ከባህር ወለል በታች 116 ሜትር ነው።

በዓለም ከፍተኛ ቦታ ያላቸውን ከዚህ በታች ያለውን ሰንጠረዥ ውስጥ ተመልከቲ/ቺ

ሰንጠረዥ1.1. የዓለም ከፍተኛ ቦታዎች

| ተ. ቁ | የተራራው ስም | ከፍታ(ሜ) | የሚገኝበት አህጉር |
|---|---|---|---|
| 1 | ኤቨረስት | 8850 | በኤሽያ |
| 2 | ኪሊማንጀሮ | 5895 | በአፍርካ |
| 3 | ቱሉ ድምቱ | 4377 | በአፍርካ |
| 4 | ራስ ዳሸን | 4620 | በአፍርካ |

## የመሬት መተጣጠፍ

የመሬት መተጣጠፍ የሚፈጠሩበት አካባቢ ዝቅጠተ አለት የሚገኝበት አካባቢ ነዉ። ዝቅጠተ አለት እንደ ሌለኛው አለት ጠንካራ ስላል ሆነ ለመተጣጠፍ ይጋለጣል። የመሬት መተጣጠፍ ምክንያት ከመሬት ውስጥ ከሚነሱ ሀይሎች አማካይነት ነው። ይሁን እንጂ በዚህ አካባቢ እንደ እሳተ ገሞራ ከመሬት ውስጥ በመውጣት የሚከማች የለም ወይም የመሬት አካል ተሰባብሮና ተሰነጣጥቆ ወደ ውስጥ ሰምጦ የሚቀር የለም። የመሬት መተጣጠፍ የሚፈጠርበት አካባቢ መሬት ወደ ላይ ተገፍቶ ተራሮች እና ኮረብታዎች ይፈጠራሉ።


ከፍተኛ ሀይል ያለበት አካባቢ ትልልቅ ተራሮች ይፈጠራሉ። በሰሜን አፍርካ የሚገኙ ትላልቅ ተራሮች እንደ አትላስ፤ በአዉሮፓ አልፐስና በኤስያ ሂማሊያ በመሬት መተጣጠፊ ምክንያት የተፈጠሩ ናቸው።

ከመሬት ውስጥ የሚነሱ ሀይሎች በመሬት አካል ላይ፣ በሰው ልጅና ሌሎች

ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ ጉዳት ልያደርሱ ይችላሉ፡ ፡ ለምሳሌ፤ በሀይት ውስጥ በ2002 የተከሰተ የእሳተ ገሞራ ፊንዳታ መውሰድ ይቻላል፡፡

## በመሬት መሰነጣጠቅ ምክንያት የተፈጠሩ የመሬት  አቀማመጥ

**መሰነጣጠቅ** ማለት የመሬት አካል በሁለት ቦታ መከፈል ማለት ነው፡፡ መሬት ተሰንጥቆ ወደ ጎን ተቆርጦ ወይም ወደ ታች ዝቅ የሚል የመሬት አካል ነው፡፡ የመሬት አካል የሚላቀቁት ተቃራኒ ሀይሎች እርስ በርሳቸው ስራራቁ በመሬት አካል ላይ በሚፈጥሩት ጫና ነው፡፡ የመሬት አካል ከቦታ መንቀሳቀስ ወይም አለት በተሰነጣጠቀበት አካባቢ የሚከሰት ነው፡፡  በመሬት መሰነጣጠቅ ምክንያት የተለያዩ የመሬት አቀማመጦች ይፈጠራሉ፡፡ ለምሳሌ መሬት በሚሰነጣጠቅበት ጊዜ ስምጥ ሸለቆዎች ወይንም ትይዩ ተራሮች ሊፈጠሩ ይችላሉ፡፡




ሥዕል1.2. ትልቁ የምስራቅ አፍሪካ ስምጥ ሸለቆ

## እሳተ ገሞራ

### እሳተ ገሞራ ማለት ምን ማለት ነው?

እሳተ ገሞራ በመሬት ውስጥ ባለው ከፍተኛ ሙቀት ምክንያት የአለቶች ቅልጠት (ማግማ) እና ጋስ የሚፈጠር ፍንዳታ  ነው፡፡

## በእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ምክንያት የተፈጠሩ የመሬት አቀማመጥ

**የግምገማ ጥያቄዎች**


1. ማግማ ምንድነው?
2. የማግማና የእሳተ ገሞራ ልዩነት ምንድነዉ?

ማግማ በከፍተኛ ግፊት ምክንያት በሚፈጠረው ከፍተኛ ሙቀት በመሬት ውስጥ ያሉት አለቶች ቀልጠው ወደ ፈሳሽነት ሲቀየሩ ነው፡፡ ማግማ በሚቀዘቅዝበት ቦታ ላይ ተመስርቶ እሳተ ገሞራ በሁለት ይካፈላል፡፡ እነርሱም፤

1. በመሬት ውስጥ የሚቀዘቅዝ እሳተ ገሞራ እና
2. በመሬት ገፅታ ላይ  የሚቀዘቅዝ እሳተ ገሞራ

ማግማ በጣም ወፍራም ፈሳሽ በመሆን ከውስጥ ወደ ውጪ የመሬት ገፅታን በሀይለኛ ጉልበት በመሰንጠቅ ወጥቶ የሚፈስ ማግማ  በአንድ ወይም በብዙ ቀዳዳዎች ሊወጣ ይችላል፡፡ በአንድ ቀዳዳ ብቻ የሚወጣ ማግማ ቬንት ይባላል፡ ፡ በብዙ ቀዳዳዎች የሚወጣ ማግማ  ደግሞ ፊሸር በመባል ይታወቃል፡፡ በአንድ ቀዳዳ በሀይለኛ ጉልበት የሚወጣ እሳተ ገሞራ የካልዴራ ይፈጥራል፡፡ የሙቀት መጠን ከፍተኛ ከሆነ የሚፈጠረው ማግማ ፈሳሽ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጅ በመሬት ውስጣዊ ግፍት ምክንያት የሚፈጠረዉ ሙቀት ዝቅተኛ ከሆነ ደግሞ የሚፈጠረው ማግማ ወፍራም ነው፡፡ የጋስ ጉልበት በፈሳሽ ማግማ ውስጥ ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሀይለኛ እንድሆን ያደርጋል፡፡  በመሬት ገፅታ ላይ ወጥቶ የሚፈስ ማግማ ላቫ ይባላል፡፡

የመሬት ውስጣዊ ሙቀት አነስተኛ ከሆነ የሚፈጠረው ማግማ ወፍራም ሆኖ አነስተኛ ጋስ  አለው፡፡ ይህ ደግሞ ማግማ በመሬት ገፅታ ላይ ሳይወጣ በድንገይ ንቃቃት ውስጥ ገብቶ የሚቀር ማለት ነው፡፡ ይህንን በመሬት ውስጥ ቀርቶ የቀዘቀዘ ማግማ እንላለን፡፡



ሀ. ፊሸር



ለ. ቬንት

ሥዕል.1.3.የተለያዩ እሳተ ገሞራ ዓይነቶች

### የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ደረጃ

ጂኦሎጅስቶች የእሳተ ገሞራ አፈጣጠር ደረጃ በሦስት ከፍለዋላ፡፡ እነርሱም፤

**ተንቀሳቃሽ እሳተ ገሞራ** - በአጭር ጊዜ ውስጥ ተደጋግሞ የሚፈነዳ የእሳተ ገሞራ አይነት ነው፡፡ ብዙ ጊዜ የሚፈጠረው በትላልቅ ውቅያኖሶች ውስጥ ነው፡፡

የተዳፈነ እሳተ ገሞራ - የተወሰኔ ጊዜ ቆይቶ የሚፈነዳ የእሳተ ገሞራ አይነት ነው፡፡

ያለቀለት እሳተ ገሞራ - ከእዝህ በፍት ፈንድቶ ያለቀለት የእሳተ ገሞራ አይነት ነው፡፡

## የመሬት መንቀጥቀጥ

የመሬት መንቀጥቀጥ ምንድ ነው?

የመሬት መንቀጥቀጥ በተለያዩ ምክንያቶች በመሬት ውስጣዊ ሀይሎች እንደ እሳተ ገሞራ እና በመሬት ውስጥ በድንጋይ መላቀቅ የመሬት አካል ስንቀጠቀጥ ነው፡፡

ቅርፍተ መሬት የተፈጠረው ከተለያየ አለቶች ነው፡፡ እነዚህ አለቶች እንደ ፒላስትክ የመሳሳብ ባህር አላቸው፡፡ ነገር ግን የመሳሳብ ሀይል ከፍተኛ ከሆነ አለቶቹ ይላቀቃሉ፡፡ አለቶቹ በሚላቀቁበት ወይም በሚሰነጠቁበት ወቅት የመሬት መንቀጥቀጥ ይፈጠራል፡፡ በዚህ አካሄድ አለቶቹ በሚላቀቁበት ጊዜ ሀይለኛ ጉልበት ይፈጠራል፡፡ የሚፈጠረው ሀይል ደግሞ አለቶችን ከቦታ ያንቀሳቅሳል፡፡ የአለቶቹ መንቀሳቀስ ደግሞ ለመሬት መንቀጥቀጥ ምክንያት ይሆናል፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥ ሀይል የሚነሳበት ቦታ ፎከስ ይባላል፡፡ ቀጥታ በፎከስ ትይዩ በላይኛው የመሬት አካል ላይ የመሬት መንቀጥቀጥ መነሻ ቦታ ኢፒሰንተር

ይባላል፡፡ የመሬት መንቀጥቀጥ በቀጥታ የመሬት ገፅታን አይቀይርም፡፡ ነገረ ግን የክስተቶች ህዴትና የመሬት ገፅታን እንቅስቃሴ ለውጥ ሊፈጠር ይችላል፡፡ የተለያዩ ጥናቶች እንደረጋገጡት 95% የሚሆነው የመሬትመንቀጥቀጥ በሚከተሉት ሦስቱ አካባቢዎች ይገኛል፡፡ እነርሱም፤ በፓስፍክ ዉቅያኖስ ደርቻ፣ ከቀይ ባህር ዳርቻ ተነስቶ እስከ ሄማሊያ ተራራ እና በትልቁ ስምጥ ሸለቆ ውስጥ ነው፡፡

## 1.1.2. የመሬት አቀማመጥን የሚለዊጡ ውጫዊ ሀይሎች

የግምገማ ጥያቄ

1. በመሬት አካል ላይ ለውጥ የሚያመጡ ውጫዊ ሀይሎች ምንድናቸው?
2. በመሬት ውጫዊ ሀይሎች ምክንያት በመሬት ገፅታ ላይ የሚታዩ ለውጦችን ዘርዚር/ሪ

**ለውጥ** - ለውጥ ሲባል በፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ለወጦች አንድ ነገር በመጠን፣ በቀለም፣ በይዘትና በመሳሰሉት ከነበረበት ወደ ለላ ሲቀየር ነው፡፡ ለውጥ በሁለት መንገድ ሊፈጠር ይችላል፡፡ እነርሱም፤ፊዚካላዊና ኬሚካላዊ ለውጦች ናቸው፡፡

### ሀ. ፊዚካላዊ ለውጥ

ፊዚካላዊ ለውጥ ነገሮች በመጠን ማነስ ወይም በቅርፅ መቀየርን የሚገለፅ ነው፡፡ የፊዚካል ለውጥ ከሚያመጡት ነገሮች ውስጥ የተወሰኑት፤ እፀዋቶች፣ እንስሳቶች፣ የውሃ ጎርፍ እና ንፋስ ናቸው፡፡ እንደሚታወቀው በቀን ሙቀትና በማታቅዝቃዜ አማካይነት በአለቶች ውስጥ ያሉ ሞሎኪሎች የመላቀቅና መኮማተር ባህርይ ያሳያሉ፡፡ ይህ ሁኔታ የአለቶች አካላት ላይ መለያየት እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡ የአለቶች መለያየት ህደት ቀስበቀስ የአለቶች መሰነጣጠቅ ምክንያት ይሆናል፡፡



ሥዕል 1.4. ፊዚካላዊ ለውጥ

## በውሃ የሚከናወን ፊዚካላዊ ለውጥ

ፊዚካላዊ በውሃ የለውጥ በተለያየ መንገድ ሊከናወን ይችላል፡፡ ከእነዚህ ውሰጥ የመጀመርያ አለት ወይም አፈር በውሃ በማርጠብ የአለት ሞሎኪሎች ወይም የተያያዜ አፈር እና ጠጣሮች የነበረዉ በማስለስለስ መላቀቅ ይጀሚራል፡፡ በ በኩል ደግሞ በተሰነጣጠቀ አለት ውስጥ ውሃ በመግባት እና በጣም በመቀዚቀዝ የተሰነጠቀው አለት ቀስ በቀስ በመራራቅ በተሰነጣጠቀበት ቦታ መካፈል ይቸላል፡፡ በዚህ አካሄድ ፊዚካላዊ በውሃ የሚከናወን ለውጥ ይሆናል፡፡



ሥዕል 1.5. በውሃ ምክንያት የአለቶች ፊዚካላዊ ለውጥ

## በዕፀዋቶች ምክንያት የሚፈጠር ፊዚካላዊ ለውጥ የሚከናወን

ሌላ ፊዚካላዊ ለውጥ የሚከናወነዉ በዕፀዋቶች ነዉ፡፡ በተለይ የዕፀዋቶች ሥር

በተሰነጣጠቀ ድንጋይ ውስጥ በመግባት ቀስ በቀስ እያደገ አለቶችን በመግፋት እንድሰነጠቅ እና በመጨረሻ እንድሰባበር ወይም እንድሰነጠቅ ያደርጋል፡፡



ሥዕል 1.6. በዕፀዋቶች የተፈጠሩ የአለቶች አካል መሰነጣጠቅ

## ለ. ኬሚካላዊ ለውጥ

ኬሚካላዊ ለውጥ በአለቶች ማዕድናቶች ላይ የሚፈጠረው ኬሚካላዊ ለውጥ ነው፡፡ ብዙ አይነቶች ኬሚካላዊ ለውጥ አሉ፡፡ ከእነዚህ ውሰጥ ታወቅዎቹ፤ ሀይዲሮላይስስ፣ ካሪቦነሽን እና ኦክስደሽን ናቸው፡፡

ሀይዲሮላይስስ: ማለት በውሃ ግፍት ምክንያት የማዕድናቶች መዋቅር ለውጥ ነው፡፡ አተሞች በማዕድን ውስጥ የለውጥ ሁኔታ የአለቶች ለውጥን ይፈጥራል፡፡



ሥዕል 1.7. በውሃ የሚፈጠር ሀይድሮላይስስ

ካርቦነሽን:የአለት ለውጥ አካሄድ የካሊሰዬም፣ ማጊንዠም፣ ሶድዬም ፖታስዬምና ውሃን በአዮኖች ማባላላት የሚፈጠሩ ናቸው። በዚህ አካሄድ ውስጥ የውህዶች ማባላላት ካርቦነት እና በይ-ካርቦነት ይፈጥራል። በመሬት ላይ የሚፈስ ውሃ ሁሉ የካርቦንዳይ-ኦክሳይዲ ማሟሟት ከአየር ስርጭት ውስጥ ወይም በአፈር ውስጥ የዕፅዋት ብስባሺ ላይ የተገኜ በውስጡ የዘዋል። በካርቦንዳይ-ኦክሳይዲ ምክንያት በነገሮች ላይ በዚህ ሁኔታ የሚፈፀም ለውጥ ካርቦነሽን ይባላል።

ኦኪስደሽን:- በውስጡ ብረት የያዙ ውህዶች ሂደት ውሰጥ የኦክስጂን መጨመር ነው። እንደዚህ አይነት አካሄድ በህብረተሰብ ዘንድ ዝገት ይባላል። ብረት ነክ ባህር ያላችው ዕቃዎች ከውሃ ወይም እርጥበት ያለበት ቦታ ከነኩ በብረት ነክ ውስጥ ያሉት አዮኖችና ኦክስጂን ከመፈጠሩ የተነሳ ዕቃው መዛግ ይችላል። ይህ አካሄድ ኦኪስደሽን ይባላል። በውስጡ ብረት ያላቸው የማዕድናት አለቶች በቀላሉ በኦኪስደሽን ይሰባበራሉ። የዚህ ከሚካላዊ ለውጥ በአካባቢና በመጠነ ሙቀት ሰዓትና ዝናብ በብዛት ያለበት ቦታ ይፈጠራል።

መሸርሸር፣ መጓጓዝ እና ማከማቸት

መሸርሸር: በመሬት ገፅታ ላይ ያሉ ነገሮች በንፋስና በውሃ ጎርፍ ከአንድ ቦታ ወደ ቦታ የመጓጓዝ ሂደት ነው። የመሸረሸር ከፍተኛ እጅ የሚከናወነው በመሬት ገፅታ ላይ የሚከሰት የመሬት ገፅታን የሚለውጡ እንደነ ጎርፍና በንፋስ ይከናወናል። በጎርፍ የሚከናወን መሸርሸር የሚጠናከር ዝናብ የሚበዛበት አካባቢ ስሆን በንፋስ የሚከናወን መሸርሸር ደግሞ በቆላማ ቦታ ነው። የአፈር መሸርሸር ከፍተኛ እጅ የሚከናወነው በውሃ ጎርፍ ነው። የውሃ ጎርፍ የመሬት አካልን በመቁረጥ/ በማፍረስ መጓጓዝና በመከማቸት በመሬት አቀማመጥ ላይ የተለያዩ ለውጦችን ያመጣል። የአፈር መሸርሸር እና የአለቶች ለውጥ በውሃ ጎርፍ ስከናወን፤ተራራማ የመሬት አቀማመጥ/ ከፍተኛ ቦታ ላይ ከፈተኛ ዝናብ በአጭር ጊዜ ውስጥ ብከናወንና የአፈር ባህር ለሸርሻሮ የሚጋለጥ ከሆነ ነው።

መጓጓዝ: በውሃ ጎርፍና በንፋስ መሸርሸር ሀይሎች ምክንያት ነገሮች ከአንድ ቦታ ተወስደው ወደ አካባቢ ማድረስ መጓጓዝ ይባላል።

መከማቸት: የነገሮች ሂደት እንደ አፈር፣ የተሰባበረ አለት፣ የዕፀዋቶች እና የአራዊቶች ቅርት አካል ከቦታ ተወስዶ በአንድ ቦታ መጠራቀም መከማቸት

ይባላሉ፡፡ ይህ የነገሮች መጠራቀም ደለል ወይም ክሚችት ይባላል፡፡ ይህ የሚከናወነው ለጥ ያለ መሬት በሀይቅ፣ በውቅያኖስ ወይም በባህር መጊብያ ሊሆን ይችላል፡፡


በመሬት አቀማመጥ ላይ ለውጥ የሚፈጠረው ከፍታ ያለበት ቦታ ሸርሻሮ የተካሄደበት አካባቢና የደለል ክሚችት የተካሄደበት ቦታ ነው፡፡



ሥዕል 1. 8. በውሃ የተፈጠሩ የአፈር መሸርሸር

**በንፋስ መሸርሸር:** ብዙ ጊዜ የሚፈጠረው በሞቃታማ ቆላ  አካባቢ ነው፡፡ ምክንያቱም በቆላማ አካባቢ በዕፀዋቶች የተሸፈኑ ጥቅት ከመሆኑ ንፋስ በቀላል ሁኔታ አፈር በመሸርሸር በ ቦታ ያጠራቀማል፡፡ ሌላ ምክንያት ደግሞ በሞቃታማ ቆላ አካባቢ አብዛኛው ጊዜ በንፋስ መሸርሸር የሚፈጠረው የመሸረሸሩ ነገሮች ያልተያያዙ አለ መሆኑና በቀላሉ መሸርሸር ስለሚችሉ ነው፡፡ የሚከተለውን ሥዕል በመመልከት በመሬት አካል ላይ የሚታዩ ለውጦች መረዳት ይቻላል፡ ፡ ትንሽ ክብደት ያላቸው ነገሮችና ደቃቅ አፈርን በንፈስ መሸከም ሂደት/ በራሱ በመቀላቀል መጥረግ ዲፌሌክሽኒ ይባላል፡፡ ሌላ ሁኔታ ንፋስ አለቶችን በማጋጨት በለውጥና በመሬት በመፋተጊ (firction) መሸርሸር መካሄድ ይችላል፡፡ በዝህ ሁኔታ የተለያዬ የመሬት አቀማመጥ በሞቃታማ ቆላ አካባቢ ይፈጠራል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ትንኒሽ ኮሮፒታዎች፣ ዲዩንስ እና የመሳሰሉት መውሰድ ይቻላል፡፡





ሥዕል 1.9. በንፋስ መሸርሸር ምክንያት የተፈጠሩ የመሬት አቀማመጥ

**በሚሸራተት በረዶ የተፈጠረ መሸርሸር:** በበረዶ መሸርሸር የሚፈጠረው በረዶ የተከመረበት አካባቢ የመጠነ ሙቀት መጠን ከጨመረ የበረዶ መቅለጥ፣ መሰነጣጠቅ እና መጠራቀም መከናወን ይችላል፡፡ ብዙ ጊዜ የበረዶ መሸርሸር የሚፈጠረዉ በረዶ በቢዘት ሚገኝበት አካባቢ ተራራማ መሬተና በዋልታዎቹ አካባቢ ነው፡፡



ሥዕል1.10. በዋልታ አካበቢ በሚሸራተት በረዶ የሚከናወን መጠራቀምና መሸርሸር

መጓጓዝ: ማለት የተለያዩ ቅሪት አካሎችና የዕፀወቶችና የአራዊቶች ቅሪት አካልን በመሸርሸር ወደ ሌላ ቦታ ማድረስ ማለት ነው፡፡ የቅሪት አካሎች መጓጓዝ የሚከናወነው በውሃ ጎርፍ፣ በንፋስ እና በሚሸራተት በረዶ ነው፡፡

**የውሃ ስብስብ:** እንደምታወቀው በመሬት አቀማመጥ ምክንያት ወንዞች ከላይኛው ተፋሰስ በፍጥነት ስለምፈሱ በብዛት ይሸረሽራሉ እንጂ አያከማቹም፡፡ በታችኛው ተፈሰስ ደግሞ ለጥ ያሌ መሬት ስለሆነ ነገሮችን የመሸከም ሀቅም ስለሌለው ደረጃ

በደረጃ መከማቸት ይጀምራሉ። በውቅያኖስና ባህር ዳርቻ የአፈር ክምችት ደለል ይባላል። የወንዞች ስሪዓተ ተፋሰስ በሦስት ይካፈላል። እነርሱም፤ የላይኛው ተፋሰስ፣የመካከለኛ ተፋሰስ እና የታችኛው ተፋሰስ ናቸው።

**የላይኛው ተፋሰስ:** እዚህ አካባቢ ወንዞች ቁሊቁሌታማ በሆኔ መሬት ላይ ይፈሳሉ። የዚህ የመሬት አቀማመጥ ለሚፈሱ ወንዞች ከፍተኛ ፍጥነትና ጉልበት እንድኖሬው ያደርጋል። በላይኛው ተፋሰስ ወንዞች ከፍተኛ ጉልበት ስለአላቸው መሸርሸር ብቻ ሳይሆን መሬትን ወደ ታች በመቆፈር “V” ቅሪፅ የሚመስለው ሸለቆ ይፈጥራሉ።

**መካከለኛ ተፋሰስ:** በዚህ ተፋሰስ ውስጥ በወንዞች ውስጥ የሚገኘው የውሃ መጠን ከፍተኛ ነው። ነገር ግን እንደ ላይኛው ተፋሰስ ፍጥነት ስለለሌው የአፈር መሸርሸር ዝቅተኛ ነው። ይሁን እንጂ የሚፈስበት ሸለቆን በግራና ቀኝ በመቆፈር ውሃ የሚፈስበት መሬት እንድሰፋ ያደርጋል። የመካከለኛው ተፋሰስ የወንዝ ሸለቆ ቅሪፅ “U” ፊደል የሚመስል ይፈጠራል። በዚህ ተፋሰስ ውስጥ የወንዝ ውሃ ከላይኛው ተፋሰስ ክብደት ያላቸው ነገሮችን በማኒከባለልና በወንዞች ዳርቻ እየከመሬ ይሄዳል።

የታችኛው ተፋሰስ: በዚህ ተፋሰስ ውስጥ ውሃ በሚተኛ መሬት ላይ ስለምፈስ በጣም ዝቅተኛ ፍጥነት አለው። ስለዚህ ከላይኛውና መካከለኛ ተፋሰስ ላይ ተሸኪሞ ያመጣውን ነገሮች በብዛት እዚህ ቦታ ያከማቻል። በክርምት ወር ወንዞች ስለሚሞሉ በወንዞች አፋፍ ላይ በመፍሰስ በአካባቢ የሚገኘው ለጥ ያሌ መሬት ሁሉንም ይሸፍናል። በክርምት ወር ውሃ በወንዝ ዳርቻ ስለሚተኛና በበጋ ወር ስለሚደርቅ የባህር ሜዳ በመባል ይታወቃል። በዝህ ሁኔታ አፈር የተከማቸበት አካባቢ የተለያዩ የአህል፣ የአታክልት እና ፍራፍሬ አይነቶች ለማምረት ያገለጊላል።

# 1.2. የመሬት ከባቢ አየር ይዜቶችና ንብርብሮች

## 1.2.1. የመሬት ከባቢ አየር ይዜቶች

**የግምገማ ጥያቄ**

1. የመሬት ከባቢ አየር ይዜቶች ምን ምን ናቸው?
2. የመሬት ከባቢ አየር ክፍፊል ያላቸው ጠቀሜታ ግለፅ/ጭ፡፡
3. የከባቢ አየር ንብርብሮችና ባህርያቸውን ለክፍል ተማርዎች ግለፅ/ጭ፡፡

የመሬት ከባቢ አየር የተለያዩ የጋሶች ውህድ፣አቧራ እና ውሃን በቲነት መልክ በውስጡ ይዘዋል፡፡ ከመሬት ከባቢ አየር አይነት ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው ናይትሮጅን ስሆን በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ ኦክሲጅን ነው፡፡

ሠንጠረዥ 1.1. የመሬት ከባቢ አየር ታዋቅ ጋሶች

| ቋሚ ገሶች | | | ተለዋዋጭ ጋሶች | |
|---|---|---|---|---|
| የጋስ ሥም | ምልክት (symbol) | ደረቁ የጋስ ይዘት(%) | ጋስና ፓርትክሎች | ይዘት (%) |
| ናይትሮጅን | $N_2$ | 78.08 | የውሃ ትነት | 0 እስከ 4 |
| ኦክሲጅን | $Co_2$ | 20.95 | ካርቦንዳይኦክሳይድ | 0.038 |
| አርጎን | Ar | 0.93 | ሚተን | 0.00017 |

## 1.2.2. የመሬት ከባቢ አየር ንብርብሮች

**የግምገማ ጥያቄ**

1. የመሬት ከባቢ አየር ጠቅሞች ምንድናቸው?
2. የመሬት ከባቢ አየር ንብርበሮችን ዘርዚር/ሪ፡፡
3. መሰረታዊ የመሬት ከባቢ አየር ክፍፊል በምን ላይ የተመሰረተ ነው?

የመሬት ከባቢ አየር በመጠነ ሙቀት ላይ ተመስርተው በአራት ዋና ዋና ንብርብሮች ይካፈላል፡፡ እነርሱም፤

- ✓ ትሮፖስፌር
- ✓ እስትራቶስፌር
- ✓ ሜሶስፌር
- ✓ ተርሞስፌር.

1. **ትሮፖስፌር:** ከመሬት ቀጥሎ የሚገኝ ንብርብር ነው፡፡ የመገኛ ሁኔታውም በምድር ወገብ አካባቢ እስከ 17 ኪ.ሜ. ከፍ ብሎ የሚገኝ ስሆን በዋልታ አካባቢ ደግሞ እስከ 7 ኪ. ሜ. ወደ ላይ ከፍ ብሎ ይገኛል፡፡ በዚህ ንብርብር ውስጥ ከፍታ በጨመሬ ቁጥር መጠነ ሙቀቱ እዬቀነሰ ይሄዳል፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የዚህ ንብርብር ሙቀት ምንጭ መሬት ስለሆኔ ነው፡፡ ከፍተኛ ግፊት ያሌው የመሬት ከባቢ አየር በዚህ ንብርብር ውስጥ ይገኛል፡፡ የዚህ ምክንያት ይህ ንብርብር ከሁሉም በላይ ጥቅጥቅ ያለ ነው፡፡ የተለያዩ ጋሶችና የውሃ ትነት በውሰጡ በመኖሩ ነው፡፡ የትሮፖስፌር የላይኛው ድንበር ትሮፖፓወዝ በመባል ይታወቃል፡፡

2. **እስትራቶስፌር:** በትሮፖስፌር ንብርብር ቀጥሎ የሚገኝ ነው፡፡ በዚህ ንብርብር ውስጥ ከፍታ በሚጨሚርበት ጊዜ መጠነ ሙቀቱም ቀስ በቀስ እየጨመሬ ይሄዳል፡፡ ይህ ሊሆን የቻለው የኦዞን ጥርቅም ($_{O3}$) በዚህ ንብርበር ውስጥ ስለምገኝ ነው፡፡ የኦዞን መኖር ደግሞ አልትራቫዮሌት ጨረር የሚባል በውሰጡ ተውጠው እንድቀር ያደርጋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ያሌው ሙቀት በዚህ ውስጥ ተውጠው እንደቀር ያግዛል፡፡ የእስትራቶስፌርና ሜሶስፌር ድንበር እስትራቶፖፖስ ይባላል፡፡ ይህም እስከ 20 ኪ. ሜ. ከፍ ብሎ ይገኛል፡፡

3. **ሜሶስፌር:** ይህ ንብርበር የእስትራቶስፌር የላይኛው ድንበርና በ90 ኪ.ሜ. መካከል ይገኛል፡፡ በዚህ ንብርብር ውስጥ ከፍታ በሚጨምርበት ጊዜ መጠነ ሙቀቱ በፍጥነት እየቀነሴ ይሄዳል፡፡ መጠነ ሙቀቱ እስከ

   $-85^0$ C ይወርዳል፡፡ ከፍታ እየጨመሬ በሚሄድበት ጊዜ የመጠነ ሙቀት መቀነሱ ምክንያት ከለላው ንብርብሮች በላይ በዚህ ንብርብር ውስጥ የጋሶች ጥርቅም ትንሽ ስለ ሆኔ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ሙቀት እንዳይጠራቀም ያደርጋል፡፡ የላይኛው ጫፍ ወይም ድንበር ሜሶፓወስ ይባላል፡፡

4. ተርሞስፌር: የመሬት ከባቢ አየር ንብርብር የላይኛው የሜሶስፌር ድንበር በላይ የሚገኝ ነው፡፡ በዚህ ንብርብር ውስጥ ከፍታ በጨመሬ ቁጥር መጠነ ሙቀቱም በፍጥነት እየጨመሬ እስከ 1500⁰C ይደርሳል፡፡ ከዚህ የተነሳ ይህ ንብርብር የመሬት ከባቢ አየር ንብርብር በከፍተኛ ሙቀት ይታወቃል፡፡ ይህ የሆኔበት በዚህ ንብርብር ውስጥ የ$O_3$ መጠን ከፍተኛ ስለሆኔ ነው፡፡




ሥዕል 1.11. መሬት ከባቢ አየር ንብርብሮች

## 1.3. ተለዋዋጭ አየርና አየር ንብረትን የሚወስኑ ነገሮች

### 1.3.1. ተለዋዋጭ አየርና የአየር ንብረትን ምንነት

**የግምገማ ጥያቄ**

1. አየር ንብረትና ተለዋዋጭ አየርን የሚወስኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
2. በአየረ ንብረትና በተለዋዋጭ አየር መካከል ያለው ልዩነት ግለፅ/ጭ

ዝናብና መጠነ ሙቀት: የተፈጥሮ የዕፀዋቶች ስርጭት ዋና ነገሮችና የአንድን ስርዓተ-እኮ(ecosystem) የሚወስኑ ናቸው፡፡ ዝናብ ብዙ ጊዜ የሚፈጠርበት አካባቢ የተለያዩ የአሬንጓደ ዕፀዋቶች ዘር በብዛት ይኖራሉ፡፡ ዝናብ በለሌበት

ደግሞ የዚህ ተቃራን ይፈጠራል። በቦታና በዘር የሚወሰኑ ዕፀዋቶች ይገኛሉ። የአራዊቶች አይነትና የሰዎች አኗኗር ሁኔታም በዝናብ ሁኔታ ላይ የተመሰረተ ነው። የመጠነ ሙቀት ስርጭት እንደ ዝናብ በዕፀዋቶች ስርጨትና ለሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ ትልቅ ጫና አለው። ስርጭትና ህይወት ያላቸው አይነቶች በትሮፒክስ አካባቢ፣ በመካከለኛ ኬክሮስና በቀዝቃዛ አከባቢ የተለያዩ የሆኔበት ዋናው ምክንያት ከመጠነ ሙቀት ልዩነት የተነሳ ነው።

ለምሳሌ፤ በሞቃታማ ዞን አካባቢ በመገኛ ሁኔታ ዓመቱን ሙሉ ተመሳሳይ ሞቃታማ መጠነ ሙቀት አለው። በሌላ በኩል በዋልታ አካባቢ ረዥም በጋ፣ በጣም ቀዚቃዛና አጭር ቀዚቃዛ ክርምት አሉት። ሌላ ቦታ ደግሞ መካከለኛ መጠነ ሙቀት አላቸው።

ትንሽ ዝናብና መጠነ ሙቀት ያላቸው ቦታዎች የቱኒድራ አካባቢ አየር ንብረት ይፈጥራሉ። ከፍተኛ ዝናብና መጠነ ሙቀት ያላቸው አካባቢ ዝናባማው የምድር ወገብ አካባቢ ደን ይፈጥራሉ። አየር ንብረት ለረዥም ጊዜ በአንድ ቦታ የሚታይ ነው። አንድ አየር ንብረት በትንሹ ለሴላሳ አምስት ዓመታት ይቆያሉ። አየር ንብረት የመጠነ ሙቀት፣ ዝናብ፣ አየር ግፍትና የመሬት ከባቢ እንፋሎት፣ ንፋስ እና የፀሐይ ብርሃን ሁኔታዎች ለረዥም ጊዜ በአንድ ቦታ የሚታዩ ናቸው።

ተለዋዋጭ አየር ማለት ደግሞ የመሬት ከባቢ አየር ክስተቶች በአጭር ጊዜ ውስጥ የሚፈፀሙ/ የሚታዩ ናቸው። ለምሳሌ ጠዋት ቀዝቃዛ ሆኖ ከሰዓት በኃላ ሞቃታማ ከሆኔ፣ አንድ ሳምንት ዝናብ ካገኘና ለላኛው ሳምንት ደረቃማ ከተፈጠረ ነው።

አየር ንብረትና ተለዋዋጭ አየርን የሚወስኑ ነገሮች ማለት የተፈጥሮ ክስተቶች የሙቀት መጠን ወይም ዝናብ አንድ አካባቢ ማግኘት ያለበትን እንዳያገኝ ማድረጊ ነው። ለምሳሌ ኢትዮጵያ በመገኛዋ ምክንያት በዓመት ውስጥ ብዙ ጊዜ ከፍተኛ ሙቀት ማጊኘት ስኖርባት የመሬቷ አቀማመጥ ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ ዝቅተኛ መጠነ ሙቀት እንድታገኝ አድርገዋል።

አየር ንብረትና ተለዋዋጭ አየርን የሚወስኑ (የሚቆጣጠሩ) ነገሮች:

- ✓ የመሬት ከፍታ
- ✓ ኬክሮስ መስመር

- ✓ ከውሃ አካል ላይ ያሌው ርቀት
- ✓ የውቅያኖስ ሞገድና
- ✓ አየር ግፊት እና ንፋስ ናቸው፡፡

**ኬክሮስ መስመር-** ኬክሮስ መስመር የሚያያዘው ከመሬት ምሰሶ መምጣትና በፀሐይ ጨረር አቅጣጫ ነው፡፡ ፀሐይ በትሮፒክስ ጭንቅላት ላይ የሚትውለው (23.5$^0$ በሰሜንና ምዕራብ) መካከል ነው፡፡ በዚህ አካባቢ ከፍተኛ ሙቀት የሚገኘው የፀሐይ ጨረር ዓመቱን ሙሉ በጭንቅላቷዋ ሰለምትውል ነው፡፡ በዋልታዎች አካባቢ የፀሐይ ጨረር በሰፍ አካባቢ ሰለምሰራጭና ከፀሐይ ያለው ርቀት ትልቅ ስለሆኔ ዝቅተኛ ሙቀት ይገኛል፡፡

**የመሬት ከፍታ:-** የመሬት ከፍታ ከባህር ጠለል ላይ 167 ሜትር ወደ ላይ እየጨመሬ በሚሄድበት ጊዜ የአካባቢ አየር መጠነ ሙቀት በ 1$^0$C እያነሴ ይሄዳል፡፡ የዚህ ተቃራን ከፍታው በሚያንስበት ጊዜ የሙቀት መጠን ይጨምራል፡፡ ይህ ሁኔታ የአካባቢ መጠነ ሙቀት ግንኙነት ወይም ቀጥተኛ ግንኙነት በመባል ይታወቃል፡፡ የመሬት ከፍታ መጠነ ሙቀትን እንደምቆጣጠርው አየር ግፊትና ዝናብም ይቆጣጠራል፡፡

**የውቅያኖሶች ሞገድ:-** በዓለም ላይ ሞቃታማና ቀዝቃዛ የውቅያኖስ ሞገድ በመባል በሁለት ይካፈላሉ፡፡ የውቅያኖሶች ሞገድ ትላልቅ የውሃ አካላት ከውቅያኖሶችና ባህሮች ላይ ይነሳል፡፡ የውቅያኖሶች ሞገድ በመሬት ከባቢ አየር ላይ ግፊት (ተፅኖ) ማድረግ ይችላሉ፡፡ ሞቃታማ ሞገድ መሬት ከባቢ አየር ዝናብና መካከለኛ ሙቀት እንድኖረው ያደርጋል፡፡

**አንድ ቦታ ከውሃ አካል ያሌው ርቀት** - አንድ አካባቢ ከውቅያኖስ አካል ወይም ከባህር ላይ ያሌው ለአንድ አካባቢ አየር ንብረት ወሳኝ ነው፡፡ የዚህ ምክንያት በውቅያኖስ ዳር የመሬት አካል አየር ወይም ያሌው ባህር ከሚገኘው ርቀት ጋር የእርጥበት ልዩነት ይኖራሉ፡፡ የውቅያኖስ ዳር የመሬት አካል ወይም ይሌው ባህር እርጥብ አየርና መካከለኛ ሙቀት ካለው የውቅያኖስ አካል ወይም ከባህር ላይ ርቆ የሚገኘው ሞቃታማ አየርና ደረቅ እንድኖረው ያደርጋል፡፡ ለምሳሌ ሞቃታማ የሞዘመብክ ውቅያኖስ ሞገድ በደቡብ ምስራቅ አፍርካ ይገኛል፡፡ ይህ የውቅያኖስ ሞገድ ሞቃታማ ስለሆነ በደቡብ ምስራቅ አፍርካ

መሬት አካል ከፍተኛ ትነትን በንፋስ ወደ መሬት ተገፍቶ ስለምመጣ እርጥበት ለአካባቢ ያደርሳሉ ወይም ይሰጣሉ ማለት ነው። ይህ ስለሆነ ደቡብ ምስራቅ አፍርካ በህንድ ውቅያኖስ ዳርቻ በዓመት ውስጥ ትልቅ ዝናብ የሚያገኝ አካባቢ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ቀዝቃዛ የበንጉላ ውቅያኖስ ሞገድ ደቡብ ምዕራብ አፍርካን የሚያዋስኑ መሬት ላይ ቅዝቃዜና ድርቀት እንድፈጠሩ ያደርጋል።

**የአየር ግፊት**: አየር ገፊት ማለት በአንድ በተወሰነ ቦታ ላይ አየር ያሌው ክብደት ማለት ነው። ይህ የሚያሳየው ከመሬት ስበት ሀይል ሁኔታ ላይ የተነሳ በባህር ጠለል አካባቢ አየር ግፊት ከፊተኛ ስሆን ከፍታው እየጨመሬ ስሄድ አየር ግፊቱ እየቀነሰ ይሄዳል።

## 1.3.2. ተለዋዋጭ አየርና የአየር ንበረት ምንነት

ተለዋዋጭ አየር; አየር ሁኔታ ከቀን ወደ ቀን፣ በሳምንት፣በወርና በዓመት ውስጥ የሚታይ የአየር መቀያየር ነው። አየር ንብረትና ተለዋዋጭ አየር ተመሳሳይ ይዘቶች አሉት። ይህንን ነገሮች ቀጫይነት ባለው መልክ ለመስፈርና ለመመዝገብ የአንድን አካባቢ (ሀገር) አየር ንብረት ለመግለፅ ያገለግላል። ተለዋዋጭ አየር ከቦታ ቦታ ተመሳሳይነት የለውም (ይለያያል)። በአንድ አካባቢ የአንድ ቀን አየር ሁኔታ፤ ሙቀት፣ ደረቅና ፀሐይ ከሆነ ሌላ ቦታ ደግሞ በተቃራን ዳመና፣ ዝናብ፣በረዶና ብርድ ልሆን ይችላል።

የአየር ንበረት ለውጥ የረዥም ጊዜ የአየር ይዘት መጠን ለውጥ ከአስርት ዓመታት ተነስቶ እስከ ሚሊዮን ዓመታት የሚደርስ ነው። የዓለም አየር ንብረት ብዙ ጊዜ የማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ ይገኛል። የአሁኑ የዓለም የአየር ንብረት ለውጥ ላይ ያሌው ተፈጥሮ ሚንጫቸው በሁለት ይካፈላል። አነርሱም ሰው ሰራሽና የተፈጥሮ ናቸው። በተለይ በሰው ልጅ ድርጊት ጋር የሚያያዝ የአየር ለውጥ ዋናው ምክንያት ነው። ይህ የአየር ንብረት ለውጥ በአሁኑ ጊዜ በሙሉ ዓለም በአየር ንብረት ሙሁራን አየተጠና ይገኛል።

# የዓለም አየር ንብረት አካባቢዎች

## የአየር ንብረት አካባቢዎች

የተለያዩ አየር ንብረት አካባቢዎች አሉት፡፡ ከነዚህ ዋና ዋና የሆኑት፡-

(ሀ) እርጥበታማውና ሞቃታማው የአየር ንብረት አካባቢ: ይህ አካባቢ በምድር ወገብ አካባቢ፣ በኮነጎ ቆሪ ዙሪያና ዝቅተኛ መሬት በጊኒ ባህረ ሰላጤ ዳርቻ በስፋት ይገኛል፡፡ በተለይ ከምድረ ወገብ ጀምሮ ወደ ሰሜን 6°ና ወደ ደቡብ 6° መካከል ይገኛል፡፡ በአማካይ የሙቀት መጠን 27°C ይሆናል፡፡ አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን 1500 ሚ. ሜ. በላይ ያገኛል፡፡ ዕለታዊና የዓመት ወራዊ የሙቀት ልዩነት በጣም ዝቅተኛ ነው፡፡ በዚህ አካባቢ የሚገኘው የዝናብ አይነት የትነት ዝናብ (convectional rain) ያገኛል፡፡ ይህ አካባብ ዓመቱን ሙሉ ዝናብ ስለሚያገኝ ጥቅጥቅ ያለው ደንና ውስብስብ በሆነ ደን ተሸፊኖ ይገኛል፡፡

(ለ) እርጥብ ደረቃማ የአየር ንብረት አካባቢ: ይህ አካባቢ እርጥበታማውና ሞቃታማ የአየር ንብረት ቦታዎችን ከቦ ይገኛል፡፡ አካባቢው ከፍተኛ የሙቀት መጠን ሲኖረው በዕለታዊና ዓመታዊ የሙቀት መጠን ልዩነት ከፍተኛ ነው፡፡ ከምድር ወገብ ወደ ሰሜንና ደቡብ በሄድን ቁጥር ልዩነቱ እየሰፋ ይሄዳል፡፡ ይህ አካባቢ ዓመቱን ሙሉ ዝናብ አያገኝም፡፡ ዝናብ የሚያገኘው በክርምት ወቅት ስሆን በሰሜናዊ ንፍቀ ክበብ የክርምት ወቅት (በሰኔ፣ ሐምሌና ነሐሴ) ሲሆን በደቡባዊ ንፍቀ ክበብ ደግሞ (ታህሳስ፣ ጥርና የካቲት) ነው፡፡ የዝናብ መጠን ወደ ሰሜንና ደቡብ በሄድን ቁጥር እያነሰ ይሄዳል፡፡

ይህ አካባቢ ጥቅጥቅ ያለ ጫካን ከቦ ብገኝም ዕፀዋቶቹ እንደ እርጥበታማና ሞቃታማ አካባቢ ውስጥ በቅሎ እንደምገኝ አይደለም፡፡ ጥቅጥቅ ያለ ደን አካባቢ የሚገኝ ፓርክ ሳቫና የሚባል ሲሆን ረጃጅም ሣሮቸና ዛፎች ተቀላቅለው ይበቅሉበታል፡፡ ከፓርክ ሳቫና ወደ ሰሜንና ደቡብ በምንቀሳቀስበት ወደ እውነተኛ ሳቫና (True savanna) እየተለወጠ ይሄዳል፡፡ የሣሮቹ ርዝመት እያጠረ ሄዶ በበረሃ ዳርቻ አካባቢ ወደ ጥሻነት (shrubs)ና አጫጭርና ጠንካራ ሣሮች ይቀየራል፡፡

(ሐ) በረሃማ አየር ንብረት አካባቢ: ይህ አካባቢ ከእርጥበታማ ደረቅ አየር ንብረት ቀጥሎ ይገኛል፡፡ ይህ አካባቢ ከፍተኛ ሞቃታማ በረሃ በመኖር ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ ሣሐራ፣ ናሚብ-ከለሐሪና ሶማሊያ ናቸው፡፡ አንድ አካባቢ በረሃ ለመባል የሚያገኘው አማካይ ዓመታዊ የዝናብ መጠን 250 ሚ.ሜ. በታች መሆን

ይኖርበታል፡፡ ይህ አካባቢ ቀን ቀን በጣም ሞቃታማ ስሆን ሌሊት ሌሊት ደግሞ በጣም ይቀዘቅዛል፡፡ ይህም ዕለታዊ የመጠነ ሙቀት ልዩነት በጣም ከፍተኛ ይሆናል፡፡ ወደዚህ አካባቢ የሚመጣ ድንገተኛ ዝናብ በከፍተኛ ሙቀት ምክንያት ወደ አፈር ውስጥ ሳይገባ በትነት ይጠፋል፡፡ በዝናብ እጥረት ምክንያት የተነሳ በዚህ አካባቢ ዕፀዋት በብዛት አይገኙም፡፡

(መ) የሜዲትራኒያ አየር አካባቢ: ይህ አካባቢ ሰሜናዊ የአፍርካ ዳርቻ በማግሪብ አካባቢና በደቡብ አፍርካ ዳርቻ በኬፕረንጅ አካባቢ ይገኛል፡፡ በዚህ አካባቢ በጋ ወቅት እርጥበታማና ቀዝቀዛ ሲሆን የክርምት ወቅት ደግሞ ደረቃማና ሞቃታማ ነው፡፡

(ሠ) የከፍተኛ ቦታዎች አየር ንብረት: ከፍታ ቦታ ያላቸው መሬት አካባቢ ውስጥ የሚገኝ ነው፡፡ የከፍታ መጠን በጨመረ ቁጥር የሙቀት መጠን እየቀነሰ ይሄዳል፡፡ የመሬት ከፍታ በ167 ሜትር በጨመረ ቁጥር የሙቀት መጠን በ1$^{0}$c ወደ ታች እየቀነሰ ይሄዳል፡፡

## 1.1.3. የተለዋወጭ አየርና የአየር ንብረት ይዘቶች

ተግበራ ; የተለዋዋጭና የአየር ንብረት ይዘቶች የአንድ አካባቢ አየር ሁኔታ ላይ ያላቸው ጫና በአነስተኛ ቡድን በመወያየት ለክፍላችሁ ጓደኞቻቹ ግለፁ? የተለዋዋጭና የአየር ንብረት ይዘቶች የሚባሉት ዝናብ፣ መጠነ ሙቀትና ንፋስ ናቸው፡፡ የተለዋዋጭና የአየር ንብረት ይዘቶች ልዩነት በአካባቢ እየታዩ የመጣው ተለዋዋጭ አየርና አየር ንብረት በሚወስኑ ምክንያቶች የተነሳ የመጣ ነው፡፡ ከዚህ በፍት እንደ ተማርከው ተለዋወጭ አየርና አየር ንበረትን ሚወስኑ፤ የመሬት አቀማመጥ፣ ኬክሮስ የመሬት መስመር፣ አነድ ቦታ ከውሃ አካል ላይ ያለው ርቀትና አየር ግፊት ናቸው፡፡

### የአየር ሁኔታን መሬጃ መስፈሪና መመዚገብ

**ተማሪዋች ብያንስ ልጉናፀፍ የምገቡ የመማር ብቃቶች:**

- የአየር ንብረት ይዘቶች አሰፋፈሪና አመዘጋገብ ስልቶችን ትገነዜባለህ/ሽ
- የተለዋዋጭ አየርና የአየር ንብረት ይዘቶች መረጃ የሚሰበሰብበት፣ የሚመዘገብበትና የሚመረመሪበትን ትለያለህ/ሽ

የሰው ልጅ ለረጅም ጊዜ በሚኖሪበት አካባብ ውስጥ የአየር ንብረት ሁኔታን በመመሪመርና መላሚልት ማድረጉ የታወቁ ነው። ይህም መረጃ ጥንታዊ ግብፅ ከወቅት ጋር በማገናኘት ክርመት ወር በመጣ ጊዜ የናይል ወንዝ በሚሞላበትና በሚቀንስበት የአስቲሮኖሚ ሁኔታን በመመርመር የቆዩ መሆኑን የተለያዩ መረጃዎች ይገልፃሉ።

**መጠነ ሙቀት መስፈር:** መጠነ ሙቀት ማለት የአንድን ነገር የሙቀት ሁኔታ ወይም ቅዚቃዜ ማለት ነው። የአንድ ነገር ሙቀት መጠን ዝቅተኛና ከፍተኛ መሆኑን ለይተን ለመመዝገብ የሚረዳ መሣርያ ተሪሞሜትር ይባላል። ዝቅተኛ ሙቀት ለመስፈር በአልኮል የሚሰራ የተሪሞሜትር አይነት እንጠቀማለን። የአንድን ነገር ከፍተኛ ሙቀት ለመስፈር በመርኩሪ የሚሰራ ተሪሞሜትርን አንጠቀማለን።

**ዝናብ መስፈር:** ዝናብ ለመስፈር የሚንጠቀምበት ዕቃ ሬንገጅ ይባላል። ይህ ዕቃ ትክክለኛ መረጃን ለመመዝገብ ከጣራና ከለሎች ነገሮች ላይ ከሚወረዱ ጠብታዎች አርቆ ማስቀመጥ በጣም አስፈላጊ ነው። የአንድን አካባቢ የዝናብ መዝገብ መረጃ በ24 ሰዓት ውስጥ የሚመዘገብ ይሆናል። የአንድ አካባቢ ዝናብ የረንገጅ የዝናብ ውሃ መያዥ ስሊንደር አንድ ጊዜ 10 ሚ.ሜ. ብቻ ይዩዛል። አንድ ቦታ የሚያገኘው ዓመታዊ አጠቃላይ የዝናብ መጠን የአገዳ ዕህሎች አይነት፣ ሣር ወይም በመስኖ ላይ የመወሰን ድርሻ አለው። ይህ ዓመታዊ የዝናብ መጠን ደግሞ ሙቀትና ከተለያዩ አካላት ውስጥ ከሚወጣው ይወሰናል። በሞቃታማ አንድ አንድ አካባቢ የዝናብ መጠን 250 ሚ.ሜ. በታች ስሆኑ በሞቃታማ ትሮፐክስ አካባቢ ውስጥ ተመሳሳይ አህሎች እስከ 500 ሚ.ሜ ዝናብ ይፈልጋል። ይሁን እንጅ አመታዊ አጠቃላይ የዝናብ መጠን በላይ ወቅታዊ የዝናብ ስርጭት በሚኖረው እርሻ በጣም አስፈላጊ ነው።

**ንፋስ:** ንፋስ የኬክሮስ የአየር እንቅስቃሴ ነው። ሀይለኛ ንፋስ ትነትን በማፋጠን አፈር እንድ ደርቅ ያደርጋል። የአንድ አካባቢ ሙቀት ወይም ቅዝቃዜ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ በማድረስ የአካባቢው ሙቀት እንድመጣጠን ያደርጋል። ዝናብ ለማግኘት ወይም ለማጣት ንፋስ በጣም አስፈላጊ ነው። ንፋስ የሚነፍስበት አቅጣጫ የሚያሳይ መሣርያ ውኒድቬን ይባላል።



ሥዕል 1.12. ውኒድቬን (የንፋስ አቅጣጫ አመልካች መሣርያ)

## 1.3.4 የኢትዮጵያ አየር ንብረት

ከምስራቅ አፍርካ አገሮች ውስጥ ኢትዮጵያ ሰፍ መሬት፣ የተለያዪ የመሬት ከፍታና የተለያዪ አየር አይነት ያላት አገር ነች፡፡ ከእነዚህ ሌላ ምክንያት ለምድር ወገብና ለህንድ ውቅያኖስ ቅርብ በመሆና በጊዜና በተለያዪ ቦታ አየር ንብረትና ተለዋዋጭ አየር የኤለመንቶች ይዘቶች የተለያዪ እንድኖራት ተደርገዋል፡፡ ስለዚህ የኢትዮጵያ አየር ንብረት ይበልጥ የሚቆጣጠረው በተለያዪ ወቅት ከተለያዪ አቅጣጫ የሚነፍስ ንፋስና በመሬቷ አቀማመጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ያላት አየር ንብረት በመሬቷ አቀማመጥና በመጠነ ሙቀት ላይ በመመስረት በአምስት ተከፍለዋል፡፡ እነሱም በረሃ፣ ቆላ፣ ወይን አደጋ፣ ደጋና ውርጭ/ቁር በመባል ይታወቃል፡፡

### ወቅታዊና ዕለታዊ የአየር ሁኔታ ልዩነት

ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በእርጥበታማ ዞን ውስጥ ትገኛለች፡፡ በዚህ ዞን ውስጥ ከመገኘቷ የተነሳ በቀንና ለሊት መካከል ያለው የልዩነት ርዚማነ በጣም ጠንሽ ነው፡፡ በአጠቃላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ከፍተኛ የጊዜ ልዩነት የሚፈጠረው በታህሳስና ሰኔ ወር ውስጥ ነው፡፡ ኢትዮጵያ አራት ታዋቅ ወቅቶች አላት፡፡ እነርሱም ክርምት፣ ፀደይ፣ በጋና በልግ ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 1.2. የወቅቶች ክፍፍል

| ወሮች | የወቅቶች ስም | ፀሐይ የሚትገኝበት ንፍቀ ክበብ ክበብ |
|---|---|---|
| ሰኔ፣ ሐምሌ፣ ነሐሴ | ክርምት | በሰሜን ንፍቀ ክበብ |
| መስከረም፣ ጥቅምት፣ ሕዳር | ፀደይ | በምድር ወገብ አካባቢ |
| ታህሳስ፣ ጥር፣ የካቲት | በጋ | በደቡብ ንፍቀ ክበብ |
| መጋቢት፣ ሚያዝያ ፣ግንቦት | በልግ | በምድር ወገብ አካባቢ |

አብዛኛው የዝናብ ስርጭት ልዩነት የሚፈጥሩ የመሬት አቀማመጥ፣ የንፋስ አቅጣጫና አንድ ቦታ ከውሃ አካል ላይ ያለው ርቀት ላይ ይመሰረታል፡፡ ዝናብ በዓመት ውስጥ ወይም በወቅታዊ የሚፈጠረው በንፋስ እንቅስቃሴ ስርዓትና በዓለም አየር ግፊት መሃል ጋር ይገናኛል፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ የዝናብ ሁኔታ በተለያዩ ወቅቶች ውስጥ እንደምከተለው ተገልፀዋል፡፡

## ሀ. ክረምት

በኢትዮጵያ ውስጥ ክረምት ከሰኔ አጋማሽ ጀምሮ እስከ መስከረም አጋማሽ ነው፡፡ በአፋር ዝቅተኛ ቦታና በደቡብ ምስራቅ የአገርቱ ዝቅተኛ ቦታ በስተቀር ሁሉም አካባቢ ብዙ ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በኢትዮጵያ ውስጥ ለክረምት ዝናብ ከፍተኛ ምክንያት የሆነው የአቲላንትክ ውቅያኖስ በትሮፒክ አካባቢ የሚፈጠረው ከፍተኛ የአየር ግፊት ነው፡፡ ይህ የሚሆነው ደግሞ ንፋስ የጊኒ ባህረ ሰላጤን በመቋረጥ በትነት የተሞላ የሞቀ አየር በመግፋት ወደ ምዕራብ ከፍተኛ ቦታ፣ መካከለኛና ወደ ሰሜን ስለሚመጡ የዝናብ መፍጠር ዕድሉ ከፍተኛ ነው፡፡ ይህም የምሆነው ከሰኔ ወር አጋማሽ ጀምሮ እስከ መስከረም ወር አጋማሽ ነው፡፡ ይህ ወቅት የክረምት ወቅት ይባላል፡፡

## ለ. ፀደይ

የፀደይ ወቅት ከመስከረም ወር ጀምሮ እስከ ሕዳር ወር ያለዉ ጊዜ በውስጡ ያቀፈ ነው፡፡ በዚህ ወቅት አነስተኛው የአየር ግፊት ዕምብርት (መሃል) በምድር ወገብ ላይ ይገኛል፡፡ እርጥበት የሚሸክም ንፋስ ከደቡብ ምስራቅ ህንድ ዉቅያኖስ

ላይ በምነፍሰው ለደቡብ ምስራቅ ኢትዮጵያ ዝቅተኛ አካባቢ ዝናብ ይሰጣል፡፡ ይሁን እንጂ ሌላ አካባቢ ቅዝቃዜና ንፋስ አላቸው፡፡

### ሐ. በጋ

በጋ ፀሐይ ከምድረ ወገብ ርቃ በደቡብ ንፈቀ ክበብ በሚትገኝበት ጊዜ ነው፡፡ ከዚህ በላይ እንደ ተገለፀው የዚህ ጊዜ ቆይታ ታህሳስ፣ ጥርና የካቲት ወር ይሆናል፡፡ በዚህ ወቅት ደረቅ ንፋስ ከሰሜን ምስራቅ ኤሽያ አህጉር ላይ የሚመጣ በኢትዮጵያ አየር ንብረት ላይ ጫና ያደርሳል(ግፊት ይፈጥራል)፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ንፋስ ከወቅቶች ጋር ቢናስተያየው የሚሸፍነው ጥቅት ነው፡፡ ይህ አየር ከቀይ ባህር ላይ ትነት ተሸክሞ በሚመጣበት ጊዜ ለአፋር ዝቅተኛ ቦታና በቀይ ባህር ዳርቻ ጥቅት ዝናብ ይሰጣል፡፡.

### መ. በልግ

በዚህ ጊዜ ፀሐይ ከምድር ወገብ በሰሜን ንፍቀ ክበብ ትገኛለች፡፡ በዚህ ወቅት ከሰሜን ምስራቅ የሚነሳ አየር ግፊት እየቀነሰ ይመጣል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ በዚህን ጊዜ ከደቡብ ምስራቅ ህንድ ባህር ላይ የሚነፍሰው ንፋስ ደቡብ ምስራቅ ከፍታ ቦታ፣ መካከለኛ ዝቅተኛ ቦታና ለደቡብ ምስራቅ ዝናብ ያመጣሉ፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ዝናብ ብዙ ጊዜ ወቅቱን ጠብቆ የሚፈጠር አይደለም፡፡ በልግ ወቅት የሚባሉት መጋቢት፣ ሚያዝያና ግንቦት ወሮች ናቸው፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ

የመሬት አቀማመጥ መቀየር የሚችሉ ሀይሎች በመሬት ውስጥና በመሬት ገፅታ ላይ በሚፈጠሩ ሀይሎች ነው፡፡ በመሬት ውስጥ የሚፈጠሩ ሀይሎች እንደ እሳተ ጎሞራና የመሬት መንቀጥቀጥ ስሆኑ የመሬት ገፅታን የሚቀይሩ ደግሞ የውሃ ጎርፍ፣ንፋስና የሚሸራተት በረዶ ነው፡፡

ተለዋዋጭ አየር የአንድ አካባቢ አየር ፀባይ በአጭር ጊዜ፣ ቀን በቀን፣ ሳምንት በሳምንት፣ ወር በወርና በዓመት ውስጥ የሚታይ ነው፡፡ አየር ንብረት የአንድ

አካባቢ አየር ሁኔታ አማካይ ለረጅም ጊዜ ብያንስ ከ35 ዓመትና ከዚያ በላይ የሚታወቅ ነው፡፡ ስለ ተለዋዋጭ አየር ሁኔታን የሚያጠና ሳይንስ ሜትሮሎጂ ስባል ስለ አየር ንብረት የሚያጠና ሳይንስ ደግሞ ኪላማቶሎጂ ይባላል፡፡
ኢትዮጵያ ሙሉ በሙሉ በትሮፕክስ አካባቢ ውስጥ ትገኛለች፡፡ ይሁን እንጂ በመሬቷ አቀማመጥ ምክንያት በዓለም ውስጥ ያሌ የአየር ንብረት ሁኔታ በውስጥ ይታያል፡፡

የዓለም ሙቀት መጨመር፣ የድርቅ መከሰት፣ የአካባቢ ሙቀት መጨመር፣ የበረሃ መስፋፋት፣ የዝናብ እጥረት፣ የተለያዩ ሕይወት ያላቸው ነገሮች መጥፋት፣ የተለያዩ በሽታዎች መስፋፋት ዋና ምክንያቶች ናቸው፡፡ ይህን የአየር ለውጥ ለመቀነስ ከሚሰራ ሥራዎች ውስጥ ጥቅቶቹ ዕፀዋት መትከል፣ የዓለምን ሙቀት የሚጨምሩ አይነቶች መቀነስ፣ በደንና እራሳቸውን የሚያድሱ ሀይሎች መጠቀምና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የምዕራፍ አንድ ማጠቃለያ መልመጃ

### I. ከሚከተሉትን ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ

1. ውስጣዊ ሀይሎች የመሬትን ገፅታ የሚቀይሩ የትኞቹ ናቸው? ስማቸውን ፃፍ/ፊ
2. የአየር ንብረትና አየር ሁኔታ ይዘቶች ምን ምን ናቸው?
3. አየር ንብረትና አየር ሁኔታን የሚቆጣጠሩ (የሚወስኑትን) ዘርዚር/ሪ
4. የመሬት አቀማመጥን የሚቀይሩ የቅርፊተ መሬት ሀይሎች የትኞቹ ናቸው?
5. በኢትዮጵያ ውሰጥ ከሚታዩ ወቅቶችን ከወራቸው ጋር ፃፍ/ፊ

### II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ የያዜውን ፊደል በመምረጥ መልስ/ሽ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የቅርፊተ መሬት ሀይል ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የውሃ ጎርፍ ለ. በንፋስ የሚፈጠር መሸርሸር
   ሐ. የመሬት መንቀጥቀጥ መ. የመሸራተት በረዶ
2. የኬሚካላዊ ለውጥ ሂደት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. የበረዶ ክምችት ሐ. በአለቶች ውሰጥ ያሉ ነገሮች መብላላት

ለ. የአፈር መሸርሸር መ. በንፋስ የሚፈጠር ክምችት

3. ፊዚካላዊ ለውጥ በምን ይፈጠራል ?

ሀ. እንስሳት ለ. ውሃ ሐ. ንፋስ መ. ሁሉም መልስ ናቸው

### III. በ “ለ” ሥር የተዘረዘሩትን ከ “ሀ” ሥር ከተዘረዘሩት ግር አዛምድ/ጂ::

| ሀ | ለ |
| --- | --- |
| 1. የመሬት መንቀጥቀጥን የሚሰፍር መሳርያ | ሀ. መፈንዳት ዕድል የሌለው እሳተ ጎሞራ |
| 2. አድፋጭ እሳተ ጎሞራ | ለ. የፊሸሪ ቀዳዳ(ጉድጋድ) |
| 3. ተንቀሳቃሽ እሳተ ጎሞራ | ሐ. ሬተር እስከል |
| 4. ፈንድቶ ያለቀለት እሳተ ጎሞራ | መ. አቧራና ጭስ |
| 5. ከእሳተ ጎሞራ ጋር ከመሬት ውስጥ የሚወጡ | ሠ. በተደጋጋሚ የሚፈነዳ እሳተ ጎመራ |
| 6. በአንድ ቀዳዳ የሚወጣ እሳተ ጎሞራ | ረ. በልታወቀ ጊዜ የሚፈነዳ እሳተ ገሞራ |
| 7. በብዙ ቀዳዳ የሚፈነዳ እሳተ ጎሞራ | ሰ. ቬንት |

# ምዕራፍ 2

# ሕዝብና የማህበራዊ-ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ

## የዚህ ምዕራፍ ትምህርት ውጤቶች

ተማርዎች ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት አካሄድና መጨረሻ በኃላ:

- ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለውን የሕዝብ ባህል እድገትና መለወጥ ትገልፃለህ/ሽ
- የ ባህል መገለጫዎችን ትገልፃለህ/ሽ
- በሕብረተሰብ ባህል ላይ ግሎባላይዘሽን ያሌውን ጫና ትገልፃለህ/ሽ
- በሕብረተሰብ ባህል መካከል ያሌው ልዩነት ታከብራለህ/ሽ
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምንነትና ባህርያቸውን ትገልፃለህ/ሽ
- የተለያዩ የአገሮች ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ከእድገታችው ደረጃ ጋር በመያያዝ ትናገራለህ/ሽ
- የመረጃ ስርጭት፣ ምርትና የአገልጊሎት መሰጫ ልዩነትን ትገልፃለህ/ሽ
- ፍላጎትና አቅርቦት በገብያ ምርት ዋጋ ላይ ያለውን ጫና ትገነዘባለህ/ሽ
- የግብርና የታኪስ ታርክ ትናገራለህ/ሽ

### መግብያ

የዓለም ሕዝብ በሙሉ ባህልና የራሳቸውን መለያ አላቸው። ባህል የአንድን በሔረሰብ ማንነት የምገለፅ ነው። በባህላዊ መገለጫ ውስጥ ከሚታቀፉ እንደ ቋንቋ፣ ሐይማኖትና የሕዝብ አኗኗር ሁኔታ ናቸው።

በአጠቃላይ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሦስት አይነት ይካፈላሉ። አነርሱም፤ የአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴና የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ናቸው። በዚህ ምዕራፍ ውሰጥ ስለ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በስፋት ትማራለህ/ሽ። በተጨማርም ስለ ግብር፣ ታክስ፣ የፍላጎትና አቅርቦት ግንኙነት ትገነዘባለህ/ሽ።

## ቢያንስ ሊደረስበት የሚቻል የመማር ብቃቶች

በዚህ ርዕስ ትምህርት በኃላ:

- የባህል ምንነትና ለዕድገታቸው ምክንያት የሆኑ ነገሮችን ትገልፃለህ/ሽ
- ቋንቋና ሀይማኖት የባህል መገለጫ መሆኑን ትገልፃለህ/ሽ
- የሕዝብ ባህል መለወጥ ላይ ግሎባላይዘሽን ያለው ተፅኖ ምን እንደ ሆነ ትገልፃለህ/ሽ
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ምንነትና አይነት በተለያዩ ደረጃ ትገልፃለህ/ሽ
- ፍላጎትና አቅርቦት በምርት ገበያ ዋጋ ላይ ያለውን ጫና ትገልፃለህ/ሽ
- የገቢና የግብር ምንነትን ትለያለህ/ሽ

## 2.1. የባህል ልዩነትና መለወጥ

### የግምገማ ጥያቄዎች

ሀ. ባህል ምንድነው?

ለ. የባህል መገለጫዎች ምን ምን ኛቸው?

ሐ. የሰው ልጅ ባህልን በምን ሁኔታ እንደምያሳድግ በቡድን በመወያየት ለክፍል አቅርቡ

ባህል የሰው ልጅ በውስጡ የቆየበት ሙያ፣ የኗኗር ሁኔታ፣ እውቀትና ልምድ ነው፡፡ የዓልም  በሙሉ የራሳቸው የሆኔ ባህልና መለያ አላቸው፡፡ እንደ ኢትዮጵያ፣ ናይጀርያ፣እንዶንዥያና የመሳሴሉት አገሮች የተለያዩ ባህል፣ በሔርና በሔረሰብ በመኖር ይታወቃሉ፡፡ ባህል የአንድ በሔር መገለጫ ስሆን እርስ በርስ የሚማማርና የሚዋዋስ ነው፡፡ የባህል ልዩነት መኖር የዓለም ሕዝብ በሙሉ እውቀትና ልምድን ከእርስ በርሳቸው እንድማማሩ ያግዛል፡፡

### 2.1.1. የሕዝብ ባህል እድገት

የሰው ልጅ ከለሎች አራዊቶች ላይ የሚለይበት ለኑሮ የሚያስፈልጋቸው ነገሮች መፍጠር የጀመረው በድንጋይ ዘመን ውስጥ ነበር፡፡ ስልጣኔ ድንጋይ ዘመን የሚንለው ለሰው ልጅ የሚያስፈልጋቸው የተለያዩ ዕቃዎች ከድንጋይ

ላይ የሰራበት ጊዜ ነው፡፡ ይህ የታርክ ዘመን የዛሬ 2.5 እስከ 5000 ሚሊየን ዓመታት አካባብ የቆዬ ነው፡፡ አነኚህ የድንጋይ ዘመኖች በሦስት ዋና ዋናዎች ይካፈላሉ፡፡ እነርሱም፤ ጥንታዊ የድንጋይ ዘመን፣መካከለኛ የድንጋይ ዘመንና ዘመናዊ የድንጋይ ዘመን በመባል ይታወቃል፡፡ ይህ በድንጋይ መጠቀም ደግሞ የእንዱስትሪ ዘመን ድንጋይ እንድባል አድርጎዋል፡፡ በለላ በኩል የዚህ ዘመን ስም የሰው ልጅ ባህላዊ አብዮት ዘመን ይባላል፡፡

የሰው ልጅ በሦስቱ በድንጋይ ዘመናት ውስጥ ባህልና የተለያዩ ችሎታዎችን አሳድገዋል፡፡ እንደ አርኪኦሎጆስቶችና የታርክ ሙሁራን ገለፃ የሰው ልጅ ባህል ማደግ የጀመረው በዝህ ዘመናት ውስጥ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ጥንታዊ ድንጋይ ዘመን(ከ 2.5 እስከ 200000 ሚሊየን ዓመታት) ውስጥ የተለያዩ መሣርያዎች ከጠንካራ ድንጋይ ላይ መስራት ችለዋል፡፡ አነኚህ መሳርያዎች ጠናካራ በመሆናቸው አጥንት መቁረጥና መስበር ይችላሉ፡፡ በተጨማሪም ሥጋ መቁረጥ፣ እንጨት መሾልና መቅረፅ፣ አታክሊትና ፍራፍሬ ወይም የተለያዩ ፍራፍሬዎች ለመቆራረጥ ተጠቅሞዋል፡፡ ከዚህ ውጭ በእሳት የመጠቀም ችሎታ፣ የመናገር ችሎታ፣ ከቆዳ ላይ ልብስ መስራትና በዋሻ ውስጥ መኖር ጀምሮዋል፡ ፡ እንደ ቤት የሚኖሩበት ዋሻም በቀለምና በተለያዩ ቅርፃቅርፅ ማሳመር ጀመሩ፡ ፤ ሀይማኖትም በዚሁ ጊዜ እንደተጀመረ ይታሰባል፡፡ ስለዚህ ይህ የመጀመርያ ድንጋይ ዘመን (ጥንታዊ) የሙያ እድገትና የባህል  መሰረት ነው፡  በመካከለኛ ድንጋይ ዘመን(200,000 - 40,000) የሰው ልጅ ባህላዊ እድገትን ለማስቀጠል የተለያዩ ፈጠራዎችን ፈፅመዋል፡፡ የዚህ ዘመናት እዉቀትና ፈጠራ ውስጥ ትልቅ ድርሻ ያለው እንስሳቶችና ዕፀዋቶችን ከሰው ጋር ማላመድ ነው፡፡ በዚህ ጊዜ ውሰጥ የሰው ልጅ በጫካ ውስጥ የሚኖሩ አራዊቶችን በማስጠጋት እንደ ውሻ በማላመድ አብረው መኖር ጀምረዋል፡፡ የተለያዬ ፍራፈሬዎችን በጫካ ውስጥ ሄዶ ከመልቀም በሚኖሬው ዋሻ አካባቢ በመዝራት መጠቀም ችለዋል፡፡ ይሁን እንጂ በከፍተኛ ደረጃ እንስሰቶችና ዕፅዋቶችን መላመድ የቻለው በአድሱ የድንጋይ ዘመን ውስጥ ነው፡፡  ለማብሰያና ለመቀቀያ አገልግሎት የሚውል የተለያዩ ዕቃዎች ከሸክላ መስራት የጀመሩት በዚሁ ዘመን ውስጥ ነው፡፡

የሰው ልጅ በአድሱ ድንጋይ ዘመን (40,000-5,000) ውሰጥ የሙያ እድገትና ለዘመናዊ ኑሮ ባህል መነሻ የሚሆኑትን አሳድገዋል፡፡ በለፉት ሁለት በድንጋይ

ዘመናት ውስጥ ያሳደገውን ባህል፣ ሙያና ችሎታን በማጠናከር በአድስ መልክ ለኑሮ አዘጋጅቶዋል፡፡ በተለይ እርሻ ሥራ ለመጀመር በእንስሳቶች ጉልበት መጠቀም መቻሉ ትልቅ ነው፡፡ ስለዚህ ይህ ዘመን በታርክ ሙሁራን 'የእርሻ አብዮት ዘመን' በመባል ይታወቃል፡፡ እንደ መሶፖታምያ፣ ምስር(ግብፅ)፣ ኑቢያ አካባቢና በተለያዩ የአፍርካ ሸለቆዎች ውስጥ በሂደት እርሻ ተጀምረዋል፡፡ ከእርሻ ጋር ተያይዘው የተለያዩ የእርሻ ዕቃዎችና ባህላዊ የእርሻ እህል ማጠራቀምያ ግንባታ አድገዋል፡፡ በለላ በኩል ሰው ልጅ ቋሚ በሆኔ ቦታ ላይ የእርሻ ስራ መካሄዱ በአንድ ቦታ እንድሰፍር አድርገዋል፡፡ የአሰፋፈር መቀጠል በሂደት ወደ ከተማዎች ምስረታና እድገት ተሻግረዋል፡፡

የከተማዎች መስፋፋት ደግሞ የመንግስቶች መመስረትና አስተዳደራዊ እድገት አመጣ፡፡ አስተዳደራዊ እድገት ሕጎችና የተለያዩ ደንቦችና በባህላዊ አስተዳደር የድንበር ማስከበር ልምድ ሥራ ላይ እንድውል አድርገዋል፡፡

በአጠቃላይ የሰው ልጅ የተለያዬ ሙያ፣ የገዳ ባህልና ደስታን የሚገልፅበትን ማሳደግ የጀመረው በሦስቱ በድንጋይ ዘመናት ውስጥ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በሂደት የቢረትና የናስ ዘመናት በፍት ያለውን ባህል ይበለጥ እያጠናከረ አሁን ያለበትን ደረጃ ላይ መድረስ ችለዋል፡፡

## 2.1.2. የባህል ዋና መገለጫዎች (ቋንቋ፣ ሀይማኖት ናቸው )

### ቋንቋ

ከዋና ዋና ባህላዊ መገለጫዎች ውስጥ አንዱ ቋንቋ ነው፡፡ ከዚህ በላይ መግለፅ እንደ ተቻለው የሰው ልጅ በቋንቋ መጠቀምና መስማማት ከጀመረ በጥንታዊ ድንጋይ ዘመን ውስጥ ነው፡፡ በዚሁ መሰረት ከዚህ ዘመናት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሚንገባባው በቋንቋ ነው፡፡ ይሁን እንጂ የተለያዩ የዓለም ህዝቦች የሚስማሙበት የተለያዬ ቋንቋ አላቸው፡፡ ሁሉም ቋንቋ እኩልና የሚስማሙበት መሣርያ ነው፡፡

ሕዝቦች ሀዘንና ደስታቸውን የሚገልፁበት በቋንቋ ነው፡፡ የተሰማውን ሀዘን በዘፈን፣ በግጥምና በለቅሶ ይገልፃሉ፡፡ በደስታ ጊዜም በዘፈን፣ በቀረሮ ፎከራና በተለያዩ ዳንስ ይገልፃሉ፡፡ የተለያዩ ሕጎችና ደንቦችን ለማውጣትና ለማወጂ ቋንቋን

በመጠቀም ውይይት ያካሄዳሉ፡፡ በውይይት መጨሬሻ ላይም የተስማሙበትን ሀሳብ በተለያዬ ቃላትና ዐረፍተ ነገር በመጠቀም ያስተዋዉቃሉ፡፡ ስለዚህ ቋንቋ ለማንኛውም ህብረተሰብ የሀሳብና ፍላጎት መገለቻ መሳርያ ነው፡፡

## ሀይማኖት

የሰው ልጅ ሀይማኖት መከተል የጀመረው በጥንታዊ ድንጋይ ዘመን እንደሆኔ ይታሰባል፡፡ የሰው ልጅ ከዚህ ዘመናት ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ የሀይማኖት ጉዳይን እያካሄድ ቆይተዋል፡፡ ሀይማኖት ከእግዚአብሔር(ከፈጣሪ) ጋር የሚገናኝ ሁኔታ ነው፡፡ የሰው ልጅ በሙሉ የዚህ ዓለም ፍጥረታት በሙሉ የሚገዛ (የመያተዳድር) አንድ አካል አለ ብለው ያምናሉ፡፡ ይህም እግዚአብሔር / አምላኪ አንደሆኔ የአጠቃላይ ግንዛቤ ሀይማኖቶች ናቸው፡ ይሁን እንጂ የሚያምኑበት ሁኔታና ሀይማኖታቸውን የሚያካሄዱበት ዘዴ የተለያዬ ነው፡ ፡ ሁሉም ሀይማኖቶች ሰው ልጅን ጥሩ ነገር የሚያተምሩና የሚመኙ ናቸው፡፡

እንደ ሀይማኖቶች አስተሚሮ የሚከበሩ ነገሮችና የሰውን መብት የሚጋፉትን ያወጊዛሉ፡፡ ለምሳሌ ስርቆት፣ ውሸት፣ መጊደል፣ የሕፃናትና ሰቶች መብት የሚግፉ ይከለኪላሉ፡፡ በቂንነታቸው ውስጥ ሰላምን፣ መረዳዳትን፣ መተጋገስን፣ በቀጥተኛና በእውነት መሥራት የሚል ነው፡፡ በተጨማርም ሁሉም ሰው እኩል ያስባል በሚለው ሀሳብ ላይ ይስማማሉ፡፡ ከዚህ ውጭም የተፈጥሮ ሀብቶች እንክብካቤና አጠቃቀም የሚያበረታቱ ስሆኑ ሁሉም ሰው ሰላም ኑሮ እንድኖር ይመክራሉ፡፡ ሀይማኖትም እንደ ቋንቋ በ መካከል ያለውን የተለያዬ ግንኙነትን የሚያበረታታ ነው፡፡

## 2.1.3. ግሎባላይዘሽንና የሰው ዘርና ባህል መለወጥ

የግምገማ ጥያቄዎች

1. ግሎባላይዘሽን ምንድነው?
2. ግሎባላይዘሽን በህብረተሰብ ባህል ላይ ያለው ጥቅምና ጉዳት ምን እንደሆኔ ግለፅ/ጭ

የግሎባላይዘሽን መሰረታዊ ሀሳብ በቀላል መንገድ ስገለፅ ሰው ልጅ ያለው የአጠቃላይ አውታር (network) ማለት ነው፡፡ የዓለም በሙሉ መገናኛ ነው፡፡ በተጨማርም የዓለም የአንድነት ሀሳብ የሚለውን በውስጡ ይዘዋል፡፡ ግሎባላይዘሽን የሚሰፋበት መንገድ፤ የገንዘብ ምንጭ፣ ምርት፣ ሕዝብ፣ ሀሳብ፣ ዕውቀትና መረጃ ነው፡፡ ከዚህ ውጭም ተክኖሎጂና የተለያዩ መገናኛ ብዙሃንን ያቅፋል፡፡ የሚገለፅበት መንገድ ደግሞ በኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ፣ ማህበራዊና ባህል ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ዓለም በአሁኑ ጊዜ በአንድ መንደር ደረጃ እየተገናኘች ነው፡፡ ይህ በአጠቃላይ ግሎባላይዘሽን የሚለውን ሀሳብ የሚገልፅ ነው፡፡

ግሎባላይዘሽን የሚከተሉትን ጥቅሞች አሉት፡፡ እነርሱም፤ በኢኮኖሚ ገበያ ላይ የተሻሻሉ አገሮች በከፍተኛ ውድድር ውስጥ እንድገቡ ያደርጋል፡፡ ይህ ማለት ደግሞ በአገሪቱ ውስጥ ያለው ሀይል በሥራ፣ ችሎታና በላቸው ዕውቀት እንድሰሩና እንድጠቀሙ ያግዛል ማለት ነው፡፡ በተጨማሪም በዓለም ላይ ያለውን የፋይናንስ ውድድር ያጠናክራል፡፡ እንደዚያውም በግሎባላይዘሽን ሂደት ውስጥ ተጠቃሚዎች የተለያዩ ዕቃዎችን በማስተያየት በርካሽ ዋጋ እንድገዙ ያደርጋል፡፡ በአጠቃላይ በግሎባላይዘሽን ስርዓት ውስጥ እንቅስቃሴ ያላቸው አገሮች ይበልጥ ወደ ከፍተኛ ደረጃ እንድሻገሩ ያደርጋ፡፡ ለምሳሌ አንደ ህንድና ቻይና ያሉ አገሮች በዚህ መንገድ ልያድጉ ችለዋል፡፡

በለላ በኩል ግሎባላይዘሽ ዋና ዋና ጉዳቶች አለው፡፡ የዓለም  ያላቸው ጊንኙነትና ዝምድና የሚያጠናክር ሂደት አገራዊ ሁኔታና ባህል እየተረሳ ይሄዳል፡፡ ከእነዚህ ውስጥ ዋናዎቹ አገራዊ ሁኔታና የመጀመርያ ባህል እየተረሳ ወይም መላላት ይችላሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ በአሁኑ ጊዜ የዓለም  በሙሉ የውጭ አገር ፍልም ያያሉ፣ የሮኪ ሙዚቃ ያዳምጣሉ፣ የተለያዩ መጠጦች መጠጣትና ቲምባሆ ማጨስ አሳድገዋል፡፡ ከዚህ ውጭም የውጭ አገር እግር ኳስ ማየት፣ ከኢሴት (moral) ውጭ የሆኑትን የውጭ ምድያ በመከታተል ጊዜያቸውን ማሳለፍ፡፡ የፋሽን ልብስ በማለት ልብስና ባህላዊ የምግብ አይነት ከመጠቀም ይልቅ የውጭ አገር መልበስ ይወዳሉ፡፡ በአጠቃላይ የኢሰት ባህሪና የአካባቢ ህብረተስብ ክብር የምሰጡትን አለማክበርና አገር መጥላት፡፡

**መልመጃ 2.1**

1. ባህል ምንድነው?
2. በአገራችን ውስጥ የሚገኙ ባህሎች የትኞቹ ናቸው?
3. ባህል ከአንድ አካባቢ ወደ ለላ አካባቢ እንደት መስፋፋት ይችላል?
4. በግሎባላይዘሽን ውስጥ ባህል እንደት ይቀየራል?

## 2.2. ዋና ዋና የኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

የሰው ልጅ ለመኖር ስባል በተለያዩ ሥራዎች ላይ በመሰማራት ኑሮውን ያካሄዳል፡፡ ከእነዚህ አንዱ አርሶ አደር ስሆን ለላ ደግሞ  የፋብርካ ሰራተኛ፣ የእንጨት ስራ፣ መንግስት ሰራተኛና በተለያዩ ሙያ ላይ በመሰማራት ለኑሮአቸው ገብ የሚሆን ላይ ይሰማራሉ፡፡የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሦስት ዋና ዋናዎች ይካፈላሉ፡፡

### 2.2.1. የአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. በሰው ኑሮ ሁኔታ ውሰጥ ሰወ ለመኖር ስል ምን ዓይነት ስራ ሰርቶ ገብ እንደምያገኝ በቡድን በመሆን ተወያይታችሁ ለክፍላችሁ ሪፖርት አቅርቡ
2. የኢትዮጵያ  ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የበለጠ እጅ ምንድነው?
3. ባደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች የእርሻ ልዩነት ምንድነው?

የአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት በተፈጥሮ ያለውን ሀብት የሰው ልጅ ለማግኘትና በመጠቀም ኑሮን መምራት ማለት ነው፡፡ ይህ የተፈጥሮ ሀብት አፈር፣ አለቶች፣ ውሃ፣ ደንና የመሳሰሉትን በውስጡ ያቅፋል፡፡

በአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚመደቡ ሥራዎች እንደ እርሻ፣ ዓሣ ማጥመድ፣ ማዕድን ማውጣት፣ ደን ማንከባከብ፣አደንና የመሳሰሉትን ያቅፋል፡፡

## እርሻ

እርሻ፡ ማለት የሚበላ ነገሮች ለማግኘት ወይም የኢኮኖሚ እድገት ለማምጣት ስባል እህሎችን የማምረትና የቤት እንስሳት ማርባት ማለት ነው፡፡ እርሻ ታስቦበት የሚከናወን የሥራ መስክ ነው፡፡

### የእርሻ መጀመር

እርሻ የተጀመረው ከ6000 ዓ.ም በፍት ነበር፡፡ እርሻ ለመጀመርያ ጊዜ የተጀመረው በደቡብ ምስራቅ ኤሽያ አገሮች ውስጥ ነው፡፡ እርሻ ቀስ በቀስ ከደቡብ ምስራቅ ኤሽያ እምብርት ወደ ቻይና፣ ጃፓን፣ደቡብ ምዕራብ ኤሽያ፣ አፍርካና አውሮፓ ተስፋፍተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ከዓለም ሕዝብ ውስጥ 67% በእርሻ የሚተዳደር ነው፡፡ ስለዚህ ሰፍ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ብዙ ሕዝብ የሚተዳደርበት ነው፡፡ እርሻ ሳይጀመር በፍት ለሰው ልጅ የምግብ ምንጭ አደንና ፍራፍሬን ከእንጨት በመልቀም ይኖር ነበር፡፡

### የእርሻ አይነቶች

1. በውጤት ላይ በመመሰረት

ሀ. እህል ማምርት: በዚህ ግብርና ውስጥ የሚመረት እህል በሁለት ይካፈላል፡፡ እነርሱም፤ የምግብ እህልና ለውጭ ምንዛሪ የሚውል ነው፡፡

ለ. ከብት እርባታ ግብርና: ይህ ደግሞ እንስሳቶችን ማርበት ነው፡፡ ይህም ብዙ ጊዜ ለእርሻ ተስማም ያልሆኔ መሬት ላይ ይካሄዳል፡፡ ከብት ማርባት የምግብ ዓላማን ለማማላትና ለገቢ ምንጭ ለማድረግ ይውላል፡፡

ሐ. ጥሚር ግብርና: የዕፀዋት ሚርትና ከብት እርብ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴን በአንድ ላይ የሚካሄድ ነው፡፡

በጊዜ ቆይታ ላይ ተመስርተው

ቋሚ ግብርና: ለረዥም ጊዜ በአንድ ቦታ ላይ የሚቆይ የግብርና አይነት ነው፡፡

ተንቀሳቃሽ ግብርና: ተንቀሳቃሽ ግብርና በከፍተኛ ዝናብና መጠነ ሙቀት ያሌበት ቦታ አፈር በፍጥነት ስለምሸረሸር ከአፈር ውሰጥ ማዕድን ይጨርሳል፡፡ ይህ ስለሆኔ ምርቱ ይቀንሳል፡፡ ይህ ደግሞ እዝህ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች

የመሬት ሌምነት ስለምቀንስ አርሶ አደሮች የእርሻ መሬትን ለመቀየር ደንን በመጨፍጨፍ በአድስ መሬት ላይ ግብርናን ያካሄዳሉ። ይህ የእርሻ መሬትን በመቀየር የምርት ማምርት ሂደት ተንቀሳቃሽ ግብርና ይባላል።

2. **በጉልበትና ገንዘብ ደረጃ በሥራ ቅንጅት ላይ ወጭ መሆን**

i. **ክብካብ ግብርና (intensive farming):** በትንሽ መሬት ላይ ትልቅ ጉልበትና ገንዘብ በመጠቀም ምርት ማምረት ነው። ይህ አይነት ግብርና ትልቅ የሰው ጉልበት በማሰማራት ከፍተኛ ምርት ማስገኘት መቻል ነው።

ii. **የሰፊ መሬት ግብርና (extensive farming):** በሰፊ መሬት ላይ ከፍተኛ የሰው ጉልበትና ቀላል ትኪኖሎጂን በመጠቀም ምርት ማምረት ነው። ይሁን እንጂ ከሰፊ መሬት ጋር ስታይ የሚመረትበት ምርት ትንሽ ነው።

## ባደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ውስጥ ግብርና ያለው ድርሻ :

ግብርና ለሁሉም አገሮች የመብል ምግብና ለፋብርካ የሚቀርብ ለላ ጥሬ ዕቃዎች የሚያገኙበት መንገድ ነው። ባደጉ አገሮች ውስጥ ግብርና በተለያዩ ተክኖሎጅ በመጠቀምና በተሻሻለ መልክ የሚካሄድ ነው። ለዚህ ነው የግብርና ምርት ባደጉ አገሮች ውሰጥ የሚመረት ከፍተኛ የሆነና ሕዝቡ የተንደላቀቀ ኑሮ የሚኖረው። በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ውስጥ ደግሞ ምርቱ ትንሽ ነው። ይህም የምግብ አህል ፍላጎት መሙላት የማይችል ነው።

አገራችን ጨምሮ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ከፍተኛ ገብ የሚያገኙት ከግብርና ላይ ነው። በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ውስጥ ግብርና የኢኮኖሚ ጀርባ አጥንታቸው ነው። ከኢትዮጵያ ሕዝብ ውስጥ 85% የሚሆኑ ኑሮአቸው በግብርና ላይ ነው የተመሰረተው።

በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ወደ ውጭ በመላክ የውጭ ሚንዛሪ የሚያገኙት ከግብርና ምርት የሚገኝ ነው። በኢትዮጵያ ውስጥ ግብርና ያለው ጥቅም ብዙ ነው። ከእነዚህ ውስጥ የምግብ እህል ምንጭ፣ የገቢ ምንጭ፣ ብዙ ሕዝብ የተሰማራበት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ፣ ለኢንዱስትሪ የሚያስፈልጋቸው ጥሬ ዕቃዎች የሚገኙበትና ለአጠቃላይ ለአገርቱ ከፍተኛ ምርት እርዳታ የሚሰጥ ነው።

## ዓሣ ማስገር

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. ዓሣ የሚጠመድበት መንገድ ስንት ነው? በቡድን በመወያየት ለክፍላችሁ ግለፁ።
2. በአገራችን ውስጥ የዓሣ ማጥመድና መብልት ባህል ምን ይመስላል?

ዓሣ ማጥመድ ከአደን ሥራ ውስጥ አንድ ስሆን በወንዞች፣ በሀይቆች፣ በባህሮችና ውቅያነሶች ውስጥ በመሰረታዊ ሥራ የሚካሄድ ነው። እነርሱም:

**ሀ. በባህላዊ መንገድ:** በባህላዊ መንገድ የዓሣ ማጥመድ ዘዴ በባህላዊ መሣርያ ሰሆን የሚገኘው ውጤት በጣም ትንሽ ነው። የተያዙት ዓሣዎቹም ትንንሽና ለመብል የማይውል ነው። በባህላዊ መንገድ ለዓሳ መያዣ የሚያገለግሉት እንደ ስለት ያለው ድንጋይ፣ የዓሣ መያዣ ጦርና ሁኮ ናቸው።

**ለ. በዘመናዊ መንገድ:** በሳይንስና ተክኖሎጅ መስፋፋት ምክንያት ዘመናዊ መሣርያን በመጠቀም በቂና ለምግብ የሚውሉ ዓሣዎችን መያዝ ነው። ዓሣን ለመጥመድ የሚያገለግሉ ዘመናዊ መሣርያዎች እንደ መረብ መዘርጋት፣ የሳይን ቲራውሎች መረብና ሊነሮች ኛቸው።

## የደን ሥራ

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. የደን ሥራ ማልማት ማለት ምን ማለት ነው?
2. አንቴ/ች ያለባችሁ አካባቢ የደን ሥራ እንደት ይካሄዳ?

የደን ሥራ ማለት ደንን በማልማት ከደን የሚገኙ ውጤቶች ለተለያዩ አገልግሎት ማዋል ነው። የደን ሥራ ሳይንሳዊ ወይም እንጨት መትከልና ማሳደግ ዘዴ የተለያዬ ምርቶችን ተከታታይ ባለሁ ሁኔታ፣ በከፍተኛ ጥራት ውጤትና በስፋት በማምረት ለተለያዩ አገልግሎት ለማግኘት መስራት ነው።

## የደን ሥራ አይነቶች:

**የደን ሥራ ለውበት:** የደን ሥራ ለውበት ማለት የደን ማልማት ሥራዎችና በመከባከብ ለውበት ወይም የተፈጥሮ አካባቢ ውበት ለመጠበቅ የሚከናወን ነው፡፡ ለምሳሌ፤ በመንገድና በመዝናኛ ቦታዎች ውበት ያለቸው እንጨቶችና ለጥላ የሚያገለግሉ መትከል ናቸው፡፡

**የደን ሥራ ለንግድ:** የደን ሥራ እንጨት ለሽያጭ የሚውሉ በስፋት ማልማት ነው፡፡ ይህ መሆን የሚችለው ሰፊ መሬት ለሌላ አገልግሎት የማይውል ለንግድ የሚሆን እንጨት በዘመናዊ መልክ በመትከል ነው፡፡ እንደ ራሽያና ኤንዶንኤሽያ አገሮች በሰፊ መሬት ላይ ለፋብሪካ የሚሆን ከጥረ ዕቃ እንጨት ጣውላን በማምረት ለዓም ገበያ ያቀርባሉ፡፡

## ማዕድን ማውጣት

### ማዕድን ምንድነው?

1. የሚትኖርበት አካባቢ የሚገኙ ማዕድናት ምን ምን ናቸው?

ማዕድናት በመሬት ውስጥና በቅርፊተ መሬት ላይ የሚገኝ የተፈጥሮ ሀብትና ለሰው ልጅ የተለያዩ ጥቅም የሚሰጥ ነው፡፡

### ማዕድን ለማውጣት የሚወስኑ ሁኔታዎች

ሀ. **የማዕድኑ መጠን (Size):** የማዕድናት ብዛት በአንድ ቦታ ተከማችቶ ያለውን ለማውጣትና ለመጠቀም በቂ መሆን አለበት፡፡ እንደምታወቀው ማዕድን ለማውጣት ሀብትና ከፍተኛ የተማረ የሰው ሀይል ይፈልጋል፡፡ ስለዚህ የወጣው ማዕድን የወጣውን ወጭ ሸፍኖ የተፈለገውን ውጤት መስጤት ስለአለበት የተከማቸው የማዕድን መጠን በቂ መሆን አለበት፡፡

ለ. **የማዕድናቱ ጥራት (Grade):** ይህ የተመረተው ማዕድን ውጤት ወይም የተፈለገበት ጥቅም መስጠት ይመለከታል፡፡ ሁሉም ማዕድናት ጥቅምና የተለያዩ ዋጋ አላቸው፡፡ ግማሾቹ በብዙ ሰዎች ስለሚፈለግና በገበያ ላይም ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው አሉ፡፡ ለሎች ደግሞ በብዛት ይገኛሉ፣ ብመረትም በገበያ ላይ ተፈላጊነቱ ትንሽ ስለሆኔ ዋጋቸውም ዝቅተኛ ነው፡፡ ለምሳሌ: ወርቅና አሊሙንየም፡፡ ዋጋውና ተፈላግነታቸው የተለያዩ ነው፡፡

ሐ. **ማዕድን የሚገኝበት ጥልቀት:** ብዙ ጥቅም ያላቸው ማዕድናቶች በመሬት

ውስጥ በከፍተኛ ጥልቀት ላይ ተቀብረው ይገኛል፡፡ ወርቅ፣ ድያመንድ፣ ፐትሮለየም ከቅርፊተ መሬት ላይ በብዙ ሜትር ጥልቀት ይገኛሉ፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ የሚገኝበትን ቦታ ቆፍሮ ለማውጣት ዕውቀት፣ ተክኖሎጅና ከፍተኛ ወጭ ይፈልጋል፡፡ የተወሰኑ ደግሞ ቅርብ በመሬት ላይና በመሬት ገፅታ ላይ ይገኛል፡፡ ለምሳሌ፤ ከሰል ድንጋይ፣ አሊሙንየምና ለሎች ብረት ነክ እንደዝያውም ለግንባታ የሚሆን የተለያዩ ድንጋዮች ናቸው፡፡

**መ. ገንዘብ (capital):** ማዕድን ለማውጣት በተለይ በከፍተኛ ጥልቀት ላይ የሚገኙትን ዘመናዊ ማሽኖችና ከፍተኛ ዕውቀት ይፈልጋል፡፡ እነኚህ ማሽኖች ለመግዛት ትልቅ ሀብት/ ገንዘብ ያስፈልጋል፡፡ የተማረ የሰው ሀይል በአገርቱ ውስጥ ከለሌ ከውጭ ለመስገባት ትልቅ ወጭ ይጠይቃል፡፡ ይህ ማዕድኖች ከወጡ በኃላም አጣርቶ ለጥቅም ለማዘጋጀት ማዕድናትን የሚያጣሩ ፋብርካዎች ለማቋቋም ገንዘብ (capital) ይፈልጋል፡፡

**ሠ. የተማረ የሰው ሀይል:** እንደምታወቀው ማዕድን ማውጣት የአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ይመደባል፡፡ ይሁን እንጂ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እንደ አደን፣ ግብርናና ዓሣ ማጥመድ ልምድ ያካበቱ ሰዎች ሙሉ በሙሉ የሚሰማሩበት አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአንድ አካባቢ ማዕድን መኖር፣ የማዕድኑ አይነት፣ ወቶ ውጤት መስጠት፣ሞከራን በበቴ ሞከራ ማካሄድ፣ በተለያዩ ደረጃ ማጣራትና ይህን የሚመስሉ ሥራዎችን ለመካሄድ በቅ የተማረ ሰው መኖር ወሳኝ ነው፡፡ ኢትዮጵያን ጨምሮ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ይህንን ሀብት እያሉ መጠቀም ያልቻሉት አንዱ ምክንያት የተማረ የሰው እጥረት መኖሩ ነው፡፡

በዓለም ላይ ያሉ አንድ አንድ አገሮች በማዕድን የታደሉና ከፍተኛ ገንዘብ በማግኘት በጣም ሀብታም የሆኑ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፤ እንደ ደቡብ አፍርካ፣ ኮንጎ፣ ሳውድ አራብያ አገሮች ናቸው፡፡ በአሁኑ ጊዜ ባደጉ አገሮችም ሆኔ በማደግ ላይ ያሉ ውስጥም ማዕድን በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ በማዕድን ሥራ ምክንያት አንድ አገር የሚታገኘው ጥቅም፤ ኢንቬስትመንት መስፋፋት፣የውጭ ንግድ መሻሻል፣ ብዙ የሥራ ዕድል መፈጠር፣ ከውጭ ምንዛሬ ላይ የሚገኘው ገብ መጨመርና የአገርቱ እድገት እየተሻሻለ መሄድ፡፡ በዚሁ መሰረት አገራችንም በአሁኑ ጊዜ ማዕድን በማውጣት የሚታገኘው ገብ ከፍተኛና ለወደፍትም እንደ ነዳጅ፣ ብረት ተንና  የመሳሰሉት ማድናቶች

አውጥቶ ለመጠቀም ከፍተኛ ዕድል ይሆናል፡፡

ማዕድን ማውጣት በኢኮኖሚ ውስጥ ያለው ጠቀሜታ

ዝቅተኛና መካከለኛ ገብ ያላቸው አገሮች ውሰጥ በኢኮኖሚ ውስጥ ማዕድን ያለው ድርሻ ከፍተኛ ነው፡፡ የማዕድናት ጥቅሞች;

- የውጭ አገር ኢንቬስትመንት መሳብ
- የንግድ ዕቃን ከውጭ ማስገባት ይሆናል
- አገራዊ ገብን ያሳድጋል
- የሥራ ዕድል ያስፋፋል

የማዕድን ማውጣት ዘዴዎች

ማዕድናቶች በቅርፍተ መሬትና በመሬት ውስጥ ተቀብረው ይገኛል፡፡ የአወጣጣቸው ሁኔታም በሚገኙበት ቦታ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ ማዕድናት የማውጣት ዘዴዎች ውስጥ:

1. ከመሬት ገፅታ/ቅርፍተ መሬት ማዕድን ማውጣት: ለመሬት ገፅታ ቀርቦ የሚገኙ ማዕድናቶች በአፈርና አለቶች የተሸፈነውን በመንሳት ማዕድናቱን አውጥቶ ለተለያዩ ጥቅሞች ላይ ለማዋል ይቻላል ወይም ደግሞ አንድ አንደ ጊዜ ማዕድን በመሬት ላይ ተከማችቶ መገኘት ይችላል፡፡ እነኚህ ማዕድናቶች በመሬት ገፅ ላይ የሚገኙበት ምክንያት ቀላል በሆኔ መንገድ፣ ገንዘብና የተማረ የሰው ሀይል ትንሽ ለጥቅም መዋል መቻሉ፡፡ እንደዚያውም በትንሽ ወጭና በአጭር ጊዜ ውስጥ በማውጣት ሥራ ላይ ማዋል ይቻላል፡፡

የማዕድን ማውጣት ሥራ በመሬት ላይ/ በመሬት ገፅታ የሚካሄድ የሚከተለውን ጉዳት ማምጣት ይችላል፡፡ እነሱም፤

- አፈር ለጎርፍ መሸርሸር መጋለጥ
- የውሃና አፈር መበከል
- የዕፀዋቶች መጥፋት
- ሕይውት ያላቸው ነገሮች መጥፋት መቻል ናቸው፡፡

2. ማዕድናት ከመሬት ውስጥ ማውጣት: እነኚህ ማዕድናቶች በመሬት ውስጥ በጥለቀት ላይ ስለምገኙ ከፍተኛ የሆኔ ጥራት አላቸው፡፡ ይህ ሥራ ብዙ ጊዜ ወጭው ከፍተኛ ስለሆኔ በመሬት ውስጥ ያሉ ማዕድናቶች ከፍተኛ ክምችት ስኖረው ብቻ ሥራ ላይ ይዉላል፡፡ ምክንያቱም የማዕድን ክምችትና ጥራት ትንሽ

ከሆኔ የሚገኘው ውጤትም ትንሽ ይሆናል። ስለዚህ እንደዚህ ያሉ ማዕድናት ከፍተኛ ጥራት በመኖርና በዚህ ሥራ ላይ የወጣውን ወጭ እንድመልስ በጥንቃቄ መሰራት አለበት። ለምሳሌ፤ እነኚህ ማዕድናቶች፡ የነዳጅ ጋስ ክምችት፣ ድፍድፍ ዜይትና ወርቅ እደዚያውም የተለያዩ ብረት ነክ ( ብር፣መዳብ፣ዘንክ፣ኒኬል፣ ናቸው)።

3. **ከዳር(ጫፍ) ላይ የሚወጡ ማዕድናቶች**: እነኚህ ማዕድናቶች የሚገኙት መሬት ተቆርጦ የተሸራተተበት ቦታ ወደ ታች ወርዶ ወይም መሬት በወንዞች ወደ ታች የቆፈረበት ቦታ የተፈጠረው ጫፍ ላይ ይወጣል። የመረጋገጫ ጥያቄ

1. የአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
2. ከአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ አይነቶች ውስጥ ብዙ ሰው የሚሰራው የቱ ነው?
3. በአገሪቱ ኢኮኖሚ ውስጥ ግብርና ያሌውን ድርሻ ግለፅ/ጭ
4. ባደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ግብርና በምን ልዩነት አለው?
5. ደን ሥራ፣ ዓሣ ማጥመድና ማዕድን ማውጣት በአካባቢያችሁ ውስጥ በሚን ደረጃ ላይ እንዳሉ በቡድን በመወያየት ለክፍላችሁ አብራሩ።

## 2.2.2. የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ

1. ፋብሪካ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የፋብሪካ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
3. በሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የሚገኙ ሥራዎች ምን ምን ናቸው?

የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት መጠገን፣ መስራት፣ ማምረትና የመቀየር ሥራዎችን በውስጡ የያዜ ነው። በአጠቃላይ ጥሬ ዕቃዎችን ሰው መጠቀም በሚችል መልክ መቀየር መቻል ማለት ነው።

**ፋብሪካ** ጥሬ ዕቃውን ሰው መጠቀም በሚችልበት መልክ የሚቀይር ነው። እንደ መዘጋጀት፣ መሥራትና የመቀየር ሥራዎችን በውስጡ የያዜ ነው። ለምሳሌ፤ ብረትን ወደ ማሽን ወይም ወደ ፋብሪካ መቀየር ጥጥን ወደ ተለያዩ ልብስ መቀየር፣ ስንደን ወደ ዱቀት፣ ፓስታና መከረን መቀየር በውስጡ ያቅፋል።

### የፋብሪካ መገኛን የሚወስኑ ነገሮች:

ፈብሪካ እንድመሰረት ወይም በአንድ ቦታ እንድቋቋም የሚያደርጉ ብዙ ነገሮች

አሉ፡፡ እነሱም፤ ጥሬ ዕቃ፣ ለማብራት ሀይል ቅረብ መሆን፣የውሃ አቅርቦትና ተስማሚ መሬት፣ ለመጓጓዣ ተስማም የሆኔ፣ መልካም አስተዳደር፣ ገንዘብ (capital)፣ የተማረ የሰው ሀይል፣ ለገበያ ቅርብ መሆን ናቸው፡፡

### የፋብሪካዎች አይነት

ፋብሪካ ማለት ጥሬ ዕቃ የሚቀየርበትና አላቂ ዕቃዎችም የሚመረቱበት ቦታና ነው፡፡ በፋብሪካ ውስጥ ጥሬ ዕቃዎች በመልክ ይቀየራሉ፣ ጥራቱም ይሻሻላሉ እንደዛውም የሚሰጡት ጥቅም ይጨምራል፡፡ ፋብሪካ በእድገት ደረጃቸው ላይ ተመስርተው በሁለት ይካፈላሉ፡፡

i. የጎጆ እንዱስትሪ: በመኖርያ ቤት አካባቢ ትንሽ በሰው ሀይል የሚካሄድ ነው፡፡ ይህ በቤት የሚመረት ዕቃዎች ሰዎች በግል ሙያቸው የሚያመረቱና የሚከተለውን ዕጅ ሥራዎች በውስጡ ያቀፈ ነው፡፡ እነሱም፤ ቆዳ መፋቅ፣ ሽመና፣ እንጨት ሥራ፣ ቀጥቃጭና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

እነኚህ የፋብሪካ ምርቶች ብዛት፣ ጥራትና ዝቅተኛ ዋጋ አላቸው፡፡ በጎጆ እንዱስተሪ ውስጥ ዘመናዊ ተክኖሎጅ ሥራ ላይ አይውሉም፡፡

ii. ዘመናዊ እንዱስትሪ : ዘመናዊ እንዱስትሪ ከፍተኛ ገንዘብ፣ ዘመናዊ ተክኖሎጅ፣ ከፍተኛ የኤሌትርክ ሀይል፣ ከፍተኛ የተማረ የሰው ሀይልና ጥሬ ዕቃን በብዛት መጠቀም ነው፡፡ እነኚህ የፋብሪካ ምርቶች ከፍተኛ ጥራትና ከፍተኛ ዋጋ ያላቸው ነው፡፡





ሥዕል 2.1 ዘመናዊ ፋብሪካዎች

የፋብሪካዎች ስረጭት በኢትዮጵያ: የኢትዮጵያ ፋብሪካዎች:-

ሀ.) በተወሰነ ቦታ ብቻ የሚገኝ ነው፡፡

ለ.) በትልልቅ ከተሞች አካባቢ ብቻ የተቋቋመ ነው፡፡

ይሁን እንጂ በአሁኑ ጊዜ ወደ ክልሎችና ዞኖች እየተስፋፉ ነው፡፡ ለምሳሌ ትልልቅ ፋብሪካዎች “industrial zone” በመባል በዞኖች ውስጥ እየተስፋፉ ነው፡፡

**የማረጋገጫ ጥያቄዎች**

1. የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የፋብሪካ አይነቶች ምን ምን ናቸው?
3. የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባህርዎች ዘርዝር/ሪ፡፡
4. የፋብሪካዎች መገኛ የሚወስኑ ነገሮችን ፃፍ/ፊ፡፡

## 2.2.3 . የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች

የግምገማ ጥያቄዎች

- የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት ምን ማለት ነው?
- ንግድን የሚወስኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?
- በአካባቢህ/ሽ ያለው የመጓጓዣና የንግድ ሁኔታ እንደት ያሉ ናቸው?
- የሚትኖርበት አካባቢ ውስጥ ሕዝብ በምን መንገድ መረጃ ያገኛሉ?
- በሚትኖርበት አካባቢ የቱሪዚም ዕድል ምን ምን ናቸው?

የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ማለት የተለያዩ አገልጊሎት የሚሰጡ ሥራዎችን በውስጡ ያቅፋል፡፡ እኤርሱም እንደ ንግድ፣ መጓጓዣ፣ ኢንሹራንስ፣ ባንክ፣ ቱሪዝም፣ የመገናኛ ዘዴዎች (communication)፣ የሆተል አገልግሎትና የመሳሴሉት ነው፡፡

**መጓጓዣ**

የግምገማ ጥያቄዎች

1. የሚትኖርበት አካባቢ ብዙ ሰዎች የሚጠቀሙበት ከመጓጓዣ አይነቶች ውስጥ የቱ ነው?
2. ከመጓጓዣ ውስጥ ውድ ዕቃና ቀላል ክብደት ያለውን የሚጭን የቱ ነው?

መጓጓዣ ማለት የዕቃዎች እንቅስቃሴ ወይም ሰዎችን ከአንድ ቦታ ወደ ለላ ቦታ የሚደረግ ነው፡፡ የኢንዱስትሪ እድገትና ንግድ በመጓጓዣ ላይ ይመሰረታል፡፡ ከመጓጓዣ ውጭ የኢንዱስትሪ ልማት፣ ጤናና ትምህርት አይታሰብም፡፡ መጓጓዣ የአገርቱ ኢኮኖሚ ደም ሥር ነው፡፡ የአንድ አገር እድገት ደረጃ

ከሚንመዝንበት ውስጥ አንዱ የመጓጓዣ ተክኖሎጅ እድገት ነው።

## የመጓጓዣ አይነቶች

በአጠቃላይ መጓጓዣ በሁለት ቦታ ይካፈላል። እነርሱም፡

1. ባህላዊ መጓጓዣ: በሰውና በእንስሳት ከአንድ ቦታ ወደ ለላ ቦታ ዕቃዎችን የሚጓጓዝ የመጓጓዣ አይነት ነው። ይህ መጓጓዣ በአሁኑ ጊዜ በአገራችን ውስጥ ሰፊ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል። የአገራች ሰፊ የገጠር ህብረተሰብ በዝህ አይነት መጓጓዣ በሰፊነት እየተጠቀመ ይገኛል።
2. ዘመናዊ መጓጓዣ: ዘመናዊ መጓጓዣ ደግሞ በሦስት ቦታ ይካፈላሉ። እነርሱም፡
   - ሀ. የምድር መጓጓዣ
   - ለ. የውሃ መጓጓዣ
   - ሐ. የአየር መጓጓዣ

### ሀ. የምድር መጓጓዣ:

**i. የመኪና መጓጓዣ:** ከለሎች ዘመናዊ መጓጓዣ ጋር ስናወዳድር በብዙ ቦታ የሚገኝ ነው። ተስማሚ በሆነበት ቦታ ሁሉ ከዘመናዊ መጓጓዣ አይነቶች በላይ ለመስራት (ለመገንባት) ቀላል ነው። የሚገዛበት ዋጋ ከባቡርና መርከብ በጣም ቀላል ነው።



ሥዕል 2.2 የመኪና መጓጓዣ

ii.የባቡር መጓጓዣ: የባቡር መጓጓዣ በአገራችን ውስጥ በብዛት አልተስፋፋም፡ ፡ በአሁኑ ጊዜ የባቡር መንገድ ከጂቡት መስመር ውጭም በአድስ አበባ ውስጥ የከተማ አገልግሎት እየሰጠ ይገኛል፡፡

የባቡር መጓጓዣ መስፋፋት ላይ ጫና (ግፊት) የሚፈጥሩ ነገሮች የመሬት አቀማመጥ፣ የኢኮኖሚ እድገትና የተክኖሎጅ መስፋፋት ናቸው፡፡



ሥዕል 2.3 የባቡር መጓጓዣ

## ለ. የውሃ መጓጓዣ

የውሃ መጓጓዣ በሁለት መንገድ ይካሄዳል፡፡ እነርሱም የአገር ውስጥ የውሃ መጓጓዣና በውቅያኖስ ላይ/ የዓለም ናቸው፡፡

የአገር ውስጥ የውሃ መጓጓዣ

የአገር ውስጥ የውሃ መጓጓዣ የሚከናወነው በወንዞችና በሐይቆች ላይ ነው፡፡ ለውሃ መጓጓዣ መንገድ ማስተካከል ወይም ለመጠገን ወጭ የለውም፡፡ ክብደት ያላቸው ዕቃዎችን በቀላል ዋጋ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመውሰድ (ለማድረስ) ያገለግላል፡፡

### የአገር ውስጥ የውሃ መጓጓዣ እንቅፋቶች

- ወንዞቹ ፋፋተና የምወረወር መሆኑ
- የውሃ ተፋሰስ አቅጣጫን ለመከተል መገደዱ
- የወንዝ ውሃ መጠን ወቅታዊ መሆን
- የውሃ መጓጓዣ ከምድር መጓጓዣ በላይ በዝግታ የሚሄድ ነው፡፡

የባህር መጓጓዣ: ለረጅም ጊዜ አገልግሎት ስሰጥ የቆዬ የመጓጓዣ አይነት

ነው፡፡ በቀላል ዋጋ ከባድና ግዙፍ ዕቃዎችን በመጫን ረጅም መንገድ በመሄዱ ተመራጭ ነው፡፡



ሥዕል 2.4 የባህር መጓጓዣ

## የባህር መጓጓዣ ጥቅም

- በባህር ላይ መንገድ ከግብር ነፃ ነው፣
- ለትራንስፖርት የመወጣው ወጭ ቀላል ነው፣
- የሚገነባ ወይም የሚጠገን መንገድ የለም፣
- ክብደት ያላቸው ዕቃዎችን ይጭናል፡፡

## የባህር መጓጓዣ ድክመቶች

- ፍጥነቱ አነስተኛ ነው
- ለመርከብ ወደብ ግንባታ የሚያስኑ ወጭ ውድ ነው
- የባህር ዕድል ያላቸው አገሮች ብቻ ይጠቀማሉ
- የባህር ላይ ወንበደ ሊጋለጥ ይችላል

## ሐ. የአየር መጓጓዣ

እንደ ኢትዮጵያ የመንገድ ግንባታ ችግር በሆኔበት አገር ውስጥ የአየር ትራንስፖርት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

## የአየር  መጓጓዣ ጥቅም

- በከፍተኛ ፍጥነት ረጅም መንገድ ይሄዳል፣
- ትልቅ ዋጋ ያላቸው፣ ቀላልና ቶሎ የሚበላሽ ዕቃዎች ለመጓጓዝ ይጠቅማል፡፡ ለምሳሌ የህክምና ዕቃዎችና መድሃንት፣ የኤሌትሮኒክስ ዕቃዎች፣ ምግብና መጠጥና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ሥዕል 2.5 የአየር መጓጓዣ

## መገናኛ

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. የመገናኛ መንገዶች/ መረጃ የሚተላለፍበት መንገዶች ምን ምን ናቸው?
2. ለመገናኛ የሚያገለግሉ ዕቃዎችን ዘርዝር/ሪ?

መገናኛ የመረጃ ስርጨት (ሀሳብ) በድምፅና በመልእክት የሚሰራጭ ስሆን የሰዎች እንቅስቃሴ ስርዓቶችና የዕቃዎች ከቦታ ቦታ የሚደረግ ውስጥ ከፍተኛ ጥቅም አለው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የዘመናዊ መገናኛ ዕቃዎች በከፍተኛ ፍጥነት መልእክትና መረጃን ለዓለም በሙሉ ለመዳረስ የቻለበት ምክንያት የኢንተርነት አገልግሎት መሻሻል ነው፡፡ በዓለም ሩቅ አገሮች ያላቸው ሰዎች በቀላልና በፈጣኝ ሁኔታ እድገናኙ ያደርጋል፡፡

ከዚህ በፍት ህብረተሰብ ለመገናኛ የሚውሉ የባህላዊ ዕቃዎች አንደ፤ ከበሮ፣ ጭስና ደምፅን በመጠቀም መልእክት በማስተላለፍ ቆይተዋል፡፡ በአሁኑ ጊዜ ደግሞ በዘመናዊ ዕቃ እንደ ስልክ፣ ሬድዮ፣ ቴሌቪይን፣ ኢሜል፣ ፋክስ፣ተለቴሌጊራም፣ እና ወዘተ በመጠቀም የተፈለገውን መልእክትና መረጃ ማሳለፍና መውሰድ ወይም መመልከትና ማዳመጥ ይቻላል፡፡

### ሀ. ቱሪዚም

1. ቱሪዚም ምንድነው?
2. የአገር ኢኮኖሚ በማሳደግ ውስጥ ቱሪዚም ያለው ድርሻ ምንድነው?

ቱሪዚም የሰዎች ድርግት ከመኖርያ ቦታ ውጭ ለመዝናኛ፣ ለጉበኚት፣ ለምርምር የሚከድ ነው፡፡ ቱሪዚም በኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ከፍተኛ ገቢ ከሚያስገኙት


ውስጥ አንድ ስሆን ድርግቱም አካባቢን ስለማይ ጎዳ ጭስ አልባ ፋብሪካ በመባል ይታወቃል።

ኢትዮጵያ ከፍተኛ የቱሪዚም ዕድል ብኖራትም በተለያዬ ምክንያቶች መጠቀም ያለባት መጤን አልተጠቀመችም ማለት ይቻላል። የቱሪዚም ቦታዎች የውጭ አገር ሰዎችና በአገር ውስጥ በተለያየ ጊዜ በመንቀሳቀስ ለመዚናኛ የሚጠቅም በኢትዮጵይ ውስጥ እንደ ሶፍ ኡመር ዋሻ፣ ጆጎል ግንብ፣ የሸክ ኡሰን ቦታ፣ ላሊበላ፣ አክሱም፣ በስምጥ ሸለቆ አካባቢ፣ የሰሜን ተራሮችን መጥቀስ ይቻላል።

የቱሪዚም ጥቅሞች

ቱሪዚም ብዙ ጥቅሞች አለው። ከእነዚህ ውስጥ ጥቅቶቹ:

- የሥራ ዕድል ይፈጥራል
- ለመዝናኛ
- የአገሪቱ ገቢ ለማሳደግ
- ለሌሎች ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ድጋፍ ይሰጣል
- ታርካዊ ቦታዎችን ለማሳወቅ
- የአገሮችን ግንኙነት ለመጠናከር ይጠቅማል







ሥዕል 2.6 በኢትዮጵያ የቱሪዚም መስብ ቦታዎች

### የመረጋገጫ ጥያቄዎች

1. በቡድን ሆናችሁ የተለያዩ የመጓጓዣ አይነቶች ከዘረዘራችሁ በኃላ ያላቸው ጥቅምና ጉዳት ላይ በመወያየት ርፖርት አቅርቡ፡፡
2. የአገራችን መጓጓዣ እድገት ላይ እንቅፋት የሆኑ ነገሮች ምን ምን ናቸው?

## 2.2.4.የተለያዩ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎች ለአገር እድገት ያላቸው ጥቅም

ያደጉና በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ኢኮኖሚያቸው በምን ላይ የተመሰረተ ነው መሰረት?

የዓለም ሕዝብ በሙሉ የአካባቢያቸውን ተጨባጭ ሁኔታ፣ የቴክኖሎጂ እድገት፣ የሥራ ባህል፣ ባላቸው ልምድ መሰረት በማድረግ ስለምሰሩና የሚያገኙት ገቢ የራሳቸው ኢኮኖሚ አላቸው። ስለዚህ ሁሉም የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በአገር እድገት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ባደጉ አገሮችም ሆኔ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ሦስቱ የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይካሄዳል። ይሁን እንጂ በዚህ ኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ የሚሰማሩ የሕዝብ ብዛት ከአገር አገር ይለያያል። ባደጉ አገሮች ብዙ ሕዝብ የሁለተኛ ደረጃና ሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ የተሰማሩ ስሆኑ በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ደግሞ በብዛት በአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ላይ ተሰማርተው ይገኛሉ። በተለይ ኢንዱስትሪ ባልተስፋፋበት አገሮች እንደ አፍርካ፣ ደቡብ አሜርካና ኤሽያ ውስጥ ለግል ገቢም ሆኔ ለአገሪቱም በጣም ወሳኝ የሆኔ ነው።

በአጠቃላይ የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባደጉ አገሮች ከፍተኛ ገቢ ሊያስገኙ ኑሮ ወይም የብዙ ሰው ሥራ ጋርም የሚያያዝ ነው። በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ደግሞ የሚገኝ ገቢ ዝቅተኛና በተወሰኔ የሰዎች ኑሮ ላይ የተመሰረተ ነው።

## ገበያ

ገበያ ማለት ምርቶች የሚሸጥበትና የሚገዛበት ቦታ ነው። ገበያ ማለት አስራር ወይም የገዥና ሻጭ ሂደት በመገናኘት የኢኮኖሚ መቀያየር ማድረግ ነው። ይህ ገበያ በአካል በመገናኘት መግዛትና መሸጥ ወይም በተዘዋዋሪ ልሆን ይችላል፡ ፡ ገበያ የዕቃዎች ዋጋ ሁኔታና ለገበያ የመቀርቡ የዕቃዎች ብዛት ይወስናል። በአሁኑ ጊዜ እንደ ዓልም ታዋቅ የሆኔ ገበያ ነፃ ገበያ ነው።

### 2.2.5 የንግደና ገበያ አመጣጥ ፅንሰ ሃሳብና ታርክ

#### ንግድ

i. ንግድ ማለት ምን ማለት ነው?
ii. ንግድ እንደት ተጀመረ?
iii. የንግድ አይነቶች ምን ምን ናቸው?

ንግድ ማለት የዕቃ ገዥና ሻጭ በሰዎች፣ በድርጅቶች ወይም በአገሮች መካከል የሚደረግ ነው፡፡ በለላ በኩል ደግሞ ንግድ የምርት ሂደት፣ ከአምራቾች ላይ ወደ ተጠቃሚዎች ጋ የሚደርስ ነው፡፡

ንግድ ለመጀመርያ ጊዜ ዕቃን በዕቃ በመለዋወጥ ነው የተጀመረው፡፡ ለምሳሌ ጨውን በብረት መለወጥ፣ አንድ አይነት ምርት ከለላ ጋር መቀየር፡፡

ለንግድ መጀመር ምክንያት የሆኑ ነገሮች፡-

- የምርት ልዩነት መኖር
- የቴክኖሎጂና ባህል ልዩነት መኖር
- ጅኦግራፍካል መገኛ (geographical location)
- ምቹ መጓጓዣ መኖርና
- ፀጥታ መኖር ናቸው፡፡

የዱሮ ሰዎች በአካባቢያቸው የሚገኙ የተለያዩ ዕቃዎች እየተጠቀሙ ኖረዋል፡፡ በዚህ ዓለም ላይ በሁሉም ምርት እራሱን የቻለ ሕዝበ የለም፡፡ ምክንያቱም በየትኛውም ቦታ ላይ ተመሳሳይ የተፈጥሮ ሀብት ተሰራጭቶ አይገኝም፡፡

በዱሮ ጊዜ ንግድ የተጀመረበት ሁኔታ ዕቃን በመለዋወጥ ነው፡፡ ለምሳሌ በድንጋይ ዘመን ውስጥ ስኖሩ የነበሩ ሕዝቦች ከድንጋይ የተሰራ የጦር መሣርያዎች በመለዋወጥ ይጠቀሙበት ነበር፡፡

የጥንታዊ ስልጣኔ ሕብረተሰብ እንደ ግብፅና በእንደስ ሸለቆ ውስጥ የሥራ ክፍፍል ተጀምረዋል፡፡ ቀስ በቀስ የሸክላ ሥራ፣ የብረታ ብረት ሥራና የእንጨት ሥራ ተጀምረዋል፡፡ በዚህ ሁኔታ የምግብ እህሎች ማምርት አጠገብ ነገሮች መስራት ማደግ ጀመሬ፡፡ በዚሁ ሁኔታ ህብረተሰቡ የሚበላ ነገር በለሎች ዕቃዎች መቀይር ጀምረዋል፡፡ ይህ የመጀመርያ ህብረተሰብ በባህልና ስልጣኔ እየተሸሻለ ስሄድ ፍላጎታቸውም ብዛትና ጥራት ጨምረዋል፡፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ ህብረተሰቡ ረጅም ርቀት እንድሄዱ አስገድደዋል፡፡ የሥራ ክፍፍል መወለድ፣ የባህል መሻሻልና የህብረተሰብ ኑሮ መጀመር ለንግደ መሰረት(base) ሆኖዋል፡፡

## የንግድ ጥቅሞች

ንግድ ለሰው ልጅ ኑሮና ለአንድ አገር ኢኮኖሚ እድገት በጣም አስፈላግ ነው፡፡ ንግድ ውድድርን በማጠናከር የዕቃዎችን ዋጋ ወደ ታች በመቀነስ ተጠቃሚዎቹ

ዕቃዎችን በአቅማቸው ገዝቶ ትርፍ እንድያገኙ ያደርጋል። ንግድ የዕቃዎች እጥረት በአንድ ቦታ ላይ የተፈጠሩትን መፍታት ይችላል። በአጠቃላይ ንግድ የሚከተሉትን ጥቅሞች አለው፡

- የሚፈለገውን ነገር ከገበያ ላይ ለመግዛትና ለመሸጥ
- ምርቶች በተለያዩ ቦታ እንድሰራጭ
- ምርቶች በተጨማገር እንድመረት ያደርጋል
- የገንዘብ እንቅስቃሴ በቀላል መንገድ እንድቀሳቀስ
- የቀሩት ምርቶች ከሰው ላይ እነድሸጥ
- ሰርቶ ለመወዳደር
- ለተለያዬ ሰዎች የሥራ ዕድል መፍጠር
- ለአገሪቱ ገቢ ለማስገባት ይጠቅማል
- ለለሎች ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ እድገት ድጋፍ ይሰጣል
- የአገሮችን ግንኙነት ያጠነክራል
- የአንድ አገር ኢኮኖሚ እድግት ምሰሶ ነው
- ሰው የፈለገውን ዕቃ በፈለገው ዋጋ እንድገዛ ያደርጋል

## የንግድ አይነቶች

ንግድ በሁለት ዋና ዋና ቦታ ይካፈላል። አነርሱም፤ የአገር ውስጥ ንግድና የውጭ አገር ንግድ ናቸው።

ሀ. የአገር ውስጥ ንግድ— የምርት ገዥና ሻጭ በአገሪቱ ሙሉ ህብረተሰብ ውሰጥ የሚከናወን ነው። ይህ ማለት እንደዚህ አይነት ንግድ ከተማና ገጠር፣ ከተማና ከተማ፣ ገጠርና ገጠር መካከል ይካሄዳል።

ለ. የውጭ አገር ንግድ: ከሁለትና ከዚያ በላይ አገሮች መካከል የሚካሄድ የንግድ አይነት ነው። ይህም በአገሮች መካከል የሚፈፀም (የሚከናወን) ስምምነት ነው። ይህ ንግድ ዕቃን ከአገር ውሰጥ ወደ ውጭ መላክና የውጭውን ደግሞ ወደ ውስጥ ማስገባት ነው።

አቅርቦትና ፍላጎት በገበያ ላይ የሚያደርሰው ጫና (ግፊት)

- በገበያ ስረአት ውስጥ ፊላጎት ማለት ምን ማለት ነው?
- አቅርቦት ማለትስ ምን ማለት ነው?

- **የፍላጎትና አቅርቦት ግንኙነት ምንድነው?**

ባለፈው ትምህርት ውስጥ ስለ ገበያ መማራች ይታወሳል፡፡ ገበያ የመግዣና መሸጫ ቦታ ነው፡፡ ህዝብ በቦታው ተገናኝተው ዕቃ ወይም አገልግሎት የሚለዋወጡበት ነው፡፡


አቅርቦታ ማለት ዕቃዎች ወይም ለአግልጊሎት የሚፈለግ በጥራት ለተጠቃሚዎች ማዘጋጀት ነው፡፡ አቅርቦት ብዛት ያላቸው ዕቃዎች በተለያዬ ዋጋ አምራቾች ለገበያ ማቅረብ የሚፈልጉት ነው፡፡

ፍላጎት ማለት ዕቃዎች ወይም አግልጊሎት ሰዎች በግል ወይም በቡድን ለመጠቀም የሚፈልጉት ነው፡፡ ይህ ፍላጎት ግብ ለመድረስ የሚከተሉት ነገሮች ላይ ይመሰረታል፡፡

- የዕቃ መግዛት ችሎታ
- ዕቃ ለመግዛት ፍላጎት መኖር

**የአቅርቦት ደንብ (ህግ)**


የዕቃ ዋጋ ከጨመረ የሚመረት ምርትና ለሻጭ የሚቀርብ ይጨምራል፡፡ እንደዚያውም ዋጋው ከቀነሴ የዕቃው አቅርቦት እየቀነሴ ይሄዳል፡፡




ሥዕል 2.7 የአቅርቦት ግራፍ


**አቅርቦትን የሚወስኑ ነገሮች**

- የደንበኞች ብዛት
- የምርት ዋጋ
- የደንበኞች ፍላጎት
- የምርት ጥራት




ሥዕል 2.8 የፍላጎት ግራፍ

ግራፉ ላይ እንደምታየው “Y” ቀስት የዕቃዎች ዋጋን የሚተካ ስሆን ቀስት ’X” ደግሞ የሚፈለገው የዕቃዎች ብዛትን ያመለክታል፡፡ ታጣፊ ፍላጎት መስመር የሚያሳየው የዋጋና የዕቃዎች ተፈላግ ብዛት ተቃራን ግንኙነት ነው፡፡
ፍላጎት ከተቃራን ዋጋ ጋር ግንኙነት አለው፡፡ ይህ ማለት የዕቃ ዋጋ ከጨመረ የደንበኛ ዕቃ መግዘት ፊላጎት ይቀንሳል፡፡




ሥዕል 2.9 የዕቃ ፍላጎት የሚወስኑ ነገሮች

በአቅርቦት ላይ ጫና (ግፊት) የሚፈጥሩ ነገሮች ብዙ ስሆኑ፤ ከእነዚህ ውስጥ ጥቅቶቹ፡-

- ለምርት የሚፈለገው የጥሬ ዕቃ ዋጋ
- የአምራቾች እውቀትና ችሎታ
- የአምራቾች ብዛት
- ቴክኖሎጂ
- የአቅም በላይ ግብርና የመንግስት ጫና (ግፊት)

## የገበያ ውድድር ፅንሰ ሀሳብ

**የነፃ ገበያ ውድድር:** የምርት ዋጋ የሚወሰነው የአቅራብዎችና የተጠቃምዎች ስምምነት ነው፡፡ ይህ ማለት የምርት ወጋ በለላ አካል የሚወሰን አይደለም፡ ፡ በዚህ ውስጥ የገበያ ዋጋ በግል የሚወስን የለም፡፡ በዚህ ገበያ አይነት ውሰጥ ዋጋ የሚወሰነው የፍላጎት ግፊት ሁኔታና በአቅርቦት ነው፡፡
የተጠቃሚዎች መብት

የተጠቃሚዎች መብት መከበር: በዚህ መብት መሰረት ተጠቃሚ ወይም አንድ ደንበኛ የዕቃዎችና የሚያገኘው የአገልግሎት መብት ከሚደርሰው አደጋ ላይ ነፃ መሆን ማለት ነው፡፡

ለምሳሌ በዕቃዎች ጥራት ማጣት ምክንያት የተነሳ በተጠቃሚዎች ላይ አደጋ ሊደርስ ይችላል፡፡ ይህ የሰላም መብት ወይም ይህ ደንበኛ የገዛ ዕቃዎች ከአደጋ ነፃ መሆን ወይም ከላይ ያለው አግልጊሎት ማለት ነው፡፡

የመረጃ ማግኘት መብት: ይህ የመረጃ መብት ስለ ዋጋ፣ ጥራት፣ ብዛት፣ የሚገኝበት ቦታ፣ የዕቃዎች ደረጃ ወይም አንድ ደንበኛ ማግኘት ያለበት አግልጊሎት የሚገልፅ ነው፡፡

## የመንግስት ገብርና ገቢ

### የግብርና ገቢ ምንነት

ገቢ; ገቢ ማለት መንግስት ከተለያዩ አግልጊሎት ላይ የሚያገኘው ገንዘብ ማለት ነው፡፡ ለመንግስት ገቢ ምንጭ የሆኑት ንግድ፣ ግብር፤ የቤት፣ የመሬት፣ የሰራተኞች ደመወዝና ከተለያዩ ተቋማት ላይ የምገኙ ናቸው፡፡

ግብር; ግበር ማለት በአንድ አገር ውስጥ የግደታ መዋጮ በመንግስት የሚታወጅ ሆኖ በአገሪቱ ውስጥ የሚኖሩ ዘጎች ከሚያገኙት ገቢ ላይ ለመንግሰት የሚከፍሉት ነው፡፡ ይህ መዋጮ ተመልሶ የመንግስት ወጭና ለተለያዩ መሰረታዊ የአግልጊሎት ግንባታ ይውላል፡፡ ግብር ግለሰብም ሆነ ማህበር ወይም በስርአት

የሚሰሩ ድርጅቶች በሙሉ የሚከፍሉት ነው፡፡ ግብር የመንግስት ገቢ ምንጭና የአንድ አገር ኢኮኖሚ እድገት መሰረት ነው፡፡

የኢትዮጵያ መንግስት ገቢና ግብር የእድገት ታርክ

በኢትዮጵያ ውስጥ ግበር የተጀመረው በዘመናዊ ታርክ ውሰጥ በሚኒልክ መንግስት ጊዜ ነው፡፡ በዚያን ጊዜ ስገበር የነበረው ግብር በህግ የታወጄና በሙያ የተቀናጀ አልነበረም፡፡ ዘመናዊ የግብር አሰባሰብ በፕሮግራም ወይም በቋም ጊዜና ተጠያቅነት ባለው በሰለጤነ አካል የተጀመረው በ1928 ዓ.ም. በኃይለ ስላሴ መንግስት ዜመን ነው፡፡

በ1929 ዓ.ም. የግብር ኮድ ( code) ያለው አዋጅ ሁሉም ዜጎች ከሚሰሩት ሥራ ከሚያገኙት ገቢ ላይ ግብር እንድገብሩ ታወጀ፡፡ በደርግ መንግስት ጊዜ በ 1967 ዓ.ም. የግብር አዋጅና መዋቅር በመሻሻል ከግብርና መሬት እዞታ ላይ ግብር እንድገበር ተወሴነ፡፡ በ1986 ዓ.ም.የኢትዮጵያ ፊዴራላዊ ዲሞክራሳዊ መንግስት የግብር አዋጅ አሻሽሎ በማውጣቱ እስከ አሁን ድረስ እያገለገለ

## የግብር ጥቅሞች

- የአገር ገቢ ለማሳደገ
- ኢኮኖሚ እድገትን ለማፋጠን
- ኢንቬስትመንትን ለማበረታታት
- መሰረተ-ልማቶችን ለማስፋፋት
- የአገር ውስጥ ኢንዱስትሪን ለማበረታታት ናቸው፡፡

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

- የዓለም ሕዝብ በሙሉ ባህልና የራሳቸውን መለያ አላቸው፡፡ ባህል የአንድን በሔረሰብ ማንነት የምገለፅ ነው፡፡
- በባህል ውስጥ የሚታቀፉ መግለጫዎች፤ ቋንቋ፣ ሀይማኖትና የህብረተሰብ አኗኗር ሁኔታ ናቸው፡፡
- የድንጋይ ስልጣኔ ዘመን የሚባለው የሰው ልጅ ለኑሮው የሚያስፈልገው ከድንጋይ ላይ ሰርተው ይጠቀምበት የነበረ ጊዜ ማለት ነው፡፡ ይህ ዘመናት በሦስት ዋና ዋና ቦታ ይካፈላል፡፡ እነርሱም፤ የጥንታዊ ድንጋይ ዘመን፣ የመካከለኛ ድንጋይ ዘመንና ዘመናዊ የድንጋይ ዘመን ናቸው፡፡
- ግሎባላይዘሽን ማለት ሰው ልጅ ያለው የአጠቃላይ አውታር (network) ማለት ነው፡፡ እሱም የዓለም የአንድነት ሀሳብ የሚለውን ነገሮች በውስጡ ይዘዋል፡፡
- የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ በሦስት ቦታ ይካፈላል፡፡ አነርሱም፤ የ1ኛ፣ የ2ተኛና የ3ተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ናቸው፡፡
- በአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የተመደቡ ሥራዎች፤ እርሻ፣ ዓሣ ማጥመድ፣የማዕድን ሥራ፣ ድን ማልማት፣ አደንና የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ሥራዎች እንደ መጠገን፣ መስራት፣ ማምረትና የመቀየር ሥራዎችን በውስጡ የያዜ ነው፡፡ ጥሬ ዕቃዎችን ሰው መጠቀም በሚችል መልክ መቀየር መቻል ማለት ነው፡፡
- የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የተለያዩ አገልጊሎት የሚሰጡ ሥራዎችን በውስጡ ያቅፋል፡፡ እኤርሱም እንደ ንግድ፣ መጓጓዣ፣ ኢንሹራንስ፣ ባንክ፣ ቱሪዝም፣ የመገናኛ ዘዴዎች፣ የሆተል አገልግሎትና የመሳሴሉት ናቸው፡፡
- የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ባደጉት አገሮች ከፍተኛ ገቢ የሚያስገኝ ስሆን በማደግ ላይ ባሉ አገሮች ደግሞ ገቢ የሚያስገባ የአንደኛና የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው፡፡
- መንግስት ከተለያዩ አገልግሎት ላይ የሚያገኘው ገንዘብ ገቢ ይባላል፡፡
- ግብር በአንድ አገር ውስጥ በመንግስት በግዳጅ መልክ የሚታወጂ መዋጮ ስሆን በአገሪቱ ውሰጥ ከሚኖሩ ዜጎች ከሚያገኙት ገቢ ላይ የሚከፍሉት ነው፡፡

የምዕራፍ ሁለት መልመጃ

I. ከዚህ በታች ያሉት ዐ.ነገሮች ትክክል ከሆኑ "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሀሰት" በማለት መልስ/ሺ

1. የቴክኖሎጂ ለውጥ አድስ ባህል ለመስፋፋት ወይም ለመቀየር ውስጥ ትልቅ ድርሻ አለው፡፡
2. የሰው ልጅ ባህሉን መግለፅ ወይም መለማመድ የጀመረው ባለፉት በሦስቱ ድንጋይ ዘመናት ውስጥ ነው፡፡
3. ያለን ባህል፣ ቋንቋና ሀይማኖት አብሮ በመኖራችን ላይ ጫና የለውም፡፡
4. በማደግ ላይ ያሉ አገሮች ህዝብ ይበልጥ በአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ይኖራሉ (ይተዳደራሉ)፡፡
5. ማዕድን አውጥቶ ለፋብሪካ ለማቅረብ በአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ ይመደባል፡፡
6. እራሻ ለመጀመርያ ጊዜ በደቡብ ምስራቅ ኤሽያ አገሮች ተጀመረ፡፡
7. የመኪና ፋብሪካ በጎጆ ኢንዱስትሪ አይነት ውስጥ ይመደባል፡፡
8. ከምድራዊ መጓጓዣ ውስጥ ክብደት ያለውን ነገር የሚጭን የባቡር መጓጓዣ ነው፡፡
9. መጓጓዣ የተለያዩ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴዎችን በማገናኘት ውስጥ ከፍተኛ ድረሻ አለው፡፡
10. የአገር ውስጥ ንግድ ገቢ ወይም ግብር ለመንግስት ለማስገባት ውስጥ ከፍተኛ ድርሻ አለው፡፡

## II በ "ለ" ሥር የተሰጡትን "ሀ" ሥር ከተሰጡት ጋር አዛምድ/ጂ

| | ሀ | ለ |
|---|---|---|
| 1 | ቱርዚም | ሀ. የአንደኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ |
| 2 | ግብርና | ለ. የሁለተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ |
| 3 | ብዙ ሰው የሚጠቀሚበት መጓጓዣ | ሐ. የሦስተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ |
| 4 | ከፍተኛ ዋጋ ያለውና በፍጥነት ዕቃ የሚጭንመጓጓዣ | መ. የምድር መጓጓዣ |
| 5. | በቀላል ወጭና ከባድ ዕቃዎችን የሚጭን መጓጓዣ | ሠ. የውሃ መጓጓዣ |
| 6 | የሣሙና ፋብሪካ | ረ. የአየር መጓጓዣ |

## III. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መለስ የያዜ ፍደል በመምረጥ ለመልስ የተዘገጀውን ቦታ ላይ ሙላ/ይ

1. ከሚከተሉት ውስጥ የባህላዊ መግለጫ ያልሆነ የቱ ነው?

   ሀ. ቋንቋ ለ. ሀይማኖት ሐ. ፖለትካ መ. መልስ የለም

2. የግሎባላይዘሽን መፈጠር መፈጠር ምክንያት የሆነው የቱ ነው?

   ሀ. የመገናኛ ቴክኖሎጂ ለ. የመጓጓዣ ቴክኖሎጂ ሐ. ሚድያ

   መ. ሁሉም መልስ ነው

3. ከሚከተሉት ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝብ የሚሳተፍበት የቱ ነው?

   ሀ. ግብርና ለ. ማዕድን ማውጣት ሐ. ዓሣ ማጥመድ

   መ. ደን መትከል

4. ለሻጭ የሚውል ዕቃዎች ኢትዮጵያ ወደ ውጭ ከሚትልክ ውስጥ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሪ የመያስገኘ የቱ ነው?

   ሀ. መኪና ለ. ነዳጅ ሐ. ቡና መ. የታሸገ ምግብ

5. የምግብ እህል ማምረት ግብርና እንቅስቃሴና እንስሳት ማርባት ጎን ለጎን የምካሄድ__________?

   ሀ. የእንስሳት ማርባት ግብርና   ለ. የዕፀዋት ማምረት ግብርና

   ሐ. ጥሚር ግብርና   መ. ኃላ ቀር ግብርና

6. ከፍላጎትና አቅርቦት ጋር ተያይዘው ውሸት የሆኔው የቱ ነው?

   ሀ. ፍላጎት ትንሽ ከሆነ የዕቃዎች ዋጋ ወደ ታች ይወርዳል

   ለ. ፍላጎት ከፍተኛ ከሆነ የዕቃዎች ዋጋ ይጨምራል

   ሐ. ፍላጎትና አቅርቦት ጠንካራ ግንኙነት አላቸው

   መ. ፍላጎትና አቅርቦት ግንኙነት የላቸውም

## IV. ለሚከተሉት ጥያቄዎች በተጠየከው መሰረት መልስ/ሽ

1. አገራችን ይበልጥ እያካሄደች ያላት የኢኮኖሚ እንቅስቃሴ የ__________ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ነው?
2. ፋብሪካ ማለት ምን ማለት ነው?
3. ፋብሪካ በስንት ይካፈላል? ስማቸውን ጻፍ/ፊ
4. የ1ኛ፣ የ2ተኛና የ3ተኛ ደረጃ ኢኮኖሚ እንቅስቃሴ ልዩነት ምንድነው?
5. በአቅርቦት ላይ ግፊት ከሚፈጥሩት ነገሮች አራት ጻፍ/ፊ

______________________________   ______________________________

______________________________   ______________________________

6. በፍላጎት ላይ ግፊት ከሚፈጥሩ ነገሮች ሦስት ጻፍ/ፊ

______________________________   ______________________________

______________________________

# ምዕራፍ 3

## 3. ተፈጥሮ ሀብት፤ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት

### ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ዉጤቶች

ከዚህ የምዕራፍ ትምህርት በ%ላ፤

- ✓ የተፈጥሮ ሃብት ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያላቸውን ጥቅም ትገነዘባለህ/ሽ፡፡
- ✓ የተፈጥሮ ሃብት ጠቀሜታ ለአገር ዕድገት ያላቸውን አስተዋፅዖ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- ✓ የአካባቢህ/ሽ ህዝብ የተፈጥሮ ሀብቶችን እንዴት እንደሚንከባከብ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- ✓ በተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ምክንያት የሚፈጠሩ ግጭቶች
- ✓ እንዴት እንደሚፈቱ ትለያለህ/ሽ፡፡

### መግቢያ

በዚህ ርዕስ ሥር የቀረበው ፅንሰ-ሃሳብ የተፈጥሮ ሃብቶች ለማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እድገት ያላቸውን አስተዋፅዖ ትማራለህ/ሽ፡፡ በተጨማሪም ተፈጥሮ ሃብቶች ለአገር እድገት ምን ጥቅም እንዳላቸውና ህዝቡም እነዚህን የተፈጥሮ ሃብቶች እንዴት እንደሚንከባከብ የሚለውን ፅንሰ ሃሳብ ትገነዘባለህ/ሽ፡፡ በመቀጠልም በተፈጥሮ ሀብቶች አጠቃቀም ምክንያት በህብረተሰቡ ዘንድ የሚፈጠሩ ግጭቶች እንዴት እንደሚፈቱ ትማራለህ/ሽ፡፡

# 3.1 ዘላቂ እድገት እንዲኖር የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና አጠቃቀም

## ቢያንስ ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃቶች፤

- በሰው ልጅ አማካይነት በተፈጥሮ ሃብት ላይ እየደረሰ ያለውን ተፅዕኖ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- ተፈጥሮ ሃብት ለማህበራዊና ኢኮኖሚ ላይ ያለውን ጥቅም ትረዳለህ/ሽ፡፡
- በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ ያላቸውን ነገሮችን ትለያለህ/ሽ፡፡
- የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ እንዲሁም በዘላቂነት በእነሱ የመጠቀም ሁኔታን ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን በተመለከተ ከአካባቢህ/ሽ ህብረተሰብ ጋር በመሳተፍ ሃላፊነትህን/ሽን ተወጣለህ/ሽ፡፡
- የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን በተመለከተ ህብረተሰቡ ያለውን የእውቀት ደረጃ ምን እንደሆነ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- በአካባቢህ ለሚገኙ ተፈጥሮ ሃብቶች አስፈላጊውን እንክብካቤ ታደርጋለህ/ሽ፡፡

### የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ

**መልመጃ 3.1**

1. እንክብካቤ ማለት ምን ማለት ነው?
2. በተፈጥሮ ሃብት ዘላቂነት ባለው ሁኔታ መጠቀም ማለት ምን ማለት ነው?
3. በተፈጥሮ ሃብት ላይ እየደረሰ ያለውን ጉዳት እንዴት መቀነስ ይቻላል?

በአሁኑ ወቅት የዓለም ህዝብ ቁጥር በየጊዜው በከፍተኛ ደረጃ በመጨመር ላይ ይገኛል፡፡ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ ደግሞ ፍላጎቱም እያደገ ይሄዳል፡፡ በዚህም የተነሳ የሰው ልጅ ፍላጎቱን ለሚሟላት ሲል ተጨማሪ ተፈጥሮ ሃብትን ይጠቀማል፡፡ በዚህም ምክንያት ተፈጥሮ ሃብት መጠኑ እየቀነሰና እያለቀ ይሄዳል፡፡

ይህ ስለሆነ ተፈጥሮ ሃብትን መንከባከብና በተገቢው ሁኔታ መጠቀም በጣም ወሰኝ ነው፡፡ ተፈጥሮ ሃብትን ለህብረተሰቡ እድገት ማዋል አስፈላጊ ነው፡፡ ተፈጥሮ ሃብትን መንከባከብ ያስፈለገበት ዋናው ምክንያት፤

- የአሁኑም ሆነ የወደፊቱ ትውልድ በተፈጥሮ ሃብት የመጠቀም መብት እንዲያገኝ ፤
- የአካባቢን ሚዛናዊነት በመጠበቅ ህይወት ያላቸውን ነገሮች ለማስቀጠል፤
- ያለምንም ብክነት በተፈጥሮ ሃብት መጠቀም፤
- የተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶች ዝርያን ከጥፋት ለማዳን ነው፡፡

በአሁኑ ወቅት ለተፈጥሮ ሃብት የሚደረገው እንክብካቤ በቂ ስላልሆነ ተፈጥሮ ሃብትን ከብክነት ለማዳን የሚከተሉትን እርምጃዎችን መውሰድ ወሳኝ ነው፡፡

1. የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን በተመለከተ ህብረተሰቡን ማስተማር፤
2. በቀጣይነት የተፈጥሮ ሃብቶችን ለወደፊቱ ትውልድ ለማስተላለፍ ማህረሰቡን ማበረታታት፤
3. ደን በሌለበት አካባቢ ዛፎችን በመትከል የአፈርን መሸርሸር መቀነስ
4. አካባቢን መንከባከብና የተገኙትን በሥርዓት ለመጠቀም የወጡትን ህጎች ተግባራዊ ማድረግ ፡፡
5. ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ትኩረቶችን ማጠናከር

- የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤን ከሁሉም ባለድርሻ ኣካላት ጋር በመወያየት የተገኘውን ውጤት ደግሞ ወደ ሥራ መቀየር፤
- ተፈጥሮ ሃብቶች ለአንድ አካባቢ ህብረተሰብ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ያላቸውን ግምት ውስጥ ማስገባትና
- በተለያየ ደረጃ የተፈጥሮ ሃብትን ለመንከባከብ የተቋቋሙትን ተቋማት ማጠናከር ናቸው፡፡

### 3.1.1 በዘላቂነት በተፈጥሮ ሃብቶች መጠቀም በኢኮኖሚ ላይ ያላቸው አስተዋፅዖ

ተፈጥሮ ሃብቶችን በዘላቂነት ጥቅም ላይ ማዋል ለወደፊቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ከፍተኛ አስተዋፅዖ አለው፡፡ ያሉትን የተፈጥሮ ሃብቶች በሥርዓት ለመጠቀም ቀድሞ መፍትሔ መስቀመጥ አስፈላጊ ነው፡፡ በዚህ መሠረት ቀጥሎ ያሉትን እንደ ምሳሌ መውሰድ ይቻላል፡፡

- ህዝቡ በተለያዩ የተፈጥሮ ሃብቶች እንዲጠቀም ማድረግ፤
- ህዝቡ ለረሃብ እንዳይጋለጥ የህብረተሰቡን የአመጋገብ ሥርዓትን ማሻሻል፡፡
- የህዝብ ቁጥርና የተፈጥሮ ሃብትን ማመጣጠን፤
- መሠረታዊ የህዝብ አገልግሎቶች እንደ ንፁህ ውሃ ፤መኖሪያ ቤት፤ የሥራ ዕድልን ለማግኘት የተለያዩ ዘዴዎችን መጠቀም ናቸው፡፡

### 3.1.2 በተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም ላይ ተፅዕኖ የሚያመጡ ነገሮች

በተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም ላይ የተለያዩ ነገሮች ተፅዕኖ ያሳድራሉ፡፡ ከነሱም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሰው ሰራሽ ወይንም ከሰው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮችና ተፈጥአዊ የሆኑ ነገሮች ናቸው፡፡

የሰው ልጅ ብዙውን ጊዜ የተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ የተለያዩ ልምዶችና ባህሎች አሉት፡፡

#### ሀ. ሰራሽ ወይንም ከሰው ጋር ተያያዥነት ያላቸው ነገሮች

የሰው ልጅ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ የተለያየ ዕውቀትና የሥራ ባሕል አለው፡፡ የሥራ ባህል ማለት የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ጋር ያለው ግንኙነት ነው ብሎ መግለፅ ይቻላል፡፡ ባህል ከቦታ ቦታ ልዩነት አለው ፡፡ በዓለም ላይ ያሉ ህዝቦች እንደ ቁጥራቸው ብዛት በተፈጥሮ ሃብት መጠቀም ላይ ያላቸው ባህል ከፍተኛ ልዩነት አለው፡፡

አፍሪካውያን በተፈጥሮ ሃብት ጠቀሜታ የዳበረ ልምድ ስለሌላቸው ከሌላው አህጉራት ጋር ስናነፃፅር የተፈጥሮ ሃብት ብክነት ይታያል፡፡ በዚህ የተነሳ ህዝቡ ከኋላ ቀርነትና ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች ውስጥ ሊወጣ አልቻለም፡፡ ለዚህም ደግሞ ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉት የተማረ የሰው ኃይል ማነስ፤ ኋላ ቀር ቴክኖሎጂን መጠቀም ፤ ጠንካራ የሥራ ባህል አለመኖር፤ የካፒታል እጥረት፤ የትራንስፖርት አለመስፋፋትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

#### ለ. ተፈጥሯዊ ምክንያቶች

የመሬት አቀማመጥና የአየር ንብረት ልዩነቶች ተፈጥሮ ሃብቶች እንደ ደን፤ ማዕድናት፤ አፈር፤ ውሃና የመሳሰሉት ከቦታ ቦታ መለያየት ምክንያት ናቸው፡፡ የእነዚህ የተፈጥሮ ሃብቶች መለያየት ደግሞ ከፍተኛ የማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ልዩነቶችን ሊያመጣ ይችላል፡፡

### 3.1.3 የተፈጥሮ ሃብቶች ከጊዜ ወደ ጊዜ ያለው ጠቀሜታ

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የተፈጥሮ ሃብቶች ለሰው ልጅ ያላቸው ጥቅም ምንድነው?
2. በተፈጥሮ ሃብቶችና በሰው ልጅ መካከል ያለው ግንኙነቶች ምንድናቸው?

የሰው ልጅ ከተፈጥሮ ሃብቶች የተለየዩ ጥቅሞችን ያገኛል፡፡ተፈጥሮ ሃብቶች ለህብረተሰቡ የየእለት ኑሮ መሠረት ናቸው፡፡ ለአገር ኢኮኖሚ ዕድገት ተፈጥሮ ሃብቶች ያላቸውን አስተዋፅዖ በተለያየ መልክ መግለፅ ይቻላል ፡፡ ለምሳሌ ተፈጥሮ ሃብቶች ያላቸውን ጥቅም የተወሰኑትን እንደሚከተለው መጥቀስ ይቻላል ፡፡ እነሱም

ለፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃነት ፤ ለምግብ ምንጭነት፤ ለግልና ለአገር እድገት ወሳኝ ናቸው፡፡ይሁን እንጂ የተፈጥሮ ሃብትን በሥርዓት ካልተጠቀምንባቸው ሊቀንሱ ወይንም ሊጠፉ ይችላል፡፡ ሰው በተፈጥሮ ሃብቶች በሚጠቀምበት ወቅት የሚፈጠሩ ግንኙነቶችን መገንዘብ የቻላል፡፡ እነዚህን ግንኙነቶች በሶስት ደረጃ መክፈል ይቻላል፡፡ እነሱም፤

**ሀ. ከአቅም በላይ የሆነ የሰው ቁጥር ፤** ይህ ማለት የአንድ አገር የህዝብ ቁጥር ካለው የተፈጥሮ ሃብት መጠን በልጦ ሲገኝ ነው፡፡ በእነዚህ አገሮች ውስጥ ቀጥሎ የተዘረዘሩት ችግሮች ሊከሰቱ የችላሉ፡፡

- ✓ ከፍተኛ ሥራ አጥነት መኖር፤
- ✓ የግልና የአገር ገቢ መቀነስ፤
- ✓ የአንድ ሰው የመኖር እድሜ ማጠር፤
- ✓ ድህነትና የፖለቲካ አለመረጋጋትና
- ✓ የማህበራዊ አገለግሎቶች አለመሟላትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**ለ. ከአቅም በታች የሆነ የሰው ቁጥር**

በተወሰኑት የዓለም አገሮች ውስጥ ያለው የህዝብ ቁጥር ከተፈጠሮ ሃብቶች ሥርጭት በታች ይሆናል፡፡ በዚህ ምክንያት በእነዚህ አገሮች ውስጥ ያለው የተፈጥሮ ሃብት ሙሉ በሙሉ በጥቅም ላይ ሳይውል ይቀራል፡፡ ይህም ሊሆን የሚችለው የሰው ጉልበት አናሳ ስለሚሆንና ትንሽ ቁጥር ያለው ሰው ሁሉንም

ሃብት አሟጦ መጠቀም ስለማይችል ነው። በመሆኑም የተፈጥሮ ሃብቶች ለብክነት ይዳረጋሉ። ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የምትሆነው አገር አውስትራሊያ ናት።

### ሐ. የሰው ቁጥርና የተፈጥሮ ሃብት መመጣጠን

በአንዳንድ አካባቢ የሰው ቁጥርና የተፈጥሮ ሃብት መጠን የተመጣጠነ ይሆናል። በእነዚህ አካባቢዎች የሰውና የተፈጥሮ ሃብቶች ግንኙነት ባህርያት እንደሚከተለው ይገለፃል፤

- ሳይንስና ቴክኖሎጂ ለውጥ ዕድገት፤
- የተሸለ የሰዎች የአኗኗር ሁኔታዎች፤
- የተሻለ የሥራ እድል መኖር፤
- የተሸለ መሠረታዊ የህብረተሰብ አገልግሎቶች መገኘት፤
- አስተማማኝና የተሻሻለ የኃይል ምንጭ መኖርና
- የኢንዱስትሪዎች መስፋፋት ናቸው።

## 3.1.4 የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤና አጠቃቀም

የግምገማ ጥያቄዎች

1. የተፈጥሮ ሃብቶችን ጥቅም ምንድን ናቸው?
2. ለተፈጥሮ ሃብቶች የሚደረገው እንክብካቤ ለምን አስፈለገ?
3. ያለጥንቃቄና እንክብካቤ የተፈጥሮ ሃብቶችን መጠቀም የሚያስከትለውን ጉዳት ምንድነው?

ተፈጥሮ ሃብትን ስንጠቀም በእንክብካቤና በጥንቃቄ መሆን አለበት። የተፈጥሮ ሃብቶችን ስንጠቀምባቸው በጥንቃቄ ካልሆነ ብክነትና መጥፋት ሊደርስባቸው ይችላል። የተፈጥሮ ሃብቶች ስርጭት በሁሉም አካባቢዎች ተመሳሳይ አይደለም፡ ፡ ለዚህ ደግሞ ትልቁ ምክንያት የሆነው የመሬት አቀማመጥ ልዩነት ነው። የመሬት አቀማመጥ ልዩነት የሌሎች ተፈጥሮ ሃብቶች አለመመሳሰልን ያመጣል።

የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ማለት በቀጣይነት በአግባቡ መጠቀምና ሳይባክኑ ለሚቀጥለው ተውልድ ማስተላለፍ ማለት ነው።

## ለተፈጥሮ ሃብቶች የሚደረጉ እንክብካቤዎች

### የአፈር እንክብካቤ

አፈር የተፈጠረው ከአለቶች ስብርባሪና ህይወት ካላቸው ነገሮች ብስባሽ ነው፡ ፡ አፈር ብዙ ዘመን ለውጥ ውስጥ አልፎ የተፈጠረ የተፈጥሮ ሃብት ነው፡፡ የአፈር ይዘቶች፤ አየር፤ ውሃ፤ ማዕድናት፤ ህይወት ያላቸው ነገሮችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የአፈር ባህርያት ደግሞ አደረጃጀት፤ ውሃ የመያዝና የማሳለፍ፤ የአፈር ቀለም፤ መጠናቸውና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ለም አፈር ምርት ለማምረትና ለዕጽዋቶች እድገት በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ አፈር ሁሉንም የእፅዋት አይነቶች ማብቀል ይችላል፡፡ እጽዋቶች ለሰው ልጅና ለሌሎች ህይወት ያላቸው የምግብ ምንጭነት ሆነው ያገለግላሉ፡፡ የህዝብ ቁጥር እየጨመረ ሲሄድ የተፈጥሮ ሃብቶች ፍላጎቱ እንደዚሁ እየጨመረ ይሄዳል፡ ፡ ይህ ሁኔታ ደግሞ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ እጽዋቶችን ይጎዳል፡፡ የእጽዋቶች መጎዳት ደግሞ ለአፈር መሸርሸር ምክንያት ይሆናል፡፡ ይህ ስለሆነ አፈርን መንከባከብ አስፈላጊ ነው፡፡

ለአፈር እንክብካቤ ከምናደርግባቸው ዘዴዎች ፤

**ሀ. ደን በመትከል፤** ለእርሻና ለተለያዩ አገልግሎቶች የማይውለውን መሬት ዛፍ በመትከል የአፈር መሸርሸርን መከላከል ይቻላል፡፡ በተጨማሪም እጽዋቶችን በመስመር እንዲሁም በዓይነታቸው ቀላቅሎ በመትከል የአፈርን መሸርሸር መከላከል ይቻላል፡፡ይህ ዘዴ በተለይ በንፋስ ሐይል የሚፈጠረውን የአፈር መጠረግን ይከላከላል፡፡

**ለ. ወደ ጎን ማረስ፤** ይህ አስተራረስ ዘዴ ተዳፋት መሬትን በውሃ እንዳይሸረሸር ለመከላከል የሚወሰድ ዘዴ ነው፡፡ ተዳፋት መሬት ላይ ዝናብ ሲዘንብ የሚፈጠረው ጎርፍ ቁልቁለት ከመፍሰስ ይልቅ ወደ ጎን በተሰራው ቦዩ ውስጥ ውሃ እንዲተኛ ይረዳል፡፡ በዚህ አይነት የሚተኛው ውሃ ወደ አፈር ውስጥ ሰርጎ የአፈርን እርጥበት ይጨምራል ማለት ነው፡፡



ሥዕል 3.1.4. ወደ ጎን የአስተራረስ ዘዴ

## ሐ. እርከን መሥራት

ከፍተኛ መሬት ላይ እርከን በመስራት አፈርን ከመሸርሸር መከላከል ይቻላል፡ ፡ ለዚህም ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የኮንሶ እርከን ሥራ ነው፡፡ የኮንሶ ህዝብ እርከን በመሥራት ከአገራችን አልፎ ለአለም ህዝብ ምሳሌ በመሆኑ በዩኔስኮ (UNSECO) ተመዝግቦ የማስታወሻ ሓውለት ቆሞለታል፡፡

**መ. የተለያዩ የእህል ዓይነቶችን በአንድ እርሻ ላይ መስመር በመስመር መዝራት፡፡** ይህም በተለያየ ጊዜ የሚደርሱትን አዝዕርት በመዝራት አንዱ ቀድሞ ቢደርስም የቀረው አዝዕርት አፈሩ በውሃና በንፋስ እንደይጠረግ ያደርጋል ፡፡

## ደንን በመንከባከብ ለዘላቂ ጥቅም ማዋል

የግምገማ ጥያቄዎች

1. የደን መመንጠር ምክንያቶች ምንድናቸው?
2. የሰው ልጅ በአካባቢው የሚገኘውን ደን ላይ ምን ዓይነት ጉዳት ሊያደርስ ይችላል?

በተወሰነ የአየር ንብረት ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ወይንም አንድ ዓይነት ዛፎች አንድ ቦታ ላይ በቅለውና አድገው የሚገኙት ደን ይባላል፡፡ በአለም

የህዝብ ቁጥር መጨመር ለደንና ለሌሎች የተፈጥሮ ሃብቶች ያለው ፍላጎት መጨመር ምክንያት ነው፡፡

ለደን መመንጠር የሚሆኑ ምክንያቶች

- የእርሻ መሬት መስፋፋት፤
- የመኖሪያ ቤት መስሪያ ቦታና ለመስሪያ የሚሆን እንጨት ፍለጋ፤
- የማገዶ እንጨት ፍለጋ እና የመሳሰሉትን ለማግኘት የሰው ልጅ ደን ላይ ያለው ፍላጎት ይጨምራል፡፡ በዚህ የተነሳ በደን ሃብት ላይ የሚከተሉት ጉዳቶች ይደርሳሉ፡፡ በተጨማሪም የከተሞች መስፋፋት፣ የመኪና መንገድ ሥራ ፣ዘመናዊ እርሻ፤ የግጦሽ መሬትና የፋብሪካዎች መስፋፋት ዋና ዋናዎቹ የደን መመናመን ምክንያቶች ናቸው፡፡ ይህ የደን መመናመን ደግሞ የሚከተሉትን ችግሮች ያስከትላል፡፡

- የአየር ንብረት ለውጥ፤
- የለም አፈር መጠረግ፤
- ህይወት ያላቸው ነገሮች ቁጥር መቀነስ፤
- የመሬት ገፅ ውሃ መድረቅ፤
- የዱር አራዊትና የሰዎች ስደትና
- ድርቅና ረሃብ ጥቂቶቹ ናቸው፡፡

## የዱር አራዊቶች እንክብክቤና ጥቅማቸው

የዱር አራዊት የሚባሉት ህይወት ያላቸው ከጥቃቅን ነፍሳቶች አንስቶ እስከ ትላልቅ አጥቢ እንስሳቶችን የሚያጠቃልል ሲሆን ከሰዎች ቁጥጥር ውጪ ወይንም ከሰው እርዳታ የማያገኙትን ሁሉ የሚያጠቃልል ማለታችን ነው፡፡ የዱር አራዊቶች የሚኖሩትም ከቀዝቃዛው እስከ ሞቃታማ አካባቢዎች ሲሆን በየብስና በውሃ አካላትም የሚያጠቃልል ይሆናል፡፡ በሚኖሩበት አካባቢ ላይ በመመሥረት የዱር እንስሳትን በአንድ አካባቢ በቋሚነት የሚኖሩና ከቦታ ቦታ እየተዘዋወሩ የሚኖሩ ብለን መክፈል እንችላለን፡፡በሌላ በኩል የዱር እንስሳት በአመጋገባቸውም ሳር በል፤ ሥጋ በል፤ ዕጽዋትና ሥጋ በል ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡ በኢትዮጵያ ብቻ የሚገኙ ብርቅዬ የዱር እንስሳቶች ውስጥ ዋሊያ፤ ቀይ ቀበሮ፤ ኒያላና የመሳሰሉት ናቸው፡፡




ሥዕል 3.1.4. በኢትዮጵያ የሚገኙ  የዱር አራዊቶች

## 3.2 ያለእንክብካቤ  በተፈጥሮ ሃብቶች መጠቀም ያለው ጉዳት

የግምገማ ጥያቄዎች

1. ያለምንም እንክብካቤ የተፈጥሮ ሃብትን መጠቀም ያለው ችግር ግለፅ/ጪ፡፡
2. የዱር አረዊቶች የምንንከባከብበት ዘዴዎች የትኞቹ ናቸው?

ያለእንክብካቤ  መጠቀም የተፈጥሮ ሃብቶች ብክነትና መመናመንን ስለሚያስከትል እያንዳንዱ  ዜጋ እንክብካቤ ሊያደርግላቸው ይገባል፡፡
በአሁኑ ጊዜ በአለም የተፈጥሮ ሃብቶች ብክነት በብዙ አገሮች ውስጥ ይታያል፡፡ በተለይ በአገራችን በህዝብ ቁጥር በፍጥነት መጨመር የተነሣ የተፈጥሮ ሃብት እንደ  ደን፤ ውሃና አፈር ጠቀሜታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህ ደግሞ ተፈጥሮ ሃብቶች መቀነስ አምጥቷል፡፡ ይህ በመሆኑ ማንኛውም ዜጋ የተፈጥሮ ሃብትን በተገቢው ሁኔታ መጠቀምና መንከባከብ ያስፈልጋል፡፡

## 3.3 በተፈጥሮ ሃብቶች አጠቃቀም ላይ የሚከሰቱ ግጭቶች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. ተፈጥሮ ሃብቶች ላይ የሚደርሱ ችግሮችን ዘርዝር/ሪ፡፡
2. የተፈጥሮ ሃብቶች ለኢኮኖሚ እድገት ያለው አስተዋፅያ ምንድነው?
3. የተፈጥሮ ሃብቶች እንክብካቤ ዘዴዎች ምንድን ናቸው?

በአግባቡ የማንጠቀምባቸው ከሆነ የተፈጥሮ ሃብቶች የመባከን ወይንም የመመናመን ሁኔታ እንደሚከሰትባቸው ይታወቃል፡፡ ይህ ስለሆነ ማህበረሰቡ የተፈጥሮ ሃብቶችን ሳያባክንና በጥንቃቄ መጠቀም ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም የተፈጥሮ ሃብቶች እጥረት ሲከሰት በህዝቦች መካከል የግጭት ምክንያት ሊሆን ስለሚችል አሰቀድሞ ግጭቱ እንዳይፈጠር የተፈጥሮ ሃብትን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል፡፡

የተፈጥሮ ሃብት ያለአግባብ መጠቀም ዓለማችንን ለተለያዩ ችግሮች ያጋልጣል፡፡ ዋናው የነዘህ ችግሮች መንስኤ ደግሞ በአንድ አካባቢ ያለው የህዝብ ቁጥር ከሚፈለገው በላይ በማደጉና በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም የተፈጥሮ ሃብት እየተመናመነ መሄድ ነው፡፡ የአንድ አካባቢ የተፈጥሮ ሃብት መባከን ለሌላውም አካባቢ ችግር ሊሆን የችላል፡፡

ይሁንና በአንደንድ አካባቢዎች የህን ቸግር ለመከላከል መተባበር ይልቅ የሚቃወሙ አገሮች አሉ፡፡ ለምሳሌ አሜሪካ በካይ ጋሶችን ለመቀነስ ስምምነት አለመፈረም አንዱ ማሳያ ነው፡፡ በዚህ ምክንያት አገሮች እነዚህን ችግሮች ለማስወገድ የሚከተሉትን እርምጃዎች መውሰድ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡

- ✓ ስለተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ከሁሉም ባለድርሻ ጋር መወያየትና የተገኘውንም ውጤት ወደ ተግባር መቀየር፤
- ✓ ተፈጥሮ ሃብት ለአንድ አካባቢ ማህበራዊና አኮኖሚያዊ ጥቅም መዋሉን ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት፤
- ✓ በተለያየ ደረጃ የተፈጥሮ ሃብትን ለመንከባከብ የተቋቋሙትን ማበረታታት፤
- ✓ በተፈጥሮ ሃብት አጠቃቀም ላይ የወጡትን መመሪያዎች ተግባራዊ ማድረግ፤

✓ ስለ ተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ህዝቡን ማስተማር፤


✓ እያንዳንዱን ዜጋ የተፈጥሮ ሃብቶች እንደ አፈር፤ ውሃ፤ የዱር አራዊቶች፣ደንና የመሳሰሉትን እንዲንከባከቡ ሁኔታዎችን ማመቻቸት።

## የውሃአጠቃቀምና እንክብካቤ

የግምገማ ጥያቄዎች

1. የውሃ አካላትን ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታቸውን ግለፅ/ጪ።
2. የውሃ ጥቅሞችን በቡድን ሆናችሁ ተወያዩና ለክፍል ጓደኞቻችሁ አቅርቡ፡

ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ለመኖር ውሃን ይፈልጋሉ። እፅዋቶች ምግባቸውን ለማዘጋጀት ውሃን ይጠቀማሉ። ውሃ ሳይቋረጥ ለማግኘት የውሃ ዑደት መኖር ወሳኝ ነው። 90% ከመሬት ላይ ውሃ ወደ ከባቢ አየር የሚገባው በትነትና በእፅዋቶች አተነፋፈስ ስርዓት(transpiration) ነው። ወደ ከባቢ አየር የሚገባው ትነት ዝናብ ፈጥሮ ተመልሶ ወደ ውሃ አካላት ይቀላቀላል። በአጠቃላይ የውሃ ዑደት ሂደቶች እንደሚከተለው ነው።




ሥዕል 3.3 የውሃ ዑደት

## የአለም ትላልቅ ወንዞች

በአለም ብዙ ትላልቅ ወንዞች አሉ። ብዛታቸው፣የያዙት የውሃ መጠንና ያላቸው ርዝመት ከአህጉር አህጉር ይለያያሉ። ከአለም ትላልቅ ወንዞች መካከል የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው።

ናይል ወንዝ ይህ ወንዝ ርዝመቱ ከአለም የመጀመሪያው ነው። ናይል ወንዝ ከምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛ ቦታዎች በመነሳት ብዙ ርቀት ከተጓዘ በኋላ ሜድትራንያን ባህር ይቀላቀላል። የናይል ወንዝ ለብዙ አፍሪካውያን በማህበራዊና ኢኮኖሚ ውስጥ ትልቅ ቦታ አለው።

አማዞን ወንዝ አማዞን ወንዝ የሚገኘው በደቡብ አሜሪካ ውስጥ ሲሆን ወንዙ ባለው የውሃ መጠንና ስፋት ከአለም አንደኛ ነው።

ያንግቲዝ ወንዝ በኤስያ አህጉር (ቻይና) ውስጥ የሚገኝ ነው።ይህ ወንዝ ከአህጉሩ በርዝመቱ የታወቀ ወንዝ ነው።

ኮንጎ ወንዝ ይህ ወንዝ በመካከለኛው የአፍሪካ ክፍል የሚገኝ ሲሆን የምድር ወገብን ሁለት ጊዜ ያቋርጣል።የኮንጎ ወንዝ ባለው የውሃ መጠን ከአማዞን ቀጥሎ በሁለተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ወንዝ ነው።

ሚሲሲፒ ወንዝ ሚሲሲፒ ወንዝ በሰሜን አሜሪካ (USA) ውስጥ ይገኛል።

## የውሃ ሃብት ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች

የውሃ ሃብት ብዙ ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች አሉት። ከእነዚህ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

ትራንስፖርት ለምሳሌ ህንድ ውቅያኖስ ፤ ቀይ ባህርና ኤደን ባህረ ሰላጤን የሚዋሰኑ አገሮች የባህር ትራንስፖርት ከእነዚ የውሃ አካለት ያገኛሉ። በሌላ በኩል ደግሞ በየብስ ላይም ያሉት የውሃ አካላት ለትራንስፖርት ይውላሉ። ለምሳሌ አፍሪካ ውስጥ ትላልቅ ሐይቆች እንደ ቪክቶሪያ፤ ታንጋናይካ፤ ማላዊና አልባርት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ደግሞ እንደ ጣና ፤ ደምበል (ዝዋይ) የትራንስፖርት አገልግሎትን ይሰጣሉ።

ለመስኖ የናይል ወንዝ በሱደንና በግብፅ አገሮች ውስጥ ፤ የሐዋስና ፊንጫኣ ወንዞች አትዮጵያ ውስጥ ለመስኖ እርሻ አገልግሎት ከፍተኛ አገልጊሎት እሰጡ ነው።

ለዓሣ እርባታ ለዓሣ እርባታ የሚውሉ የውሃ አካላት ባህሮችና ሐይቆች ብዙ ናቸው፡፡የቪክቶሪያ፤ ጣና፤ ቱርካና፤ ቀይ ባህር፤ ኤደን ባህረ ሰላጤ እና የህንድ ውቅያኖስ ከአፍሪካና አፍሪካ ዙሪያ ዋና ዋናዎቹ የዓሳ መገኛ ናቸው፡፡
የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጫነት በተለይ ከምስራቅ አፍሪካ ከፍተኛ ቦታዎች የሚነሱ ትላልቅ ወንዞች ከከፍታ ቦታዎች ላይ ወደ ቁልቁለት ስለሚወረወሩ ለከፍተኛ የኤሌክትሪክ ሀይል ማመንጨት ትልቅ አገልግሎት አላቸው፡፡ ለምሳሌ ኢትዮጵያ ውስጥ ብዙ ግድቦች ተገንብተዋል፤ እየተገነቡም ነው፡፡ ይንንም ከሚከተለው ሠንጠረዠ ተመልከት/ቺ፡፡

| የወንዙ ሥም | በወንዙ ላይ የተገነባው ግድብ |
|---|---|
| ሐዋስ | ቆቃ |
| አበይ | የህዳሴው ግድብ፤ ጢስ እሳት |
| ፊንጫኣ | ፊንጫኣ |
| ዋቢ ሸበሌ | መልካ ዋከና |
| ጊቤ | ጊቤ 1ኛ፤2ኛና 3ኛ |
| ተከዜ | ተከዜ |

በየጊዜው እየጨመረ የሚሄደው የህዝብ ብዛት የተነሳ የውሃው መጠን ክምችት ከምድረ ገፅ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ይህም ሊሆን የቻለው ለውሃው ያለው ፍላጎት መጨመር ሲሆን፤ ከእነዚህም ውስጥ ለመጠጥ ፤ለመስኖ ሥራ፣ ለፋብሪካዎች ለጥሬ እቃነትና እጥበት፤ እና ለመሳሰሉት ናቸው ፡፡
ከሰው ሰራሽ ምክንያቶች በተጨማሪ በተፈጥሮ ምክንያቶችም እንደ አየር ለውጥ ፤ የዉሃ ትነት መጨመር፤ የእፅዋቶች መመንጠርና ሌሎችም የምድረ ገፅና ከርሰ ምድር የውሃ ክምችት መቀነስ ናቸው፡፡

## የምዕራፍ ሦስት ማጠቃለያ

የተፈጥሮ ሃብት ማለት በተፈጥሮ በአካባቢያችን ውስጥ የሚገኙ የተለያዩ ነገሮች፤ ለሰው ልጅና ለሌሎች እንስሳት መኖር በጣም አስፈላጊ የሆኑ ናቸው፡ ፡ እነዚህ የተፈጥሮ ሀብቶች መገኛቸው ከቦታ ቦታ ይለያያል። ይህም ሊሆን የቻለው የአየር ንብረት፤ የመሬት አቀማመጥ፤የአፈር ለምነትና የህዝብ ቁጥር መለያየት ናቸው። በተለይ አፍሪካ ውስጥ የመሬት አቀማመጥ የተፈጥሮ ሃብት ሥርጭት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ አለው።

አፍሪካ ብዙ የተፈጥሮ ሀብቶች ቢኖራትም ይህን የተፈጥሮ ሀብት በአግባቡ አልተጠቀመችበትም። ስለሆነም ህዝቡም ከፍተኛ ድህነት ውስጥ ይገኛል።.

## የምዕራፍ 3 ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. የሚከተሉተን ዐ/ነገሮች ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ /ሺ

1. የተፈጥሮ ሀብትን መንከባከብና ማስቀጠል ፍላጎት እንጂ ግዴታ አይደለም።
2. አሁን ያለው ሀብት ለወደፊቱ ትውልድ መሆን የለበትም።
3. በተፈጥሮ ሀብት አጠቃቀም ላይ የሚፈጠረው ግጭት በሰላም መፈታት አለበት።
4. የተፈጥሮ ሀብት ያላቸው ሀገሮች ሁሉ ኢኮኖሚያዊ መሻሻል አምጥተዋል።

II. ቀጥሎ ‘ለ’ ሥር ካሉት ውስጥ መርጠህ ‘ሀ ‘ ሥር ካሉት ጋር አዘምድ/ጂ

| ‘ሀ’ | ‘ለ’ |
|---|---|
| 1. አማዞን ወንዝ | ሀ. አፍሪካ |
| 2. ኮንጎ ወንዝ | ለ. ኤሲያ |
| 3. ናይል ወንዝ | ሐ. ሰሜን አሜሪካ |
| 4. ሚሲሲፒ ወንዝ | መ. ደቡብ አሜሪካ |
| 5. ያንግትዝ ወንዝ | |

## III. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ/ሺ፡፡

1. የተፈጥሮ ሀብቶችን መንከባከብና መጠቀም የማያቋረጥ ሂደት ነው ሲባል ምን ማለት እንደሆነ ግለፅ/ጪ፡፡
2. በተከታታይነት የተፈጥሮ ሀብትን መጠቀም ኢኮኖሚ ላይ ያለውን ጥቅም ግለፅ/ጪ፡፡
3. በተፈጥሮ ሀብት ጠቀሜታ ላይ ተፅዕኖ የሚያደርሱትን ነገሮች ጥቀስ/ሺ፡፡
4. የአፈር እንክብካቤና ቀጣይ ጠቀሜታ እንዴት ይከናወናል?
5. የውሃን ምጣኔ ሀብታዊ ጠቀሜታን ግለፅ/ጪ፡፡
6. የደን መመንጠር የሚያስከትለውን ችግር ዘርዝር/ሪ ፡፡
7. የህዝብ ቁጥር መጨመርና የተፈጥሮ ሃብት ብክነት ያላቸውን ግንኙነት አብራራ/ሪ፡፡

# ምዕራፍ 4

## ዘመናዊው የአለም ታሪክና አጀማመሩ

### ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርት ውጤቶች፤

- ✓ ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ሂደት ትገልጻለህ/ሽ
- ✓ የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter - Reformation) በማነጻጸር ታገናዝባለህ/ሽ
- ✓ ስለ ኢንዱስትሪ አብዩት ጽንሰ ሀሳብ በስፋት ትገልጻለህ/ሽ
- ✓ የሁለቱን የአለም ጦርነቶች ምክንያትና ባህሪያት ታገናዝባለህ/ሽ
- ✓ ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ባህሪያት ትገልጻለህ/ሽ፡፡

### መግቢያ

በሰባተኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ስለ ቀደምት አውሮፓ፣ ኤሽያ እና የአፍሪካ ስልጣኔዎች ተምረሀል/ሻል፡፡ በተጨማሪም ስለ ክርስትና ሀይማኖትና እስልምና ሀይማኖት አመጣጥ እንዲሁም መስፋትን ተምረሀል/ሻል፡፡ በተጨማሪም ስለ ባዛንታይን ኢምፓየር ባህሪያትን ለይተሀል/ሻል፡፡

በ8ኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ደግሞ በዘመናዊው የአለም ታሪክ ውስጥ ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ትማራለህ/ሽ፡፡ እንዲሁም ስለ አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation) ትማራለህ/ሽ፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ስለ ኢንዱስትሪው አብዮት ውጤቶች፣ የሁለቱን የአለም ጦርነቶች እና ስለ ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ትማራለህ/ሽ፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሳሾች ሲጠቀሙበት የነበረውን የአሰሳ መስመሮችን በካርታ ላይ ታሳያለህ/ለሽ
- የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation) ትገልጻለህ/ሽ
- የኢንዱስትው አብዩት ያመጣውን ለውጥ ትዘረዝራለህ/ሽ
- ሁለቱ የአለም ጦርነቶች ያስከተሉትን ጉዳቶች በጽሁፍ መልክ በማዘጋጀት ታቀርባለህ/ሽ
- በሁለቱ የአለም ጦርነቶች የተፈጠሩትን ክስተቶች ትገልጻለህ/ሽ
- የቀዝቃዛው አለም ጦርነት ባህሪያት ታገናዝባለህ/ሽ፡፡

## 4.1. ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ የተጀመረበት ምክንያትና ሂደቱ ላይ ተወያዩበት
2. የሰው ልጅ እንዴት በባህርና በውቅያኖሶች ላይ መጓዝ ቻለ?
3. ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ውጤቶችን ዘርዝር/ሪ

ጂኦግራፊያዊው የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ መጀመር ለዘመናዊው ታሪክ እድገት ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡ እንዲሁም የአለምን ህዝብ ያስተሳሰረ ነበር፡፡ ለረጅም ዘመናት በአውሮፓ እና በሌላው አህጉር የሚኖሩ የአለም ማህበረሰብ በመሬት ላይ አሰሳ ሲገናኝ ቆይቷል፡፡ የአውሮፓ ነገዴዎች ከእሩቅ ምስራቅ እስከ መካከለኛውና ደቡብ ምስራቅ ኤሽያ በባህላዊ መጓጓዣ ዘዴ ሲጓዙ ቆይተዋል፡፡ ይህ አሰሳ ከባድ ቢሆንም ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖሊቲካዊ ችግሮችን ሲፈታ ቆይቷል፡፡ ይሁን እንጂ ከ11ኛው

ክፍለ ዘመን ጀምሮ በአውሮፓውያኖችና በኦቶማን ቱረኮች መካከል ያለው አለመግባባት እየተካረረ በመምጣቱ በመሬት ላይ ወደ ኤሽያ የሚወስደው መንገድ ሊዘጋ ችሏል፡፡ይህ አለመግባባት ከ1090ዎቹ እስከ 1270ዎቹ እ.አ.አ የተካሄደውን የመስቀል ጦርነት ሊያስከትል ችሏል፡፡


በዚህ ሁኔታ ወደ ምስራቅ የሚሄደው የንግድ መስመር በመዘጋቱ ምክንያት አውሮፓውያኖች አዲስ የንግድ መስመር ለመፈለግ ተገደዋል፡፡ አውሮፓውያኖች የፖለቲካና ምጣኔ ሀብታዊ ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ጉዞአቸውን ወደ ምዕራብ አቅጣጫ በመቀየር ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ አካሂደዋል፡፡ በዚህ መሰረት በንፋስ ሀይል የሚገፉ መርከቦችን በመጠቀም ከምዕራብ አውሮፓ በመነሳት ወደ ምዕራብ አፍሪካ አሰሳ ጀመሩ፡፡ በጊዜ ሂደት የፖርቹጋልና የእስፔን አሳሾች እስከ ደቡብ አፍሪካ ጫፍ ጉዞ አድርገዋል፡፡ በዚህ መሰረት በ1488 ባርቶሎሚዩ ዲየዝ የደቡብ አፊሪካ ጫፍ ሲደርስ፣ ቫስኮ ዳጋማ ደግሞ በ1498 ሕንድ ሊደርስ ችሏል፡፡ በ1492 ክርስቶፈር ኮሎምቦስም ቀድሞ የማይታወቀውን አህጉር አሜሪካን ሊያገኝ ችሏል፡፡ እንዲሁም ከ1519-1522 ፈርዲናንድ ማጄላን አለምን ለመጀመሪያ ጊዜ ዞሯል፡፡ የፈርዲናንድ ማጄላን አሰሳ አለም የሉል ቅርጽ እንዳላት ያረጋገጠ ነበር፡፡

ከጥንት ዘመን ጀምሮ ብዙ አውሮፓዊያኖች የባህር ላይ ጉዞ በመጀመር የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ሲያካሄዱ ቆይተዋል፡፡ ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ እንዲሳካ ካደረጉ ሀገሮች መካከል ዋናዎቹ ፖርቹጋል እና እስፔን ናቸው፡፡ በተጨማሪም ይህ አሰሳ እንዲሳካ ካደረጉት ነገሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የኮምፓስ መገኘት፣ ካርታን መጠቀም መቻል እና ዘመናዊ መርከቦችን ለአገልግሎት ማዋል ናቸው፡፡ በተጨማሪም የ16ኛው ክፍለ ዘመን የምጣኔ ሀብት ዕድገት የባህር ላይ አሰሳ እንዲሳካ ትልቅ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ትላልቅ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን አምጥቷል፡፡ ከእነዚህ ለውጦች ውስጥ ዋናዋናዎቹ ከምጣኔ ሀብታዊ ዕድገት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት አውሮፓዊያኖች አዲሱን

የንግድ መስመር በመጠቀም በአሜሪካና በአፍሪካ አህጉራት እንዲሁም በእሩቅ ምስራቅ መስፈር የተለያዩ ቦታዎች መስፈር ችለዋል፡፡ አውሮፓዊያኖች የሰፈሩበትን አህጉሮች የተፈጥሮ ሀብት በመዝረፍ የሀገራቸውን ካፒታልና ኢንዱስትሪ ማበልጸግ ችለዋል፡፡

በፖሊቲካዊና በማህበራዊ ዘርፎች ደግሞ የባሪያ ንግድና የቅኝ ግዛት ስርዓቶች እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡ በዚህ ሁኔታ በ17ኛው እና በ18ኛው ክፍለ ዘመን እስፔንና ፖረቹጋል ደቡብ አሜሪካን በመቆጣጠር የምጣኔ ሀብታዊና የፖሊቲካዊ የበላይነትን አግኝተዋል፡፡ እንደ ሆላንድና እንግሊዝ ደግሞ እስፔንና ፖረቹጋልን በመከተል ደቡብ ምስራቅ ኤሽያን፣ ደቡብ አፍሪካን እና ደቡብ ምስራቅ አፍሪካን ሊቆጣጠሩ ችለዋል፡፡




ካርታ 4.1 የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ መስመሮች

### መልመጃ 4.1

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. ጂኦግራፊያዊው የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ በስኬት ሲያካሄዱ ከነበሩ ሀገሮች ውስጥ ሁለቱን ፃፍ/ፊ
1. ፈርዲናንድ ማጄላን በምን ይታወቃል?
1. አዲሱ አህጉር ተብሎ የሚታወቀው አህጉር ማን ነው? ለምን አዲሱ የአለም አህጉር ተባለ? ግለፅ/ጪ
1. ከጂኦግራፊያዊው የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ጋር ተያይዞ ካደጉት ጥበቦችና ዕውቀቶች ውስጥ ሶስቱን ፃፍ/ፊ
1. የአለምን ካርታ በማንሳት ቫስኮ ዳጋማ የተጓዘበትን አቅጣጫ አሳይ/ዪ
1. ጂኦግራፊያዊ የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ያስገኘውን ውጤቶች ዘርዝር/ሪ

## 4.2 የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance) የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation)

### 4.2.1. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance)

የሙከራ ጥያቄዎች

1. በቀደምት የአለም ስልጣኔ ዘመን የተገኙት አዳዲስ ጽንሰ ሀሳቦች ላይ ተወያዩ
2. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦች መፍለቅ (Renaissance) ዋናው መነሻ ምክንያት ምንድ ነው?
3. በሁለት ቡድን በመከፈል የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መፍለቅ (Renaissance) ባህሪያት ላይ በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ

በቀደምት የአለም ስልጣኔ ዘመን ውስጥ የሰው ልጅ እንደ ዴሞክራሲ ስርዓት፣ የሪፐብሊክ አስተዳደር ስርዓት እና የተለያዩ ህጎችን መመስረት

መቻሉን በ7ኛ ክፍል ትምህርት ውስጥ ተምረሃል/ሻል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ይህን ቀደምት የአለም ስልጣኔ ለማስቀጠል ሲባል የሰው ልጅ አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን ማፍለቅ ጀመረ፡፡ እነዚህ አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች መሰረት ያደረጉት ቀደምት የአለም ስልጣኔን በጥልቀት መልሶ ማጥናት፣ መፈተሽ እና ማገናዘብ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በተለይ ጥንታዊ የግሪክ እና የሮማ ስልጣኔዎችን መልሶ በጥልቀት ማጥናትና መጠቀም ዋናው ትኩረቱ ነው፡፡

አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን ማፍለቅ ወይም የአለም ህዳሴ የተጀመረው በ14ኛው ክፍለ ዘመን በጣሊያን ሲሆን ከ14ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ወደ ሌሎች ሀገሮች መስፋፋት ችሏል፡፡ በአጠቃላይ ይህ እንቅስቃሴ የተለያዩ እውቀቶች፣ ጥበቦች ፣ ሳይንሳዊ ሀሳቦች እና የተለያዩ የፈጠራ ስራዎች ከ14ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 17ኛው ክፍለ ዘመን ያደጉበትና የተስፋፉበት ጊዜ ነበር፡፡

አዲሱን ጽንሰ ሃሳብ መልሶ የማስፋፋት ዘመን የተለያዩ ባህሪያት አሉት፡፡ እነሱም የተለያዩ እውቀቶችን ማስፋፋትና አሳማኝ ምክንያቶችን መጠቀም ናቸው፡፡ እንዲሁም ሀሳብን በነጻነት መግለፅ፣ የቀደምት ስልጣኔ ላይ ጥናትና ምርምር ማድረግ፣ በጥልቀት ማሰብ እና እራስን መጠየቅ ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በተጨማሪም የአፍ መፍቻ ቋንቋን በመጠቀም ልዩ ልዩ የፈጠራ ስራዎችን ማካሄድ፣ መጻፍ እና የሰው ልጅ አመጣጥ ላይ በጥልቀት ጥናት እና ምርምር ማድረግ ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት የሰው ልጅ የእለት ተእለት ኑሮውን በሚያካሂድበት ጊዜ አሳማኝ ምክንያቶችን ማቅረብ መቻል አለበት፡፡ በቂ ማስረጃ የሌላቸውና አሳማኝ ያልሆኑ ጉዳዮችን በተደጋጋሚ ማገናዘብ አስፈላጊ ነው የሚል ሀሳብን ጭምር ያካትታል፡፡

በአጠቃላይ አዲሱ ጽንሰ ሃሳብን መልሶ የማስፋፋት ዘመን አብዛኛውን የግሪክና የሮማን ስልጣኔ መልሶ ማጥናት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ በዚህ መሰረት ቀለማትን የመቀባት ጥበብ፣ ስነ ህንፃ፣ ስነ ሥዕል እና የሰው ልጅ ህዋስ ላይ ጥናትና ምርምሮችን ማካሄድ ያካተተ ነበር፡፡ በተጨማሪም ሳይንሳዊ በሆነ መልኩ የተለያዩ ሃሳቦችን ማገናዘብ፣ ሀሳብን በነፃነት የመግለፅ እና ዕውቀትን የማስፋፋት ስራ ተሰርቷል፡፡

## 4.2.1. የፕሮጀክት ስራ

I. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ጥያቄዎች በታዘዛችሁት መሰረት ለክፍላችሁ ተማሪዎች አቅርቡ

1. አምስት አባላት ያለው ቡድን በመመሰረት በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በምሁራን የተሳሉትን ስዕሎችን በመፈለግ አስመስላችሁ ሳሉ

2. በቡድን በመሆን በአውሮፓውያን መካከለኛው ክፍለ ዘመን ምሁራን የሰሩትን ስራዎች የተለያዩ ቀለማትን በመጠቀም እንጨትን፣ ጭቃን እንዲሁም ካርቶንን በመጠቀም የተለያዩ የቤት ዕቃዎችን በመስራት ለክፍል ተማሪዎች አሳዩ

ከዚህ በታች ባለው ሠንጠረዥ ውስጥ የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች ባለቤት የሆኑ ምሁራንና የተለያዩ የፈጠራ ስራዎቻቸው ስለተዘረዘሩ በአግባቡ ለመረዳት ሞክሩ፡፡

ሠንጠረዥ 4.2.1.የታዋቂ ምሁራን አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችና ስራዎቻቸው

| የምሁራኖቹ ስም | ዓመተ ምህረት | ዜግነት | የፈጠራ ስራዎቻቸው |
|---|---|---|---|
| ኒኮላስ ኮፐርንከስ | 1473-156 | ፖላንድ | የህዋ ጥናትና የፀሀይ ስርዓት አጥንቷል |
| ቶማስሙር | 1466-1533 | እንግሊዝ | ዩቶፒያ የሚለውን ጽንሰ ሀሳብ አፍልቋል |
| ቬሳሊየስ | 1514-64 | ቤልጂየም | የሰው ልጅን የስሜት ህዋስና የደም ዝውውር ስረአትን አጥንቷል |
| ዊሊያም ሼክስፒር | 1483-1546 | እንግሊዝ | ድራማና ቲያትርን ጽፏል |
| ዋይክሊፍ | 1328-84 | እንግሊዝ | መጽሀፍ ቅዱስን ወደ እንግሊዘኛ ቋንቋ ተርጉሟል |

### 4.2.2. የተሓድሶ እንቅስቃሴ (Reformation)

#### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የተሓድሶ  እንቅስቃሴ እንዴት ተጀመረ?
2. የተሓድሶ  እንቅስቃሴ ምክንያቶችን በመዘርዘር ተወያዩበት

የካቶሊክ ሀይማኖት ተሓድሶ እንቅስቃሴ የተጀመረው በ16ኛው ክፍለ ዘመን በምዕራብ አውሮፓ በማርቲን ሉተር አማካኝነት ነው፡፡ የተሓድሶ እንቅስቃሴው የተጀመረበት ምክንያቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነሱ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ሀይማኖትና መንግሥት መለያየት አለባቸው የሚል ሀሳብ፣ የካቶሊክ ቤተክርስትያን የበላይነትና የስልጣን ገደብ አለመኖር፣ የካቶሊክ ቤተክርስትያን ንብረት ወሰን አለመኖር እና ሁሉም ሰው ሀይማኖቱን በነፃነት የመከተል መብት መከልከል ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በካቶሊክ ቤተክርስትያን አስተዳደር ውስጥ የቤተክርስትያን መሪዎች ከፍተኛ የግል ሀብት ለማፍራት ሲባል ሲያካሂዱ የነበሩት አላስፈላጊ ድጊቶች/ሙስና/ ለክርስትና ሀይማኖት ተሐድሶ እንቅስቃሴ ዋነኛው ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡

የተሓድሶ እንቅስቃሴ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን በኋላ ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች ሊስፋፋ ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት በ1517 ማርቲን ሉተር ግልጽ በሆነ መንገድ ሉተሪያን የሚል ቤተክርስቲያን አቋቁሟል፡፡ በተጨማሪም ማርቲን ሉተር በመጽሀፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉተን ሃሳቦች በመጠቀም በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሲካሄዱ የነበሩትን አላስፈላጊ ድጊቶችን ግልፅ አውጥቷል፡፡እንዲሁም መጽሀፍ ቅዱስን ወደ ጀርመንኛ ቋንቋ ተርጉሟል፡፡ በተመሳሳይ ጆን ካልቪን የካልቪኒስት ቤተክርስቲያን በማቋቋም ሀይማኖቱ እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ንግስት ኤልሳቤት (1558-1603) የአንግሊካን ቤተክርስቲያን በማቋቋም ሰዎች ሁሉ በነፃነት እንዲከተሉት አድርጋለች፡፡በዚህ እንቅስቃሴ የተመሰረቱ የክርስትና ሀይማኖት ቅርንጫፎች የፕሮቴስታንት ሀይማኖት (Protestant Christian Religion) በመባል ይታወቃሉ፡፡

በአጠቃላይ ከተሐድሶ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዘው የመጡ ለውጦች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነሱም ውስጥ የፕሮቴስታንት ክርስቲያን ሀይማኖት መመስረት፣

በካቶሊክ ቤተክስቲያን ውስጥ የአስተዳደር ለውጥ መምጣት፣ የዘመናዊ ትምህርት መስፋፋት እና የሀይማኖት ተቋማት መብት መከበር ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

## 4.2.3. የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation)

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የካቶሊክ ሀይማኖት ተከታዮች ለምን የክርስትና ሀይማኖት ተሐድሶ እንቅስቃሴን (Reformation) ተቃወሙ?
2. ከተሓድሶ እንቅስቃሴ ጋር ተያይዘው የመጡ ለውጦችና የተወሰዱ እርምጃዎችን ዘርዝር/ሪ
3. አራት አራት አባላት ያላቸውን ቡድኖች በመመስረት የተሓድሶ እንቅስቃሴና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞን በማነፃፀር አገናዝቡ፡፡

የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ (Counter-Reformation) ማለት የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ለተሓድሶ እንቅስቃሴ መልስ ለመስጠት ያደረገችው ውስጣዊና ውጫዊ የተሓድሶ እንቅስቃሴ ማለት ነው፡፡ የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ ዋና ዓላማ በተሓድሶ እንቅስቃሴ የተነሱትን ተቃውሞዎች በመለየት ውስጣዊ ተሓድሶ ማድረግ እና በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ ለተነሱት ጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ነው፡፡ እንዲሁም የካቶሊክ ሀይማኖት ተከታዮች ወደ ሌላ ሀይማኖት እንዳይሄዱ ለማስተማር የታሰበ ነው፡፡ ስለዚህ የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ ዘመቻ የተካሄደው በውስጣዊ እና በውጫዊ አካሄድ ነው፡፡

የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተሓድሶ የተለያዩ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ የመጀመሪያው እርምጃም የእየሱሳዊያን ቤተሰብ (The Society of Jesus) መመስረት ነው፡፡ ሁለተኛው ደግሞ በፊት የነበሩትን የካቶሊክ ቤተክርስቲያን የሀይማኖት አባቶችን በመሻር አዳዲስና በህዝብ ፊት ተቀባይነት ያላቸው የሀይማኖት አባቶችን መሾም/መቀባት/ነበር፡፡ ሶስተኛው ደግሞ በአለም አቀፍ ደረጃ ትላልቅ ስብሳባዎችን በማድረግ በተሓድሶ እንቅስቃሴ የተነሱትን ተቃውሞዎች ማውገዝ ናቸው፡፡

በ1534 የእየሱሳዊያን ቤተሰብ (The Society of Jesus) በእስፔናዊው ኢግናቲዎስ ሎዮላ ተመሰረተ፡፡ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የእየሱሳዊያን ቤተሰብን (The Society of Jesus) የተሓድሶን ተቃውሞ በማውገዝ የካቶሊክ ሀይማኖትን በኤሽያ፣ አውሮፓ፣ አሜሪካ እና አፍሪካ ማስፋፋት ችለዋል፡፡ ይህ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን ተሓድሶ ቡድን (missionary) ከ1557-1665 አከባቢ ወደ ኢትዮጲያ በመምጣት ንጉስ ሱስንዮስ የካቶሊክ ሀይማኖት እንዲቀበል አድርጓል፡፡ በዚህ ምክንያት የሀይማኖት ግጭት በጎንደር ከተማ ሊነሳ ችሏል፡፡

ይህን ግጭት ለማረጋጋት ሲባል ንጉስ ፋሲለደስ የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ ቡድንን (missionary) ከሀገር አባሯል፡፡ በዚህም የተነሳ ከአውሮፓውያን ጋር ያለውን የውጭ ሀገር ግንኙነትን በማቋረጥ ዝግ የሆነ የውጭ ግንኙነት ፖሊሲን (Close Door Policy) ተግባራዊ አድርጓል፡፡ ይህ ፖሊሲ ከአንድ ክፍለ ዘመን በላይ ሀገሪቱን ከውጭ ሀገር ግንኙነት ሊያርቃት ችሏል፡፡

## መልመጃ 4.2

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን መልሶ የማስፋፋት እንቅስቃሴ ዓላማ ምንድ ነው?
2. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን መልሶ የማስፋፋት እንቅስቃሴና የክርስትና ሀይማኖት ተሐድሶ ልዩነቶችን ግለፅ/ጪ
3. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን መልሶ የማስፋፋት እንቅስቃሴ የት ተጀመረ?
4. የዴሞክራሲ ጽንሰ ሃሰቦችንና አዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦችን በማነፃፀር ግለፅ/ጪ
5. በካቶሊክ ቤተክርስቲያን ላይ የተነሱትን ተቃውሞዎች ዘርዝር/ሪ
6. የአዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦች ባለቤት የሆኑ ምሁራን እንደ ማርቲን ሉተር፣ ሊኦናረዶ ዳቪንቺ፣ ዊሊያም ሼክስፒር እና የሚካኤል አንጄሎ ስራዎችን ግለፅ/ጪ

## 4.3 የኢንዱስትሪ አብዮት

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. የኢንዱስትሪና የፋብሪካ ልዩነት አብራራ/ሪ
2. የኢንዱስትሪ አብዮት ማለት ምን ማለት ነው?
3. የኢንዱስትሪ አብዮት ጥቅምና ጉዳት በማነፃፀር ግለፅ/ጪ

የኢንዱስትሪ አብዮት የሰው ልጅ ከባህላዊ የማምረት ዘዴ ወደ ዘመናዊ የማምረት ዘዴ የተሸጋገረበት ሂደት ነው፡፡ የኢንዱስትሪው አብዮት የተለያዩ ዕድገቶችንና የስራ ዘርፎች እንዲፈጠሩ ከፍተኛ አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡ ይህ የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረውና ከፍተኛ እድገት ያስመዘገበው በእንግሊዝ ሀገር ውስጥ ነው፡፡በዚህ መሰረት በ1750ዎች ውስጥ የተለያዩ ማሽኖችን በመጠቀም ምርቶች በከፍተኛ ቁጥርና ጥራት እንዲመረቱ ማድረግ ተችሏል፡፡ የፋብሪካዎች በፍጥነት መስፋፋት የአንድ ሀገር ምጣኔ ሀብት ፣ ፖሊቲካና እንዲሁም ቴክኖሎጂዎች እንዲያድጉ ትልቅ አስተዋጽኦ አበርክቷል፡፡በእንግሊዝ ሀገር የተጀመረው የኢንዱስትሪ አብዮት በሂደት ወደ ሌሎች የአውሮፓ ሀገሮች እንዲሁም ወደ ሰሜን አሜሪካ ሊስፋፋ ችሏል፡፡

### በእንግሊዝ ሀገር የኢንዱስትሪ አብዮት እንዲጀመር ያዳረጉት ነገሮች፤


- በቂ የከሰል ድንጋይና የብረት ምርት መኖር፤
- እንግሊዝ በባህር የተከበበች መሆኗና ብዙ የመርከቦች ማረፊያ ወደቦች መኖር፤
- ሰላምና መረጋጋት እንዲሁም መልካም አስተዳርር የሰፈነባት ሀገር መሆኗ፤
- የምጣኔ ሀብት ዕድገትን ለማረጋገጥ የተለያዩ ሳይንሳዊ ጥናትና ምርምሮች መካሄዱ፤

የባህር ላይ ንግድ ደህንነትን ለማስጠበቅ በቂ የባህር ሀይሎች መኖርና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

የኢንዱስትሪ አብዮት ሁለት ትላልቅ ደረጃዎች አሉት፡፡ ከእነሱ ውስጥ የመጀመሪያው ደረጃ ከ1750-1870ዎቹ የቆየ ሲሆን የተለያዩ የቴክኖሎጂ

ፈጠራዎችንና እደጥበቦችን ማስፋፋት ችሏል፡፡ ከእነዚህ የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ውስጥ ዋናዋናዎቹ፤ በእንፋሎት ሀይል የሚሰሩ ቀላል ማሽኖች መሰራታቸው፣ ብረትን የሚያቀልጥ የከሰል ድንጋይ መጠቀም መቻል፣ ዘመናዊ መጓጓዣ እና የመገናኛ ብዙሃን መዘመን ናቸው፡፡ በእንፋሎት ሀይል የሚሰሩ ዘመናዊ መጓጓዣዎች እንደ ባቡርና መርከብ እንዲሁም መኪና በአገልግሎት ላይ ውለዋል፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ የጨርቃ ጨርቅ፣ የምግብ ዘይት፣ የዱቄት ፋብሪካዎች እና ጥጥ የሚፈትል ማሽን በመጠቀም ብዛትና ጥራት ያለው ምርት እንዲመረት ማድረግ ተችሏል፡፡

ሁለተኛው የኢንዱስትሪ አብዮት የተጀመረው በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሁለተኛው አጋማሽ ነበር፡፡ በዚህ ዘመን የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችና የፈጠራ ስራዎችም ተስፋፍተዋል፡፡ ከእነዚህ የፈጠራና ቴክኖሎጂ ስራዎች ውስጥ አንዱ የኤሌክትሪክ ኃይልን ማመንጭት መቻል ነው፡፡ በተጨማሪም የጠፈር ላይ ጥናት በከፍተኛ ደረጃ ተከሄዷል፡፡ በዚህም መሰረት ሳተላይቶችን ወደ ህዋ በማምጠቅ አዳዲስ ምርምሮችን ማካሄድ የተጀመረበት ጊዜ ነበር፡፡ በአጠቃላይ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ዘመናዊ የመገናኛ ብዙሃን በማስፋፋት የአለምን ህዝብ ግንኙነት ማጠናከር ተችሏል፡፡ እንዲሁም ትላልቅ ማሽኖችን የሚያመርት ማሽን የተፈጠረበት ጊዜ ነበር፡፡



ሥዕል 4.3 ትላልቅ ማሽኖችን የሚያመርት ፋብሪካ

የኢንዱስትሪ አብዮት የተለያዩ ጥቅሞችና ጉዳቶች አሉት፡፡ ከኢንዱስትሪ አብዮት ጥቅሞች ውስጥ አንዱ በእጅ የአመራረት ዘዴን ወደ በማሽን የማምረት ዘዴ መቀየሩ ነው፡፡ በሰው ጉልበት ሲመረት የነበረው ምርት ጉልበትና ጊዜን በሚቆጥበው በዘመናዊው ማሽን መተካቱ ምርትና ምርታማነትን ማሻሻል ችሏል፡፡ የከሰል ድንጋይን፣ የፀሀይ ብርሃን እና የውሃ ሀይልን በማመንጨት መጓጓዥን እና መገናኛ ብዙሃንን ማዘመን መቻሉ ሌላው የኢንዱስትሪ አብዮት ጥቅም ነው፡፡ በአጠቃላይ የኢንዱስትሪ አብዮት መስፋፋት ግብርና እና ኢንዱስትሪን በማስተሳሰር ምርትን ማሳደግ ችሏል፡፡

## የፕሮጀክት ስራ 4.3. (ሀ)

I. ሶስት ወይም አራት አባላት ያለው ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች የተሰጠውን የፕሮጀክት ስራ በመስራት አሳዩ

1. በአከባቢያችሁ የሚገኙትንና የምትጠቀሙባቸውን የፋብሪካ ምርቶች አስመስላችሁ በመስራት ለመምህራችሁ አሳዩ፡፡

የኢንዱስትሪ አብዮት እንደ ጥቅሙ ሁሉ የተለያዩ ጉዳቶችን አስከትሏል፡፡ ከእነሱም ውስጥ ዋናው ስራ አጥነትንና ድህነትን ማስፋፋቱ ነው፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታም ከገጠር ወደ ከተማ ስደትን በማስፋፋቱ የተነሳ ማህበራዊ ችግሮችን አስፋፍቷል፡፡ በመሆኑም ብዙ እናቶች በፋብሪካ ውስጥ ተቀጥረው በመስራታቸው ህፃናትን ማሳደግና መንከባከብ ላይ ከፍተኛ ችግር ፈጥሯል፡፡ ከዚህም ሌላ ጥቃቅን ባህላዊ(የጎጆ) ኢንዱስትሪዎችን ከውድድር ውጭ አድርጓቸዋል፡፡ ከእነዚህም ማህበራዊ ችግሮች በተጨማሪም የአከባቢ ብክለትና የአየር ለውጥ አስከትሏል፡፡ ይህ የአየር ለውጥም በረሃማነትና ድርቅ እንዲስፋፋ አድርጓል፡፡

የጥሬ ዕቃና ሰፊ ገበያ ፍለጋ በመስፋፋቱ በአውሮፓዊች መካከል ከፍተኛ ፉክክርና ትልቅ ግጭት እንዲፈጠር ምክንያት ሆኗል፡፡ ይህ ግጭትም ለአንደኛው የአለም ጦርነት መጀመር ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡ ይህም

ፋክክር የአፍሪካ፣ አሜሪካ እና የኤሽያ አህጉሮች በቅኝ ግዛት ስር እንዲወድቁ ትልቅ አስተዋጽዖ አድርጓል፡፡

## መልመጃ 4.3(ለ)

I. ከዚህ በታች ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል የሆኑትን "እውነት" ትክክል ያልሆኑትን "ሐሰት" በማለት መልስ/ሽ፡፡

1. የኢንዱስትሪ አብዮት የማሽኖች ለውጥ ብቻ ላይ ያተኮረ ነበር
2. የኢንዱስትሪ አብዮት ሁለት ደረጃዎች አሉት
3. እንግሊዝ የኢንዱስትሪ አብዮት መነሻ ማዕከል ነበረች
4. ትምህርት፣ ቴክኖሎጂ እና መገናኛ ብዙሀን የተስፋፋው በመጀመሪያው ደረጃ የኢንዱስትሪ አብዮት ዘመን ነበር፡፡

II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. በእንግሊዝ ሀገር የኢንዱስትሪ አብዮት እንዲጀመር ካደረጉት ነገሮች ውስጥ ሦስቱን ዘርዝር/ሪ
1. በሞባይል መጠቀም በየትኛው የኢንዱስትሪ አብዮት ደረጃ ውስጥ ይመደባል?
2. ከኢንዱስትሪ አብዮት ጥቅሞች ውስጥ ሦስቱን ዘርዝር/ሪ
3. ከኢንዱስትሪ አብዮት ጉዳቶች ውስጥ ሦስቱን ዘርዝር/ሪ፡፡

## 4.4 .ትላልቅ የአለም ጦርነቶች

### 4.4.1 የአንደኛው አለም ጦርነት (1914-1918)

#### የሙከራ ጥቄዎች

1. በጦርነት ፅንሰ ሀሳብ ላይ ተወያዩበት
2. የአንደኛው አለም ጦርነት ምክንያቶች ላይ ተወያዩበት
3. የአንድ አከባቢ ማህበረሰብ የአለመግባባትና ግጭት ምክንያቶችን ከአንደኛው የአለም ጦርነት ምክንያቶች ጋር በማነጻጸር ገምግም/ሚ
4. የአንደኛው አለም ጦርነት ያስከተለውን ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ማህበራዊ ለውጦችን በማደራጀት ለክፍል ተማሪዎች በዘገባ መልክ አቅርብ/ቢ፡፡

በአለም አቀፍ ደረጃ ሁለት ትላልቅ የአለም ጦርነቶች ተካሄዷል፡፡ እነሱም አንደኛው (1914-1918) እና ሁለተኛው (1939-1945) የአለም ጦርነቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ትላልቅ የአለም ጦርነቶች አጀማመር መንስኤ፣ ሂደት እና የተለያዩ ውጤቶች አሏቸው፡፡ በዚህ መሰረት እነዚህ የአለም ጦርነቶችም ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖሊቲካዊና ማህበራዊ ለውጦችን አምጥዋል፡ ፡ በዚህ መሰረት አንደኛው የአለም ጦርነት የራሱ የሆነ መሰረታዊ እና ቅጽበታዊ ምክንያቶች አሉት፡፡ የአንደኛው የአለም ጦርነት መሰረታዊ ምክንያቶች የሚባሉትም፤

- በአውሮፓ ውስጥ ብሔረተኝነት መስፋፋት፤
- የቅኝ ገዥዎች ፉክክር፡- በአውሮፓ መንግሥታት መካከል ቅኝ ግዛትን የመያዝ ፉክክር ለምሳሌ ፈረንሳይና ጀርመን ሞሮኮን ለመያዝ፣ ሩሲያና ኦስትሮ ሀንጋሪ በባልካን አገሮች አካባቢ መፎካከር ፣ እንግሊዝና ጀርመን በምሥራቅና መካከለኛ አፍሪካ መገኘትና የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል፡፡
- የተለያዩ የጦር ቡድኖች መመስረት፤ ለጦርነት ዝግጅት ማድረግ፣ ወታደር መመልመል፣ ማሠልጠን እና ዘመናዊ የጦር መሣሪያ ማስታጠቅ ናቸው፡፡ በዚሁ መሠረት የአውሮፓ አገሮች ሁለት ተቃራኒ ወታደራዊ ቡድኖችን አቋቁመዋል፡፡ እነርሱም መካከለኛው ኃይሎች (Central Powers)፤ ጀርመን፣ ኦስትሮ-ሀንጋሪና ጣሊያን ሲሆኑ የሦስትዮሽ ኅብረት (Triple Alliance) ቡድኖች ደግሞ ፈረንሳይ፤ እንግሊዝ እና ሩሲያ ናቸው፡፡ ጦርነቱም እንደተጀመረ ጣሊያን ከመካከለኛው ኃይሎች(Central Powers) በመውጣት ወደ የሦስትዮሽ ኅብረት (Triple Alliance) ተቀላቅላለች፡፡

ጦርነቱ ሲጀመር ብዙ አገሮች በሁለቱም ወታደራዊ ቡድኖች ውስጥ ተቀላቅለዋል፡፡ የመካከለኛው ኃይል ቡድን የመሠረቱት ሀገሮች እንደ ጀርመን፣ ኦስትሮ-ሀንጋሪና ጣሊያን ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ጣሊያን ከቡድኑ ስትወጣ ኦቶማን ቱርክና ቡልጋሪያ ደግሞ ቡደኑን ተቀላቅለዋል፡ ፡ የሦስትዮሽ ኅብረት (Triple Alliance) ደግሞ ፈረንሳይ፤ እንግሊዝ እና ሩሲያ ናቸው፡፡ ጣሊያን በ1915፤ ሰርቢያና ቤልጅየም ጨምሮ በአጠቃላይ ብዙ አገሮች ደጋፊዎች ነበሩት፡፡ የአለም አገሮች ባብዛኛው፤ በቀጥታም

ሆነ በተዘዋዋሪ መንገድ አንዱን ቡድን በመደገፍ ሌላውን ሲወጉ ነበር፡፡ የአለም ጦርነት የተባለበት ምክንያትም የአለም አገሮች በአብዛኛው በዚህ ጦርነት ስለተሳተፉበት ነው፡፡

የአንደኛው አለም ጦርነት በቅፅበት መቀስቀስ ምክንያት የሆነው በ1914 የኦስትሮ-ሀንጋሪ መንግሥት አልጋ ወራሽ ፍራንሲስ ፈርድናንድና ባለቤቱ ግድያ ነበር፡፡



ፎቶግራፍ 4.4. (ሀ) ፍራንሲስ ፈርድናንድና ባለቤቱ ሶፊያ

ከኦስትሮ-ሀንጋሪ መንግሥት አልጋ ወራሽ ግድያ በኃላ የኦስትሮ-ሀንጋሪ መንግሥት ለሰርቢያ ማስጠንቀቂያ ላከች፡፡ ሩሲያ የሰርቢያ ወዳጅ ስለነበረች ጦሯን ማደራጀት ጀመረች፡፡ ጀርመን ደግሞ ኦስትሮ- ሀንጋሪን በመደገፍ በ1914 ቤልጅየም ላይ ጦርነት አወጀች፡፡ በዚህ ዓይነት የተጀመረው ጦርነት ወደ አለም ጦርነት ተሸጋግሯል፡፡ በ1917 አሜሪካ በትሪፕል ኢንቴንት (ፈረንሳ፣ እንግልዝና ሩሲያ) ወገን ጦርነቱን በመቀላቀል የጦር ሚዛኑ እንዲቀየር ማድረግ ችላለች፡፡ በመጨረሻም በ1918 የአንደኛው የአለም ጦርነት በእንግሊዝ ቡድን አሸናፊነት ሊጠናቀቅ ችሏል፡፡

የአንደኛው አለም ጦርነት ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞችና ጉዳቶችን አምጥቷል፡፡ የአንደኛ አለም ጦርነት ያስከተለው ጉዳቶች ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል፤

- በ10 ሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ሞተዋል፤ ከ20 ሚሊዮን በላይ የሆኑ ቤተሰቦች ተሰደዋል እንዲሁም ተበታትነዋል፤
- ጀርመን ከፍተኛ የገንዘብ ቅጣት እንድትከፍል በቨርሳይልስ ስምምነት(1919) ተወስኖባታል፤
- አሜሪካና የሦስትዮሽ ህብረት መንግሥታት በማሸነፋቸው የምጣኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ የበላይነት ማግኘት ችለዋል፤
- ከ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያው አካባቢ የኦቶማን ቱርክ፣ አውሰትሮ-ሀንጋሪ እና የጀርመን ኢምፓየሮች መፈራረስ ችለዋል፡፡
- የአለም መንግሥታት ሊግ በ1919 በፈረንሳይ ሀገር በቬርሳይል ከተማ መመሥረት ናቸው፡፡ድርጅቱም የተመሠረተው በአሸናፊ አገሮች ነበር፡፡



ፎቶግራፍ 4.4. (ለ) የአንደኛው አለም ጦርነት ያስከተለውን ጉዳት

## 4.4.2. ሁለተኛው የአለም ጦርነት (1939 —1945)

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. አንደኛው የአለም ጦርነትን ምክንያቶችን ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ጋር በመነፃፀር ገምግም/ሚ
2. አሜሪካ በሁለተኛው የአለም ጦርነት ላይ እንዴት ልትሳተፍ ቻለች? መሳተፏ ያመጣው ለውጥ ምንድነው?
3. በሁለተኛው የአለም ጦርነት ላይ ኢትዮጵያ መሳተፏን ወይም አለመሳተፏን ተወያዩበት
4. ሁለተኛው የአለም ጦርነት ያስከተለው ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ላይ በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ልክ እንደ አንደኛው የአለም ጦርነት ሁለተኛውም የአለም ጦርነት የተለያዩ ምክንያቶች አሉት፡፡ እነሱም መሰረታዊና ቅፅበታዊ ምክንያት ናቸው፡፡ መሰረታዊ ምክንያቶች እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፤

- የኢምፔሪያሊስት ኃይሎች ሥልጣን መያዝ፤ እነርሱም የጀርመን ናዚስት የኢጣሊያ ፋሽስት እና ጦረኛዋ ጃፓን ናቸው፡፡ በዚህ መሰረት ከ1920ዎቹ ጀምሮ ቤኒቶ ሞሶሎኒ በጣልያን ውስጥ ስልጣን በመያዝ ፋሺዝምን አውጇል፡፡ በ1930 ደግሞ አዶልፍ ሂትለር የናዚዝምን ፅንሰ ሀሳብ በመያዝ በ1930ዎቹ ወደ ስልጣን መጥቷል፡፡
- የአለም መንግሥታት ሊግ መዳከም እንዲሁም የመደራደርና የመለማመጥ ፖሊሲ አለመሳካት፤
- የአንደኛው አለም ጦርነት ውጤቶች ለምሳሌ ከ1929—1933 የነበረው ኢኮኖሚ መዳከም፣ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ ዜጎች ሥራ ማጣት፣ የቬርሳይለስ ስምምነት ውሳኔዎች ተጽዕኖ ጀርመንን ለበቀል እንድትነሳሳ ማድረጉ እና የመሳሰሉት ናቸው፡፡



ፎቶግራፍ 4.4.2. ከግራ ወደ ቀኝ ቤኒቶ ሞሶሎኒና አዶልፍ ሂትለር

ጦርነቱ ከመጀመሩ በፊት የአክሲስ ቡድን(ጀርመን፣ ጣልያን እና ጃፓን) የጦር ዝግጅት ካደረጉ በኋል ተቀናቃኞቻቸውን የአላይድ ቡድን ላይ ጦርነት አወጁ፡፡ መስከረም 1, 1939 ጀርመን ፖላንድ ላይ በከፈተችው ወረራ የአላይድ ቡድኖች እንደ ቅጽበታዊ ምችንያት በመጠቀም ሁለተኛው የአለም ጦርነትን ለመቀስቀስ ችለዋል፡፡ በዘዚህ መሰረት እንግሊዝና ፈረንሳይ በጀርመን ላይ ጦርነት በማወጃቸው ሁለተኛው የአለም ጦርነት በአውሮፓ ሊጀመር ችሏል፡፡

በ1941 የጃፓን ጦር በሐዋይ ደሴቶች በፐርል ሀርበር የነበረውን የአሜሪካን ጦር ማዘዣ ጣብያ አጠቃ፡፡ ይህ ደግሞ አሜሪካ ወደ ጦርነቱ እንድትገባ ቅፅበታዊ ምክንያት ሆኗል፡፡ በመቀጠልም በ1945 የአሜሪካ የጦር አውሮፐላኖች ሁለት የጃፓን ከተሞችን ሂሮሺማና ነጋሳኪን በአውቶሚክ ቦንብ ደብድበዋል፡፡ በመጨረሻም የሃይል ሚዛኑ ወደ አላይድ ቡድን አገሮች አዘንብሏል፡፡ በዚሁ መሠረት የኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ተሸንፈው ጦርነቱ በ1945 ተጠናቋል፡፡

ሁለተኛው የአለም ጦርነት የተለያዩ ጥቅሞችንና ጉዳቶችን አምጥቷል፡፡ ከጥቅሞቹ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፤

- የተባበሩት የአለም መንግስታት ድርጅት መመስረት፤
- የቅኝ ግዛት ስርዓት መፍረስና የተለያዩ ሀገራት ነፃ መውጣት፤
- ኢንዱስትሪና ፋብሪካዎች መስፋፋት፤
- የአሜሪካና ሶቭየት ሕብረት ሃያል መንግሥታት መሆን መቻላቸውና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ሁለተኛው የአለም ጦርነት ከፍተኛ ጉዳቶችን አስከትሏል፡፡ እነሱም፤

- በርካታ ሀብት ወድሟል ለምሳሌ ለጦርነቱ ብዙ ቢሊዮን የአሜሪካ ዶላር ወጪ ሆኗል፡፡ እንዲሁም በርካታ መሰረተ ልማቶችና ከተሞች መውደም፤
- ከ50 ሚሊዮን በላይ ሰዎች መሞት፣ የስራ አጥነትና ድህነት መስፋፋት፤
- እንደ ጀርመን፣ ጃፓን፣ ጣሊያንና የመሳሰሉት ሀገራት መሸነፋቸው በአገራቸው የመንግሥት ለውጥ እንዲመጣ አድርጓል፡፡

## መልመጃ 4.4

### ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. ከአንደኛው የአለም ጦረነት ምክንያቶች ውስጥ አራቱን ዘርዝር/ሪ
2. የአንደኛው አለም ጦርነት በቅጽበት መቀስቀስ ምክንያት የሆነውን ግለፅ/ጪ
3. አሜሪካ ወደ ሁለተኛ የአለም ጦርነት መቼና እንዴት ተቀላቀለች?
4. አንደኛውና ሁለተኛው የአለም ጦርነት ያስከተለውን ማህበራዊ ጉዳቶችን ግለፅ/ጪ
5. አንደኛውና ሁለተኛው የአለም ጦርነቶች በኢትዮጲያ ላይ ያስከተሉትን ፖለቲካዊ ተፅዕኖ የተለያዩ መረጃዎችን በማገናዘብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ
6. የአሜሪካ የጦር አውሮፕላኖች ሁለት የጃፓን ከተሞችን ሂሮሺማና ነጋሳኪን በአውቶሚክ ቦንብ መደብደባቸው ያስከተለውን ጉዳት መረጃዎችን በማገናዘብ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

## 4.5.ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት

የሙከራ ጥያቄዎች

1. ከሁለተኛው የአለም ጦርነት ምን እንደተገነዘባችሁ ዘርዝሩ
2. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ማለት ምን ማለት ነው?
3. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት መቀስቀስ ምክንያት ምንድነው?
4. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ያመጣው ውጤቶችን በመዘርዘር ሰፊ ውይይት አድርጉ፡፡

ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ማለት የሀሳብ ወይም የአመለካከት ግጭት ማለት ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ አለም በምጣኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግጭቶች የተነሳ እንዲሁም በእርስ በርስ ፍረጃና መወነጃጀል ምክንያት የተካሄደ ጦርነት ነው፡፡ በዚህ መሰረት አለም በሁለት ጎራዎች ልትከፈል ችላለች፡፡ እነሱም የምዕራቡ ጎራና የምስራቁ ጎራ ናቸው፡፡ የምዕራቡ ጎራ በአሜሪካ የሚመራ የካፒታሊስት አገሮችን ያካተተ ሲሆን የምስራቁ ጎራ ደግሞ በሶቬት ኅብረት የሚመራ  የኮሚኒስት ሀገሮች ጥርቅም ነው፡፡

አሜሪካ የኮሚኒስት ሀገሮችን ስለምትጠራጠራቸው ለማዳከምና ለማጥፋት ወሰነች፡፡ይህ ደግሞ የሀሳብና የአመለካከት ልዩነት በምዕራብና በምስራቁ ቡድኖች መካከል እንዲፈጠር አድርጓል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከ1945 በኋላ በሶቬት ኅብረት የሚመሩ የኮሚኒስት ሀገሮች አሜሪካን ለማዳከምና ለማጥፋት ትልቅ እንቅስቃሴ አድረገዋል፡፡ በአጠቃላይ ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በካፒታልስት አገሮችና በኮሚኒስት ሀገሮች መካከል የኢኮኖሚና የፖሊቲካ ፉክክር እንዲከሄድ አድርጓል፡፡

ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ግልጽ በሆነ መንገድ የተካሄደ ጦርነት አይደለም፡፡ ነገር ግን ከ1953-54 በሁለቱ ኮሪያዎች መካከል የተካሄደው ጦርነት እና በ1956-1974 በቬትናም የተካሄደው ጦርነት በቀጥታ ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት እንዲጀመር አድረገዋል፡፡ በእነዚህ ጦርነቶች ውስጥ አሜሪካና ራሽያ በተዘዋዋሪ መንገድ ተሳትፏል፡፡ እንዲሁም የጦር መሳሪያ የማምረት ፉክክር እንዲካሄድ አድርገዋል፡፡

ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ከተጠናቀቀ በኋላ የተለያዩ ጥቅሞችንና ጉዳቶችን አምጥቷል፡፡ ከጥቅሞቹ ውስጥ ዋና ዋናዎቹ እንደሚከተሉት ተዘርዝረዋል፤

- የተለያዩ ሀገሮች ምጣኔ ሀብት መቀጨጭ
- እንደ ሰሜንና ደቡብ ኮርያ ያሉ ሀገሮች በሁለት እዲከፈሉ አድርጓል
- መርዛማ የጦር መሳሪያዎች መመረትና ጥቅም ላይ መዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ካስገኘው ጥቅም ውስጥ አንዱ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነታቸውን እንዲጎናጸፉ ማድረግ መቻሉ ነው፡፡ በተጨማሪም የተለያዩ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂዎች እንዲስፋፉ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ሂደቱም እስከ ሶቭየት ኅብረት መፈራረስ ድረስ ቆይቷል፡፡

መልመጃ 4.5

ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. ቀዝቃዛውን የአለም ጦርነት በበላይነት ሲመሩ የነበሩትን ሁለቱን ሀገሮች ፃፍ/ፊ
2. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ካደረሰው ጉዳቶች ውስጥ ሦስቱን ዘርዝር/ሪ
3. በቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ምክንያት የተመሰረቱ ጎራዎችን(camps) ግለፅ/ጪ
4. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት ለምን ቀዝቃዛው ጦርነት ተባለ?
5. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በይበልጥ የተካሄባችውን ሀገሮች በመለየት ያደረሰውን ጉዳቶች በመለየት ግለፅ/ጪ፡፡

## ማጠቃለያ

የሰው ልጅ አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን ማፍለቅ ከጀመረ በኋላ ትላልቅ ለውጦችን ማምጣት ችሏል፡፡ ከእነዚህ ለውጦች ውስጥ ዋናዋናዎቹም የባህርና የውቅያኖስ ላይ አሰሳ ማካሄድ፣ የተሓድሶ እንቅስቃሴ እና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞዎች ናቸው፡፡በተለይ የተሓድሶ እንቅስቃሴና የተሓድሶ እንቅስቃሴ ተቃውሞ ከሀይማኖት ተሐድሶ ጋር ተያያዥነት ባላቸው ጉዳይዮች ላይ ለውጦችን አምጥተዋል፡፡ይሁን እንጂ የካቶሊክ ቤተክርስቲያን መሰረታዊ ለውጥ ባለማምጣቱ ለፕሮቴስታንት ክርስቲያን ሀይማኖት (Protestant Christian Religion) መመስረት ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡

18ኛ ክፍለ ዘመን ከመጀመሪያው ጀምሮ የኢንዱስትሪው አብዮት በአለም ላይ ትላልቅ ለውጦችን አምጥቷል፡፡ በዚህ መሰረት በ1750ዎች ውስጥ የኢንዱስትሪ አብዮት ከእንግሊዝ ሀገር ወደ ሌሎች ሀገራት መስፋፋት ችሏል፡፡ ይሁን እንጂ የተለያዩ የጦር መሳሪያዎች መመረት የተለያዩ የጦር ቡድኖች በአለም ላይ እንዲመሰረቱ አድርጓል፡፡ ይህ ደግሞ ለአንደኛውና ለሁለተኛው የአለም ጦርነቶች መጀመር ምክንያት ሊሆን ችሏል፡፡

በአጠቃላይ አዳዲስ ጽንሰ ሃሰቦችን ማፍለቅ በአለም ላይ ትላልቅ ለውጦችን ማምጣት ችሏል፡፡ የኢንዱስትሪው አብዮትም ለዘመናዊው የአለም ዕድገት ትልቅ አስተዋጽዎ አበርክተዋል፡፡

## የምዕራፉ ማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. ከዚህ በታች ያሉትን ዐረፍተ ነገሮች ትክክል የሆኑትን “እውነት” ትክክል ያልሆኑትን “ሐሰት” በማለት መልስ/ሽ

1. የኢንዱስትሪው አብዮት ጥቅም እንጂ ጉዳት የለውም
2. በ15ኛው እና በ16ኛው ክፍለ ዘመን ውስጥ ከተካሄደው የባህርና ውቅያኖስ ላይ አሰሳ ፖርቹጋል ከፍተኛውን ሚና ተጫውታለች
3. የአዲሱ ፅንሰ ሀሳቡ እንቅስቃሴ በምዕራብ አውሮፓ የተጀመረ የሀይማኖት እንቅስቃሴ ነው
4. የተሓድሶ እንቅስቃሴ ከመፅሐፍ ቅዱስ በተቃራኒ የተካሄደ እንቅስቃሴ ነው
5. ከአንደኛው የአለም ጦርነት ምክንያቶች ውስጥ አንዱ የብሔርተኝነት እንቅስቃስሴ ነው

II፡ ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ በመምረጥ መልስ ስጥ/ጪ

1. የፖርቹጋል ዜጋ የሆነውና ለመጀመሪያ ጊዜ የደቡብ አፍሪካ ጫፍ የደረሰው ማነው?
   ሀ. ቫስኮ ዳጋማ
   ለ. ባረቶሎሞው ዲያዝ
   ሐ. ክርስቶፈር ዳጋማ
   መ. ፈርድናንድ ማጄላን
2. በተሓድሶ እንቅስቃሴ ውስጥ ትልቅ አስተዋጽኦ ያበረከተው ማነው?
   ሀ. ማርቲን ሉተር
   ለ. ማርቲን ሉተር ኪንግ
   ሐ. ቶማስ ሙር
   መ. ኒኮላስ ኮፐርኒከስ
3. ከዚህ በታች ስማቸው ከተዘረዘሩት የኢትዮጵያ ንጉሣን ውስጥ የካቶሊክ ሀይማኖትን በመቀበል ሀገራዊ ሀይማኖት ያደረገው ንጉስ ማነው?
   ሀ. ፋሲለደስ
   ለ. ሱሲንዮስ
   ሐ. ኢዛና
   መ. ተስፋ ኢየሱስ

4. የኢንዱስትሪ አብዮት በየትኛው የህብረተስብ መደብ ተመሰረተ?
   ሀ. ላባደሮች
   ለ. አርሶአደሮች
   ሐ. ከበርቴው
   መ. ሀ እና ሐ መልስ ናቸው

4. ለአንደኛው የአለም ጦርነት መጀመር ቅጽበታዊ ምክንት የሆነው የቱ ነው?
   ሀ. ብሄርተኝነት
   ለ. ጦረኝነት
   ሐ. የፍራንሲስ ፈርድናንድ መገደል
   መ. የአብርሀም ሊነከን መገደል

6. በአንደኛው የአለም ጦርነት መጨረሻ የተፈረመው ስምምነት የቱ ነው
   ሀ. ቨርሳይለስ
   ለ. ሞስኮ
   ሐ. በርሊን
   መ. ዋርሶ

## III. ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ታሪካዊ ክስተቶች በቅደም ተከተላቸው ከቅርብ ዘመን ወደ ሩቅ ዘመን በመዘርዘር ፃፍ/ፊ

1. የአለም መንግሥታት ድርጅት መመስረት፣ የሂሮሽማ እና ነጋሳኪ መመታት፣ የቨርሳይለስ ስምምነት፣ የናዚና ፋሽስት ስልጣን መያዝ፡፡

## IV.ከዚህ በታች ለተዘረዘሩ ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. በሁለተኛ የአለም ጦርነት በአውቶሚክ ቦምብ የጋዩ ሁለቱ የጃፓን ከተሞችን ፃፍ/ፊ
2. ቀዝቃዛው የአለም ጦርነት በስንት ቡድን መካከል ተካሄደ?
3. የግሪኮ-ሮማን ስልጣኔ ላይ በማተኮር የተካሄደው ጥናትና ምርምር ምን ይባላል?

# ምዕራፍ 5

# የአፍሪካ ታሪክ ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ

## ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ ውጤቶች

- ✓ የአፍሪካ ባርያ ንግድ ስርዓት ትገልፃለህ/ሽ
- ✓ የቅኝ ግዛት ስርዓት በአፍሪካ ያስከተለውን ችግሮች ትዘረዝራለህ/ሽ
- ✓ የአፍሪካ ህዝቦች ለነፃነታቸው ያደረጉትን ትግል ታገናዝባለህ/ሽ
- ✓ በቅኝ ግዛት ስርዓት ዘመን የአፍሪካ ምጣኔ ሀብታዊና ፖሊቲካዊ ግንኙነቶችን ታብራራለህ/ሽ፡፡

### መግቢያ

ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የአፍሪካ ህዝቦች የተለያዩ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ እና ማህበራዊ ችግሮችን አሳልፈዋል፡፡ ከእነዚህ ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የባርያ ንግድ ስርዓትና የአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ስርዓቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች ከ16ኛው ክፍለ ዘመን እስከ 20ኛው ክፍለ ዘመን የአፍሪካ ህዝቦችን የእኩልነትና የነፃነት መብቶችን የገፈፉ ናቸው፡፡ የአፍሪካ ህዝቦችን ያለፍላጎታቸው ወደ ሌላ አህጉር እንዲጓዙ በማድረግ አፍሪካ ከፍተኛ ቁጥር ያለውን አምራች ኃይሏን እንድታጣ አድርጓል፡፡ በአጠቃላይ የባርያ ንግድ ስርዓት፣ የአውሮፓውያን ቅኝ አገዛዝ ስርዓት እና ከነፃነት በኋላ ያለውን የአፍሪካ ህዝቦች ምጣኔ ሀብታዊና ፖቲካዊ ሁኔታዎች በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በስፋት ተገጸዋል፡፡

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- በአፍሪካ ህዝቦች ላይ የባርያ ንግድ ስርዓት ያስከተለውን ጉዳት ትገልፃለህ/ሽ
- ከ15ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አፍሪካኖች የባርያ ንግድን ለማስቆም ሲያካሄዱ የነበረውን ተቃውሞ ትገልፃለህ/ሽ
- የፀረ ቅኝ አገዛዝ ስርዓት አመለካከትን ታጎለብታለህ/ሽ
- የአውሮፓ ሀገሮች ከአፍሪካ ውጪ በቅኝ ግዛት የያዙዋቸውን ሀገሮች ትዘረዝራለህ/ሽ
- የአፍሪካ ህዝቦች ነፃነታቸውን ለማግኘት የከፈሉትን መስዋእትነት ትልቅ ዋጋ ትሰጠዋለህ/ጪዋለሽ
- ከነፃነት በኋላ የአፍሪካ ህዝቦችን ምጣኔ ሀብታዊና ፖቲካዊ ሁኔታዎችና የእርስ በእርስ ትስስር ለመፍጠር ያደረጉትን እንቅስቃሴዎች በመረዳት ትልቅ ክብር ትሰጠዋለህ/ጪዋለሽ፡፡

## 5.1. የባሪያ ንግድ ስርዓት

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የባሪያ ንግድ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የባሪያ ንግድ እንዴት እንደ ተጀመረ አስበህ/ሽ ታውቃለህ/ሽ? ካስብክ/ሽ ምን ስታስቡ እንደ ነበረ ለክፍላችሁ አስረዱ
3. የባሪያ ንግድ ያስከተለውን ጉዳት ዘርዝር/ሪ?

ባርነት የሰውን ልጅ በጉልበት ያለፍላጎቱ የተለያዩ አገልግሎቶችን እንዲሰጡ የሚገደድበት አካሄድ ነው። በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ ባርነት መቼና የት እንደ ተጀመረ በግልጽ የሚታወቅ ነገር የለም። ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ማህበራዊ የዕድገትና የለውጥ ታሪክ እንደሚያመለክተው የባረነት አጀማመር ከሰው ልጅ የሀብት ልዩነት መፈጠር ጋር ይያያዛል። ይህ ስርዓትም ጉልበት ያለው ጉልበት የሌለውን አስገድዶ የሚጠቀምበት ስርዓት ነው። እንዲሁም ጉልበት ያለው ቡድን የተወሰነ ቁጥር ያለውንና ደከም ያለውን የህብረተሰብ

ቡድን በጉልበት በማስገደድ ለተለያዩ አግልግሎቶች የሚጠቀምበት አካሄድ ነው።

የሰው ልጅ በባርያ ንግድ ስርዓትና በባርነት ውስጥ በጣም አሰቃቂና አስቸጋሪ የሆነ የህይወት ውጣ ውረዶችን አሳልፏል። በባርያ ንግድ ስርዓት በባርነት የተገዛ ሰው ማንኛውንም የተጠየቀውን አገልግሎት ያለምንም ማንገራገር እንዲፈፅም ይገደዳል።

በባሪያ አስተዳዳሪ ስርዓት ውስጥ የምጣኔ ሐብቱ መሰረት የባሪያ ጉልበት ነው። ባሮችን የሚያስተዳድረው ማንኛውም የባሪያ አስተዳዳሪ ባሪያን እንደ ዕቃ ይጠቀምበታል እንዲሁም ሊሸጠውም ይችላል። በመሆኑም በጥንታዊ ስልጣኔ ዘመን ውስጥ የተለያዩ ስራዎች በአብዛኛው ሲከናወኑ የነበሩት በባሮች ጉልበት ነው።. በዚህ መሰረትም እንደ ጥንታዊ ግሪክ፣ ሮማ፣ ግብጽ፣ ሜሮኤና አክሱም የመሳሰሉት መንግስታት በባሮች ጉልበት ሲጠቀሙ ኖረዋል። እንዲሁም የተለያዩ መሪዎች፣ ነገሥታት፣ ባላባቶችና የሀይማኖት መሪዎች የባሮችን ጉልበት ሲገለገሉበት ቆይዋተል። በዚህን ጊዜ እንደባሪያ ሲቆጠሩ የነበሩ የማህበረሰብ ክፍሎችም በጦርሜዳ ወይም በተለያዩ ግጭቶች የተማረኩ ሰዎች ናቸው። ስለዚህም ባርነት የሰዎችን ጉልበት ያለፍላጎታቸውና በኃይል ጉልበታቸውን ከመጠቀም የመነጨ አካሄድ መሆኑን ያሳያል።



ፎቶግራፍ .5. 1(ሀ) የባሪያ ንግድ ስርዓት ሂደት

## የሙከራ ጥያቄዎች


1. ከዚህ በላይ የሚታየውን ስዕል በጥንቃቄ በመመልከት የተሰማህን/ሽን ስሜት ለክፍል ተማሪዎች አብራራ/ሪ?
2. ከዚህ በላይ እንደሚታየው ባሮች ለምን በአንድ ላይ እንደሚቆራኙ በመወያየት ለክፍል ተማሪዎች ሪፖርት እቅርቡ?

ከላይ እንደተገለጸው በአፍርካ ውስጥ የባሪያ ንግድ ከጂኦግራፊያዊ አሰሳ በፊት ሲካሄድ ነበር። ከዚህ ዘመን በፊት በምስራቅ አፍሪካ ድንበሮች አከባቢና በናይል ሸለቆዎች ውስጥ የባሪያ ንግድ ሲካሄድ ቆይቷል። በዚህም መሰረት ባሮች ወደ መካከለኛው ምስራቅ፣ ህንድና አውሮፓ ሲሸጡ ነበር። ይህ የባርያ ንግድ ሲካሄድበት የነበረው አከባቢ ቀይ ባህር፣ የሜድትራኒያን ባህርና የህንድ ውቅያኖስ ናቸው። ወደ መካከለኛው ምስራቅ ሲሸጡ ከነበሩት ባሮች ውስጥ አብዛኞዎቹም ሴቶች ነበሩ። ምክንያቱም ሴቶች ለቤት ውስጥ ስራና ለተለያዩ አገልግሎቶች ስለሚፈለጉ ነው።

ከአሰሳ ዘመን በኋላ አውሮፓውያኖች በምዕራብ አፍሪካ ድንበር አከባቢዎች ብዙ የባሪያ ንግድ ማዕከላት በግልጽ ማቋቋም ጀምረው ነበር። በዚሁም መሰረት ፖርቹጋል ባሮችን ወደ ሳኦቶሚና ፕሪንሲፔ ደሴቶች በማጓጓዝ ባሮችን ለእርሻ ስራ ትጠቀምባቸው ነበር። እንዲሁም ባሮችን ወደ አውሮፓ መነገድ ጀምራለች።

በ15ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ አከባቢ የአሜሪካ አህጉር መገኘት የባሪያ ንግድን በጣም እንዲስፋፋ አድርጎታል። ምክንያቱም የፖርቹጋልና እስፔን ሰፋፊ የጥጥ፣ የሸንኮራና የትምባሆ እርሻዎችን መጀመራቸው ነው። ይህ ሰፋፊ እርሻ መስፋፋቱ ደግሞ ብዙ የሰው ልጅ ጉልበት አስፈልጎት ነበር። ይህንን የሰው ጉልበት ለሟሟላት ደግሞ ባሮችን በብዛት ከምዕራብ አፍሪካ ወደ አሜሪካ ማጓጓዝ ጀመሩ፡፡ ይህም አካሄድ የባርያ ንግድ በይፋ እንዲጀመር አድርጓል። ይህ የባሪያ ንግድም የአትላንቲክ ውቅያኖስን ተሻጋሪ የንግድ መስመር ፈጥሯል።


የአትላንቲክ ውቅያኖስ ተሻጋሪ የንግድ መስመር የሶስት ማዕዘን የባሪያ ንግድ በመባል ይታወቃል። ምክንያቱም የአፍሪካ፣ አሜሪካና የአውሮፓ አህጉሮችን ስለሚያገናኝ ነው። ይህም የሶስት ማዕዘን የንግድ መስመር ከአፍሪካ ባሮችን ወደ አሜሪካና አከባቢዋ ያጓጉዛል። በሁለተኛው ዙር ደግሞ የእርሻ ውጤቶችን ከአሜሪካ ወደ አውሮፓ የሚያደርስ የንግድ እንቅስቃሴ ነው። በመጨረሻም የተለያዩ የፋብሪካ ምርቶች ከአውሮፓ ወደ አፍሪካ ገበያ የሚያጓጉዝ የንግድ አካሄድ ነው። በዚህ መሰረት የሶስት ማዕዘን የንግድ መስመር ሶስት ዙሮች ያሉት ሲሆን በአፍሪካ ጀምሮ በአፍሪካ የሚጠናቀቅ ነው።




ካርታ 5.1(ለ) የባሪያ ንግድ መስመሮች

ከ15ኛው እስከ 16ኛው ክፍለ ዘመን ፖርቱጋልና እስፔን በከፍተኛ ደረጃ ባሮችን ሲነግዱ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ከ17ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ የዓለም የበላይነት ሚዛን ከፖርቱጋልና ከእስፔን በመውሰድ ወደ እንግሊዝና ፈረንሳይ እንዲዘዋወር አድርጓል። በዚህ መሰረት በ18ኛው ክፍለ ዘመን እንግሊዝ የባሪያ ንግድን በላይነት በመቆጣጠር በሰፊው ስታካሂድ ቆይታለች። በተጨማሪም አውሮፓውያኖች ለአፍሪካኖች የጦር መሳሪያ በማስታጠቅ አፍሪካኖች አፍሪካኖችን አድነው በባርነት እንዲሻሻጡ ግፊት ሲያደርጉ ነበር።

አፍሪካኖች በባርነት ለመሸጥ ከተያዙበት ቦታ ጀምሮ አሜሪካ እስከ ሚደርሱ ድረስ በጣም አስከፊና አሰቃቂ ሁኔታዎችን ያሳልፉ ነበር።. በዚህ መሰረት እጅና እግራቸውን በሰንሰለት በማሰር ማቁሰል፣ በተላላፊ በሽታ መያዝ፣ እራሳቸውን ወደ ባህር በመወርወር መግደልና ምግብ ያለመብላት አድማ በማድረግ ህይወታቸው እንዲያልፍ ሲያደርጉ ነበር።. በስራ ቦታም ቢሆን ብዙ መከራና ግፍ ሲደርስባቸው ቆይቷል። ለምሳሌ በሰንሰለት በማቆራኘትና አካላቸውን በጋለ ብረት በማቃጠል የተለያዩ ምልክቶችን በአካላቸው ላይ መቅረጽ የተለመድ አሰራር ነበር። እንዲሁም ይህንን የተቃወሙና ለመቃወም የሞከሩትን ባሮች ለሌሎች ምሳሌ ይሆኑ ዘንድ አሰቃቂና አስፈሪ እርምጃዎች ይወሰዱባቸው ነበር።



ሥዕል.5.1. (ሐ) በባሮች ላይ ሲወሰዱ የነበሩ እርምጃዎች

የአውሮፓ ሀገራት የባሪያ ንግድን ለሶስት መቶ ዓመታት አከባቢ በማካሄድ ከፍተኛ ሀብት አግኝተውበታል።. ይህ ደግሞ ወደ ካፒታሊስት ስርዓትና እንዱስትሪ አብዮት ለመሸጋገራቸው ምክንያት ሆኗቸዋል። ይሁን እንጂ አፍሪካን አምራች የሆነውን የሰው ኃይል በማሳጣት ለድህነት፣ ለፖለቲካ አለመረጋጋት እና ለማህበራዊ ችግሮች እንድትጋለጥ አድርገዋል። ቀስ በቀስም ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ አውሮፓውያን የአካሄድ ስልታቸውን በመቀየርና የባሪያ ንግድን የተቃወሙ በመምሰል የአፍሪካን ሀብት መዘረፍ ጀምረዋል።

የባሪያ ንግድ ተቃውሞ መሰረቱ ከምጣኔ ሀብት ፍላጎት መቀየር ጋር የተያያዘ ነው። ይህም ከኢንዱስትሪው አብዮት ጋር ተያይዞ በመጡት ለውጦች ምክንያት የሰው ጉልበት ብዙም የማይፈለግ መሆኑና የጥሬ ሐብት አስፈላጊነት መጨመር ነው። በሌላ በኩል ደግሞ የባሪያን ንግድ ተቃውሞዎች በመጨመራቸው የባሪያ ንግድን ለማስቀረት ጉልህ ሚና ተጫውቷል።

አውሮፓዊያኖች በፊት የባሪያ መገኛ የሆነችውን አፍሪካ የማዕድኖች መገኛ ማዕከል እንደሆነች በመገንዘባቸው ፍላጎታችው ሊጨምር ችሏል። እንዲሁም የአፍሪካ አህጉር የፋብሪካ ሽቀጦች መሸጫ ገበያ ማዕከል እንድትሆን ስለተፈለገ የባሪያ ንግድን ለመቃወም ችለዋል።

እንግሊዝ "የባሪያ ንግድን በህጋዊ ንግድ መተካት" የሚለውን አመለካከት አስጀምራለች። ይሁን እንጂ በእጅ አዙር የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብትና ጉልበት በዚሁ በአፍሪካ አህጉር ውስጥ መጠቀም (Exploitation of Africa on the spot) በሚል አመለካከት የቅኝ ግዛትን ማስፋፋት ችላለች።

የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ህዝቦች ላይ ካደረሰው ጉዳቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

- የአፍሪካን ህዝብ ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እንዲቀንስ አድርጓል
- አፍሪካ አምራች የሆነውን የሰው ኃይሏን እንድታጣ በማድረግ ድህነት እንዲስፋፋ አድርጓል
- ሕፃናትን ያለ አሳዳጊና አረጋዊያን ያለጧሪ እንዲቀሩ አድርጓቸዋል
- የሰላም አለመረጋጋት እንዲሁም የእርስ በርስ ጦርነት እንዲስፋፋ ምክንያት ሆኗል
- አድልዖና ጥላቻ በማስፋፋቱ የዘር ማንነትን መሰረት ያደረገ ልዩነት እንዲፈጠር ማድረጉና የመሳሰሉት የባሪያ ንግድ ካደረሰው ጉዳቶች ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በአጠቃላይ የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ህዝቦች ላይ ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና የስነልቦና ጉዳቶችን አድርሶባቸዋል። በአሁኑ ጊዜ አፍሪካ ያለችበት ችግሮች በአብዛኛው የባሪያ ንግድ ያስከተለው ችግር ውጤቶች ናቸው። በተለይ በአፍሪካኖች መካከል ያለውን ግንኙነት በማደከም ጥላችን አስፋፍቷል።

መልመጃ. 5.1.

## I.ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ስጥ/ጪ

1.ከአውሮፓ ሀገራት ውስጥ የባሪያ ንግድን በቅድሚያ የጀመረችው ሀገር ማናት?

2.እንግሊዝ ለምን ፀረ-ባሪያ ንግድ እንቅስቃሴን ደገፈች?

3.የሶስት ማዕዘን የባሪያ ንግድ በየትኛው የአፍሪካ አከባቢ ላይ የበለጠ ጉዳት አደረሰ ?

4.በባሮች ላይ ሲደርስ ከነበረውን አሰቃቂ ጉዳቶች ውስጥ ሶስቱን ፃፍ/ፊ።

5.የባሪያ ንግድ በአፍሪካ ህዝቦች ላይ ያስከተለውን ጉዳት ዘርዝር/ሪ?

## II. አምስት አባለትን ያካተተ ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች የተሰጡትን ጥያቄዎች በመስራት ለክፍል ተማሪያችሁ አቅርቡ

1.የአፍሪካ ካርታን በማንሳት ከ16ኛው እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን የባሪያ ንግድ መስመሮችን የተለያዩ ቀለማት በመቀባት አሳይ/ዪ

2. አንተ/ቺ በምትከተለው/ዪው ሃይማኖት ውስጥ የሰው ልጅን ባሪያ ማድረግ እንዴት እንደሚታይ ለክፍል ጓደኞችህ ግለጽ/ጪ?

3. በኦሮሞ ባህል ውስጥ የሰው ልጅን ለባርነት መጠቀም ለምን እንደማይፈቀድ በአከባቢያችሁ የሚገኙ አረጋዊያንን በመጠየቅ ለክፍል ተማሪያችሁ ግለጽ/ጪ?

## 5.2 የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካ

**የሙከራ ጥያቄዎች**

- የቅኝ ግዛት ስርዓት ማለት ምን ማለት እንደሆነ አጭር ውይይት አድርጉ
- የቅኝ ግዛት ስርዓት እንዲካሄድ ያደረጉ መሰረታዊ ምክንያቶችን በመዘርዘር ውይይት አድርጉ
- የቅኝግዛት ስርዓት በአፍሪካ ውስጥ እንዴት እንደተጀመረ ያላችሁን ግንዛቤ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ
- አራት አባላትን ያካተተ ቡድን በመመስረት የቅኝ ግዛት ስርዓት አስተዳደር ባህርያት ላይ በጥልቀት ተወያዩበት፡፡

ቅኝ ግዛት የሚለው ጽንሰ ሀሳብ ብዙ ትርጉሞች አሉት፡፡ ይሁን እንጂ አብዛኛው ምሁራን እንደሚገልጹት ቅኝ ግዛት ማለት አንድ ሀገር በሌላ ሀገር ላይ ያለው የምጣኔ ሀብታዊና የፖሊቲካዊ የበላይነት ነው በማለት ይገልፃሉ፡፡ በተጨማሪም ቅኝ ግዛት ማለት አንድ ሀገር የሌላውን ሀገር በመቀራመት የተፈጥሮ ሀብቱን በመዝረፍ ለራሱ ጥቅም ማዋል በማለትም ይገልፃሉ፡፡ በዚህ ሁኔታ አንድ ሀገር በሌላ ሀገር ላይ የፖሊቲካ የበላይነት ካለው የራሱን ስርዓት በመዘርጋት የአንድ ሀገር የተፈጥሮ ሀብቱን መቆጣጠር ይጀምራል፡፡ ከዚህ ተቃራኒ ግን በቁጥጥር ሥር የዋሉ ህዝቦች ደግሞ ዴሞክራሲያዊ መቶቻቸምውን ይነፈጋሉ። በአጠቃላይ ቅኝ ግዛት ከላይ በተዘረዘሩት ሀሳቦች ይገለፃል፡፡

### አውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛት የያዙበት ምክንያቶች


አውሮፓውያን አፍሪካን በቅኝ ግዛት እንዲይዙ ካደረጉት መሰረታዊ ምክንያቶች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

- በኢንዱስትሪ አብዮት ምክንያት ለተፈበረኩት የተለያዩ ፋብሪካዎች ጥሬ ዕቃዎችና የተፈጥሮ ሀብት ለመፈለግ ሲባልህ የአፍሪካን የተፈጥሮ ሀብቷን ለመቆጣጠር ማቀድ
- አውሮፓውያን ቀድመው አፍሪካን በቅኝ ግዛት ለመያዝና ግዛታቸውን ለማስፋፋት ማቀዳቸው ነው።

የተለያዩ ፋብሪካዎች መስፋፋት የተለያዩ ማዕድናትን የማግኘት ፍላጎትን ጨምሯል፡፡ ስለዚህ አውሮፓዊያኖች ይህን ፍላጎታቸውን ለሟሟላት ማዕድናት የሚገኙበትን ቦታዎች አሰሳ ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ በዚህ መሰረት ጂኦግራፊያዊ አሳሾችን በመጠቀምና ሀይማኖትን ከለላ በማድረግ በአፍሪካ ላይ አሰሳ በማካሄድ ማዕድናት ያሉበትን ቦታዎች ማረጋገጥ ችለዋል፡፡ በዚህ መሰረት ምጣኔ ሀብታዊ፣ ፖሊቲካዊ እና ማህበራዊና የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካ ሊመሰረት ችሏል፡፡ በአጠቃላይም ከላይ የተጠቀሱት መሰረታዊ ምክንያቶች የቅኝ ግዛት ስርዓት በአፍሪካ ውስጥ በፍጥነት እንዲስፋፋ አድርገዋል፡፡

## አውሮፓውያኖች አፍሪካን በቅኝ የገዙበት ሂደት

በ19ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ የተመቻቹ ሁኔታችን በመጠቀም አውሮፓውያኖች አፍሪካን በቅኝ ግዛት መያዝ ችለዋል፡፡ አውሮፓውያኖች በአፍሪካ መስፈር የጀመሩት የባርያ ንግድ መጀመርን ተከትሎ ነበር፡ ፡ ይሁን እንጂ በ19ኛው ክፍለ ዘመን በቀጥታ የአፍሪካ አህጉር ጫፎች ላይ መስፈር ችለዋል፡፡ ይህ ሰፈራ የተጀመረበት ምክንያት የእርሻ ስራን ለማስፋፋትና የባርያ ጉልበትን ለመጠቀም ታስቦ ነበር፡፡ ነገር ግን በሂደት የአፍሪካውያንን መሬት ለመቀራመት ችለዋል፡፡ ለዚህም ምሳሌ የሚሆኑ የአፍሪካ ሀገሮች እንደ የሴራሊዮን ጫፍ፣ ጋምቢያ፣ ሳኦቶቴሜና ፕሪንሲፔ፣ ጋና፣ ኮትዲቫር እና የደቡብ አፍሪካ ጫፎች ናቸው፡፡ እንዲሁም አልጄሪያ፣ ቱኒዚያ፣ ሞሮኮ እና ግብፅ በቅድሚያ በአውሮፓውያኖች ቁጥጥር ስር ገብተው ነበር፡፡ እነዚህን ማዕከላት እንደመነሻ በመጠቀም ወደ ምዕራብና ደቡብ እንዲሁም በስተ ሰሜን ወደ መካከለኛው አፍሪካ በፍጥነት መስፋፋት ችለዋል፡፡ በዚህ መሰረት አስፈላጊ በሆነበት ቦታ የጦር መሳሪያን በመጠቀም በ1914 አብዛኛውን የአፍሪካዊያኖችን መሬት በእጃቸው አስገብተዋል፡፡




ካርታ 5.3 (ሀ) አፍሪካኖች በአውሮፓውያኖች ቅኝ የተያዙበት ሂደት

## የአፍሪካ ሕዝብ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል

አፍሪካኖች የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎችን ለመከላከል ትላልቅ ትግሎችን አካሂደዋል፡፡ ከእነዚህ ትግሎች ውስጥ ዋናዎቹ፣

- የማሊ(ማንዲንካ)ህዝብ ትግል፣ የጋና (አሻንቲ) ህዝብ ትግል፣ የኢቦ ህዝብ ትግል እና የዙሉ ህዝብ ትግሎች ናቸው
- በተጨማሪም የዛንዚባር፣ የታንጋኒካ እና የግብፅ ህዝቦች ጠንካራ ትግሎችን አካሂደዋል
- የሱዳንና የኢትዮጵያ ህዝቦችም ትላልቅ ትግሎችን አካሂደዋል፡፡

ከአፍሪካ አገሮች የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል መከላከል ኢትዮጵያ በ1896 ባካሄደችው የአደዋ ጦርነት ጣልያንን በማሸነፍ የተሳካላት ሀገር ናት፡፡ ይህ

የኢትዮጵያ ድል ለሌሎች የአፍሪካ ሀገሮችም ጥሩ ተምሳሌት ሊሆን ችሏል፡፡

## የአፍሪካ ሕዝብ ፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል የሚገልፅ ሰንጠረዥ

| ተ.ቁ | ቅኝ ገዢዎች | የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል | የአፍሪካ አገሮች |
|---|---|---|---|
| 1 | ፈረንሳይ | የዎልፍ ህዝብ ትግል | ሴኔጋልና ጋምቢያ |
| 2 | ፈረንሳይ | የቶክሎርና ማንዲንካ ህዝብ ትግል | ማሊ |
| 3 | እንግሊዝ | የአሻንቴ ህዝብ ትግል | ጋና |
| 4 | ጣሊያን | የኢትዮጵያ ህዝብ ትግል | የኢትዮጵያ |
| 5 | ጣሊያን | ያሳኑሲያን ትግል | ሊቢያ |
| 6 | ደች/ሆላንድ/ | የባሱቶና ዙሉ ህዝብ ትግል | ደቡብ አፍሪካ |
| 7 | እንግሊዝ | የዑራቢ ትግል | ግብፅ |
| 8 | እንግሊዝ | የማህዲሰቶች ትግል | ሱዳን |
| 10 | ጀርመን | የማጂማጂ ትግል | ታንጋኒካ |
| 13 | ቤልጂየም | የኮንጎ ህዝብ ትግል | ኮንጎ |
| 15 | እንግሊዝ | የቡጋንዳ ህዝብ ትግል | ሁጋንዳ |
| 16 | እንግሊዝ | የሚዝሩኢ ህዝብ ትግል | ኬንያ |

## የፕሮጀክት ስራ 5.2.

I. አራት አራት አባላት ያሏቸውን ቡድኖች በመመስረት ከዚህ በታች ያሉትን ጥያቄዎች በደንብ በማንበብ አጭር ክርክር አድርጉ

1. የማሊ (መንዲንካ)ና የኢትዮጵያ ህዝቦች ባደረጉት የፀረ-ቅኝ አገዛዝ ትግል ላይ ክርክር አድርጉ

አፍሪካውያን የአውሮፓ ቅኝ ገዥዎችን ለመከላከል ያደረጉት ትግል በተለያዩ ምክንያቶች ሊከሽፉ ችለዋል፡፡ ከእነሱ ውስጥም ዋናውና ትልቁ የአውሮፓውያን ዘመናዊ የጦር አደረጃጀትና የጦር መሣሪያ የበላይነት ማግኘት ነው፡፡ በተጨማሪም የአፍሪካ ህዝቦች አንድነት ማጣት፣ የጦር ልምድ ማነስ እና ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ማጣት ለአፍሪካ ትግል መክሸፍ ዋና ዋና ምክንያቶች ሊሆኑ ችለዋል ፡፡


አውሮፓውያኖች አፍሪካኖችን በቅኝ ከያዙበት ጊዜ በኋላ የተለያዩ የአስተዳደር ስርዓቶችን መስርተዋል፡፡ ለምሳሌ እንግሊዝ በተዘዋዋሪ የአስተዳደር ስርዓትን (Indirect Rule) ስትመሰርት ፈረንሳይ ደግሞ የቀጥተኛ አስተዳደር (Direct Rule) ስርዓትን በመዘርጋት ሲያስተዳድሩ ቆይተዋል፡፡ ተዘዋዋሪ የአስተዳደር ስርዓትን (Indirect Rule) በመመስረት ስራ ላይ ያዋለው እንግሊዛዊው ፍሬድሪክ ሉጋርድ ይባላል፡፡ ተዘዋዋሪ የአስተዳደር ስርዓት የስልጣን የበላይነትን በመቆጣጠርና እንዲሁም የአፍሪካን አመራሮችን(የጎሳ አለቆችን) በመጠቀም አድልአዊ፣ ኢፍትሀዊ ያልሆነ እና የሰው ልጅ መብትን የሚጋፋ ስርዓት ሲያካሂዱ ቆይተዋል፡፡ የእንግሊዝን ተዘዋዋሪ የአስተዳደር ስርዓትን (Indirect Rule) ሌሎችም የተወሰኑ ሀገራት ሲጠቀሙበት ቆይተዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ ቀጥተኛ የአስተዳደር ስርዓትን (Direct Rule) በመመስረት ስራ ላይ ያዋለው ፈረንሳያዊው አልበርት ሳርውት ይባላል፡፡ በቀጥተኛ የአስተዳደር ስርዓት ውስጥ በቀጥታ ፈረንሳይ የስልጣን የበላይነትን በመቆጣጠር ትታወቃለች፡፡ በዚህ መሰረት ፈረንሳይ በቅኝ የያዘቻቸውን የአፍሪካ ሀገሮች በሙሉ የፈረንሳይ ዜግነት እንዲያገኙ

በማድረግና በፈረንሳይ ህግ እንዲተዳደሩ ትልቅ ጫና አድረጋለች፡ ፡ በመሆኑም በፈረንሳይ ቅኝ ግዛት ስር ያሉ የአፍሪካ ሀገሮች በሂደት ባህላቸውንና ቋንቋቸውን እንዲዘነጉ ተደርጓል፡፡ በአጠቃላይ በቀጥተኛና በተዘዋዋሪው የአስተዳደር ስርዓቶች ዘመን አውሮፓውያኖች የአፍሪካ ሀገሮችን ለማስተዳደር ህጎችን የሚያረቁት እንዲሁም የሚያስወስኑ በአውሮፓ ፓርላማ ነበር፡፡

በቅኝ ግዛት የአስተዳደር ስርዓት ዘመን ብዙ የተለያዩ ጉዳቶች በአፍሪካ ህዝቦች ላይ ደርሰዋል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ፤

- የዴሞክራሲ መብቶች በመጣሳቸው የተነሳ አፍሪካኖች ማንነታቸውን እንዲዘነጉ ተፅዕኖ ማድረጉ፤
- የተፈጥሮ ሀብት ዘረፋ ማከሄድ ለምሳሌ የተለያዩ ማዕድናትን መዝርፍ
- በዴሞክራሲያዊ መብት ጥሰት ምክንያት የአፍሪካ ህዝቦች ፖሊቲካዊና ሰብአዊ መብቶችን እንዲያጡ ተደርጓል፡፡ እንዲሁም የመምረጥና የመመረጥን መብት፣ ከቦታ ቦታ የመንቀሳቀስ መብት፣ የመደራጀት መብት እና ሀብት/ንብረት የማፍራት መብቶችን ተነፍገዋል፡፡




ካርታ. 5.2. (ለ) በአውሮፓኖች ቅኝ የተገዙ የአፍሪካ ሀገሮችን የሚያሳይ ካርታ

## መልመጃ. 5.2.

### ከዚህ በታች ለተዘረዘሩት ጥያቄዎች አጫጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. የአውሮፓ ሀገሮች አፍሪካን ቅኝ ለመግዛት የሄዱበት ሂደት በቅደም ተከተል ዘርዝር/ሪ
2. የአፍሪካን ካርታ በማንሳት በአውሮፓ ሀገሮች ቅኝ የተገዙትን የአፍሪካ ሀገሮችን የተለያዩ ቀለማትን በመቀባት አሳይ/ዩ
3. የአውሮፓ ሀገሮች ቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካውያኖች ላይ ያደረሰውን ጉዳቶች ግለፅ/ጪ

# 5.3 የአፍሪካ ህዝቦች ከነፃነት በኋላ ያጎለበቱት ፖሊቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር

## 5.3.1 የአፍሪካ ህዝቦች ነፃነት

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. 5.3 (ለ) ላይ ያለውን ካርታ በመጠቀም ብዙና አነስተኛ የቅኝ ግዛት ያላቸውን የአውሮፓ ሀገሮችን በማነፃፀር አገናዝብ/ቢ.
2. ለአፍሪካ ሀገሮች ነፃ መውጣት ዋና ዋና ምክንያቶችን በመለየት ከተወያያቹበት በኋላ ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ
3. የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነት ሂደት ላይ አጭር ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

በ1950ዎቹ ውስጥ ብዙ የአፍሪካ ሀገራት ከአውሮፓውያኖች የቅኝ አገዛዝ ስርዓት ስር ነፃ መውጣት ጀምረዋል፡፡ ለአፍሪካ ሀገሮች ነፃ መውጣት ዋና ዋና ምክንያቶች የሚከተሉት ናቸው፤

- ሁለተኛው የዓለም ጦርነት
- የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ
- የፖሊቲካ ድርጅቶች መመስረት እና በዓለም ላይ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሚዛን ለውጦች መምጣት ናቸው፡፡

### ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያበረከተው አስተዋጽዖ

ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የአፍሪካ ሀገሮችን ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ግንዛቤን እንዲያጎለብቱ አድርጓል፡፡ እንደ ጋና፣ ሴኔጋል፣ ደቡብ አፍሪካ፣ አንጎላ እና አልጄሪያ ያሉት የአፍሪካ ሀገራት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በቀጥታ በመሳተፋቸው ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና የተዋጊነት ግንዛቤን እንዲያገኙ ረድቷቸዋል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንት የአውሮፓውያኖች ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና የጦር ኃይል ብቃታቸው እየተዳከመ በመሄዱ የአፍሪካ ሀገሮችን ማስተዳደር አልቻሉም፡፡ እንዲሁም እንደ

ራሽያና አሜሪካ ያሉት ሀገሮች የቅኝ አገዛዝ ስርዓትን በመቃወም በቅኝ አገዛዝ ሥር ያሉትን የአፍሪካ ሀገሮች በመደገፍ ትልቅ ጉለበት ሆነዋቸዋል፡፡ ስለዚህ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ለአፍሪካ ሀገሮች ነፃነት ትልቅ አስተዋጽዖ አበርክቷል፡፡

## የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴና የፖሊቲካ ድርጅቶች መመስረት

በ1920ዎቹ ውስጥ የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ በጥቁር አሜሪካኖች በሰሜን አሜሪካ ተመሰረተ፡፡ ይህ ድርጅት የተመሰረተው ጥቁር አሜሪካኖች ከባርነት ነፃ ከወጡ በኋላ መብታቸውን ለማስከበር ታስቦ ነው፡፡ ከ1945 ዓ.ም በኋላ ግን የፓን አፍሪካኒዝም እንቅስቃሴ ወደ አፍሪካ በመግባትና የፖሊቲካ ድርጅቶችን በመመስረት ለአፍሪካኖች ግንዛቤ መፍጠር ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የአፍሪካ ሀገሮችም የራሳቸውን የፖሊቲካ ድርጅት በመመስረት የነፃነት ትግላቸውን መምራት ችለዋል፡፡ በተጨማሪም የአፍሪካ አንድነት ድርጅትና የደቡብ፣ የምዕራብና የሰሜን ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ማህበሮች መመስረት ችለዋል፡፡ እነዚህ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ማህበሮች የአፍሪካውያን የነፃነት ትግልን በመቀላቀል ለአፍሪካውያን ነፃነት ትልቅ ሚና ተጫውተዋል፡፡

### የዓለም ፖለቲካዊ ሚዛን ለውጦች

በ20ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ የዓለም ፖለቲካዊ ሚዛን ከአውሮፓውያኖች ወደ ራሽያና አሜሪካ ሊያዘንበል ችሏል፡፡ ይህ ደግሞ ከ1950ዎቹ በኋላ የአውሮፓውያን የቅኝ አገዛዝ ስርዓት እንዲናቅና እንዲጥላላ ማድረግ ችሏል፡፡

## 5.3.2 ከቅኝ አገዛዝ ስርዓት በኋላ የአፍሪካ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የቅኝ አገዛዝ ስርዓት በአፍሪካውያኖች ላይ የፈጠረውን ጠባሳ ተወያዩበት
2. የአፍሪካውያኖች አለመግባባትና መከፋፈል ለቅኝ አገዛዝ ስርዓት ያበረከተውን ጥቅምና ጉዳት አስመልክቶ ክርክር አድርጉ
3. ከቅኝ አገዛዝ ስርዓት በኋላ የአፍሪካ ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች ምን እንደሚመስሉ ዘገባ በማዘጋጀት ለክፍል ተማሪዎች አቅርቡ፡፡

ከ1960ዎች በኋላ የአፍሪካውያኖች ፖለቲካዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታዎች በከፍተኛ ደረጃ ሊለወጥ ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የምጣኔ ሀብት ጥገኝነት፣ የማህበራዊ ችግሮች፣ መፈንቅለ መንግስት እና የእርስ በእርስ ጦርነት መስፋፋት ናቸው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ከአውሮፓውያኖች ተፅዕኖ ነፃ የሆነ ፖለቲካ ባይኖርም ብዙ የአፍሪካ ድርጅቶች ተመስርተዋል፡፡ ከእነሱም ውስጥ አንዱ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሲሆን ሌሎቹ ደግሞ አከባቢያዊ ድርጅቶች ናቸው፡፡ ከላይ የተጠቀሱት ድርጅቶች እንደሚከተለው ተገልጸዋል፤

### የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ግንቦት 1963 ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ ሊመሠረት ችሏል፡፡ በተለይ የሃሳብ ልዩነቶች መፈጠር ለተለያዩ ቡድኖች መመስረት ምክንያት ሆኗል፡፡ እነዚህ ቡድኖችም እንደሚከተለው ተዘርዝሯል፤

- የካሳብላንካ ቡድን፤ ጋና፣ጊኒ፣ አልጄሪያ፣ ግብፅ፣ ሞሮኮ እና ማሊ ናቸው
- የብራዛቪል ቡድን፤ ሴኔጋል፣ ሞሪታኒያ፣ አይቮሪኮስት፣ ኮንጎ፣ ጋቦን፣ ኒጀር፣ ቮልታ፣ ዳሆሜ፣ ቻድ፣ ካሜሮን እና የመካከለኛው አፍሪካ ሪፐብሊክ ያካትታል
- የሞኖሮቪያ ቡድን አባላት ደግሞ ኢትዮጵያ፣ ላይቤሪያ፣ ሊቢያ፣ ናይጄሪያ እና የመሳሰሉት ነበሩ፡፡

የካሳብላንካ ቡድን ሁሉም የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ እንዲወጡ እና ህብረት

እንዲመሠርቱ የሚል አቋም ያለው ሲሆን የብራዛቪል ቡድን ደግሞ የአፍሪካ ሀገሮች ለተወሰነ ጊዜያት ከቀኝ ገዥዎች ጋር የኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ግንኙነት እንዲቀጥል የሚፈልግ ቡድን ነበር፡፡

ሦስተኛው ቡድን ደግሞ የሞኖርቪያ ቡድን ሲሆን አስታራቂ ሃሳብ ያለውና ለጊዜው የተለያዩ የአፍሪካ ሀገሮችን ፍላጎት የሆነው ህብረት ሳይሆን አንድነት መመስረት የሚለው ሃሳብ ያቀፈ ነበር፡፡ በዚህ የሶስተኛው ቡድን ሀሳብ ላይ በመመስረት የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ግንቦት 1963 በፊንፊኔ ከተማ ሊመሰረት ችሏል፡፡



ሥዕል 5.4 የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፅ/ቤት

## የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዋና ዋና ዓላማዎች

- በአፍሪካ ውስጥ ሰላምና መረጋጋት ማስጠበቅ፣ የአፍሪካ ሀገሮች ግጭትን በውይይት መፍታት፣ ቅኝ ግዛትን ማጥፋት እና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡
- እንዲሁም በአፍሪካ ሀገሮች መካካል የፖለቲካ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና የባህል ትስስር መፍጠር እንዲሆም ዘመናዊ የሳይንስ፣ ትምህርት እና ቴክኖሎጂዎችን ማስፋፋት ናቸው፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ዓላማ ከግብ ለማድረስ አራት መዋቅሮች

ተመስርተዋል፡፡ እነሱም ጠቅላላለ ጉባኤ ፣ የሚኒስተሮች ምክር ቤት፣ የአፍሪካ አንድነት የሠላም ኮሚሽን እና የፀሐፊዎች ምክር ቤት ናቸው፡ ፡ በተጨማሪም መንግስታዊ ያልሆኑ የተለያዩ የኮሚሽኖች መዋቅሮችን በውስጡ ያካትታል፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ጠቅላላለ ጉባኤ በዓመት አንድ ጊዜ የሚሰበሰብ እና ሁሉም የአባል ሃገራት መሪዎች የሚሳተፉበት ነው፡፡ የሚኒስተሮች ምክር ቤት ሁለተኛው መዋቅር ሲሆን የአባል ሀገራት የውጭ ጉዳይ ሚኒስተሮች የሚሳተፉበት ነው ፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፀሃፊዎች የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ሠራተኞች ሲሆኑ ይህ መዋቅር የአፍሪካ አንድነት ድርጅን በበላይነት ይመራል፡፡ የመጀመሪያ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ፀሀፊ ኢትዮጰያዊው ዶክተር ክፍሌ ወዳጆ ነበር፡፡ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት የሠላም እና አማካሪ ጠቅላላ ጉባኤ ሰላምና መረጋገት ላይ የሚሰራ መዋቅር ነው፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ትላልቅ ስኬቶችንና ችግሮችን አሳልፏል፡፡ ስኬት ከሚባሉት ውስጥ የቀኝ ግዛት ስርዓትን ማጥፋት፣ የዘር መድሎ መቀነስ፣ አፓርታይድን ማጥፋት፣ የነፃነት ታጋዮችን ማበረታታት እና በአፍሪካ ሀገሮች መካከል የነበረውን የድንበር ችግሮችን መፍታት ናቸው፡ ፡ በዚህ መሰረት በኢትጵያ፣ በሶማሊያ እና በኬኒያ መካከል የነበሩትን የድንበር ግጭቶች እንዲሁም በሞሮኮና በአልጀሪያ መካከላቸው ያለውን ግጭት መፍታት ችሏል፡፡

የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ችግሮች ከአለም አቀፍ ችግሮች ጋር የተያያዘ ቢሆንም ዋናው ችግሩ ግን የድርጅቱ ድክመት ነው፡፡ እነሱም የራሱ ቋሚ የጦር ኃይል አለመኖር፣ ድህነት መቀነስ አለመቻል፣ የሀገሮች ግንኙነት መላላት፣ ስደት መስፋፋት እና የተለዩ በሽታዎችን መቀነስ አለመቻሉ ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ድርጅት በበለጠ እንዲጠናከርና መሠረታዊ ለውጥ እንዲያመጣ ተብሎ በ53 አባል ሀገሮች ተወካይ አማካኝነት በተካሄደው ስብሰባ የአፍሪካ አንድነት ድርጅት ወደ አፍሪካ ህብረት በ2002 ዓ.ም ተቀይሮ በመስራት ላይ ይገኛል፡፡

## የተለያዩ የአፍሪካ አከባቢያዊ ድርጅቶች

የአፍሪካ ሀገሮች ከነፃነት በኋላ በሁሉም የአፍሪካ አካባቢዎች የተለያዩ ድርጅቶችን አቋቁመዋል፡፡ በዚህ መሰረት በምዕራብ አፍሪካ ፣ በሰሜን ምስራቅ አፍሪካ፣ በደቡብ ምስራቅ አፍሪካ የማህበራዊ፣ ምጣኔ ሀብታዊ እና ፖለቲካዊ ድርጅቶች ተመስርተዋል፡፡ እነዚህ ድርጅቶች የተለያዩ አገልግሎቶችን እና አላማዎችን አካተዋል፡፡ የተቋቋሙ ድርጅቶችም እንደሚከተለው ተዘርዝረዋል፤

- የምዕራብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበር (ECOWS)፤ ይህ ማህበር በ1975 በናይጄሪያ በሌጎስ ስምምነት በ15 አባል ሀገራት ተመሰረተ፡፡ የዚህ ድርጅት ዋና ዓላማ በምዕራብ አፍሪካ ሀገሮች መካካል ጠንካራ ምጣኔ ሀብታዊ ትስስር መፍጠር ነው፡፡ ይህ ድርጅት ከምጣኔ ሀብታዊ ትስስር በተጨማሪ የአካባቢውን ሰላም ለማስጠበቅ አትኩሮ ሲሰራ ቆይቷል፡ ፡ ከ1990 ጀምሮ ደግሞ የአባል ሀገሮች ጦርነት ያለመፈለግ ስምምነት ፈጥሯል፡፡ በተጨማሪም ግጭቶችን በሰላም መንገድ ለመፍታት የሚቻልበትን መንገድና ችግሮች በአባል ሀገሮች መካካል እንዳይፈጠሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት የሚለው ላይ ተስማምተዋል፡፡
- የምስራቅ አፍሪካ በየነ መንግስታት (IGADD)፤ የተመሰረተው በ1986 በጅቡቲ ከተማ ነው፡፡ የምስራቅ አፍሪካ በየነ መንግስታት ማለት የአፍሪካ ቀንድ ሀገሮች ቅድሚያ ለልማት ማህበር የሚል ነው፡፡ ይህ ምህፃረ ቃል በሂደት በ1996 ወደ (IGAD)ተቀይሯል፡፡ የዚህ ድርጅት ዓላማ ፖለቲካዊ፣ ሰብዓዊ፣ ማህበራዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ትስስርና ልማት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ የዚህ ድርጅት አባል ሀገራት ኢትዮጵያ፣ ጁቡቲ፣ ኬኒያ፣ ሱማሊያ፣ ሱዳን እና ኡገንዳ ናቸው፡፡
- የደቡብ አፍሪካ አገሮች የልማት ኮሚሽን (SADC)፤ የዚህ ድርጅት ዋና አላማው ልማትና ዕድገት በደቡብ አፍሪካ ሀገሮች መካከል ማጠናከር ነው፡፡ ይህ ድርጅት 16 አባል ሀገራትን በውስጡ ያከተተ ነው፡፡
- የምስራቅ ደቡብ አፍሪካ ሀገሮች የጋራ ገበያ (ECOWS)፤ የተመሰረተው በ1993 ዓ.ም በኡጋንዳ ዋና ከታመ ካምፓላ ነው፡፡ ይህ ድርጅት

ኢትዮጵያን ጨምሮ 20 አባል ሀገራትን ያቀፈ ነው፡፡

- በሰሜን አፍሪካ ከተመሰረቱት ድርጅቶች ውስጥ ታዋቂው የአረቦች ሊግ ነው፡፡ የዚህ ድርጅት አባል ሀገራት ብዙዎቹ የአረብኛ ቋንቋን የሚጠቀሙና የመካከለኛው ምስራቅ ሀገሮችን የካተተ ነው፡፡ መስራች ሀገሮች አራት ሲሆኑ በጊዜ ሂደት ብዙ ሀገሮች ይህንን ድርጅት ሊቀላቀሉ ችለዋል፡፡ የዚህ ድርጅት ዋና አላማ የሰሜን አፍሪካ ሀገሮችን ግንኙነት፣ ልማትና ምጣኔ ሀብትን ማጠናከር ላይ ያተኮር ነው፡፡ ይህን ድርጅት ለመመስረት ትልቁን ሚና የተጫወተችው ግብፅ ስትሆን የዚህ ድርጅት ዋና መቀመጫው የግብፅ ዋና ከተማ ካይሮ ነው፡፡

## የፕሮጀክት ስራ 5.3

ከ8-10 አባላት ያሉት ቡድን በመመስረት ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ድርጅቶች ዓላማና የተመሰረቱበትን ዓመተ ምህረት ከተለያዩ የመረጃ ምንጮች በማሰባሰብ በዘገባ መልክ ለክፍል ተማሪዎች አቀረቡ፡፡

- የድርጅቶቹ ስም IGAD, ECOWS እና COMESA ናቸው፡፡

## ማጠቃለያ

ከ1500 ክፍለ ዘመን በፊት አውሮፓውያኖች የአፍሪካን አህጉር እንደ ጨለማ አህጉር እና የማይታወቅ አህጉር አድረገ ይቆጥሩ ነበር፡፡ ምክንያቱም በአውሮፓ አህጉር አከባቢ ያሉትን ጫፎች፣ ውቅያኖስ እና ባህር ውጭ ያለውን አህጉር አያውቁትም ነበር፡፡ ይሁን እንጂ ከ16ኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ በኋላ የባህር ላይ አሳሾች መምጣት ለባርያ ንግድ መጀመር ምክንያት ሆኗል፡፡ በዚህ መሰረት "አፍሪካ የጨለማ አህጉር" የሚለው ሃሳብ በመተው "በተፈጥሮ ሀብት የበለፀገች" ወደሚለው ሀሳብ ቀይረዋል፡፡

በዚህ ምክንያት የባሪያ ንግድ ለሦስት ክፍለ ዘመናት ተጠናክሮ በመካሄድ የአፍሪካ ህዝቦችን ወደ አውሮፓና አሜሪካ በባርነት እንዲሸጡ አድርጓል፡ ፡ በዚህ መሰረት በአሜሪካ ለሸንኮራ አገዳ ምርት፣ ለጥጥ ምርት እና ለሻይ ቅጠል ምርት አፍሪካውያኖች በባርነት ወደ አሜርካ ሲጓዙ ቆይተዋል፡፡ ወደ አፍሪካ ደግሞ የጦር መሣሪያን፣ የአልኮል መጠጥ እና ጨርቃጨርቆችን በማስገባት ሲሸጡ ቆይተዋል፡፡

በ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ አካባቢ የኢንዱስትሪ አብዮት በመስፋፋቱ ምክንያት የአውሮፓውያኖች ፍላጎት ሊቀይር ችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የባሪያ ንግድ እንዲቆም ከፍተኛ አስተዋጽዖ አድርጓል ፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ለኢንዱስትሪዎች ግብዓት የሚሆኑ ጥሬ ዕቃና ገበያ ፍለጋ ላይ አውሮፓውያን እንዲያተኩሩ አድርጓል፡፡ ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት በኋላ የፖለቲካ ሚዛን መቀየር በቀኝ ግዛት ስር ያሉ ሀገሮች ነፃነታቸው እንዲቀዳጁ አድርጓል ፡፡

በተጨማሪም የነፃነት ትግል በአፍሪካ ውስጥ መስፋፋት የአፍሪካ ሀገሮች ነፃነት እንፋጠን አድርጓል ፡፡ በዚህ ሁኔታ ከ1960 ዓ.ም ጀምሮ የአፍሪካ ሀገሮች ነፃ መውጣት ችሏል፡፡ይህ ደግሞ 1960 የአፍሪካኖች ዘመን በመባል ይታወቃል፡፡

## የምዕራፍ አምስት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

### I. ከዚህ በታች ያሉትን ዓ.ነገሮች ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ሐሰት በማለት መልስ/ሺ

1. የባሪያ ንግድ የአፍሪካ ህዝብ ላይ ከፍተኛ ጉዳት አስከትሏል
2. በ18ኛው ክፍለ ዘመን የባሪያ ንግድን በበላይነት ተቆጣጥረው የነበሩት እስፔኖች ናቸው
3. በቅኝ ግዛት ዘመን አውሮፓውያኖች የአፍሪካን ሀብት ዘርፈዋል
4. ለመጀመሪያ ጊዜ የአፍሪካን አህጉር በቅኝ ግዛት የያዘችው ሀገር ጣልያን ነች
5. ከአፍሪካ ሀገሮች የፀረ- ቅኝ ግዛት ትግል ስኬታማ የሆነችው ኢትዮጵያ ብቻ ናት፡፡

### II. ከዚህ በታች ላሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

1. ከአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች ውስጥ አብዞቹን የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት የያዘችው የቷ ናት?
   ሀ. ፈረንሳይ  ለ. እንግሊዝ  ሐ. ፖርቹጓል
   መ. ጣሊያን
2. የበርሊን ስምምነት አላማ ምንድ ነው?
   ሀ. አፍሪካን ማልማት  ሐ. የባሪያ ንግድ ለማስፋፋት መወሰን
   ለ. አፍሪካን መከፋፈል  መ. የአፍሪካ ሀገሮች ወሰን መለየት
3. አፍሪካን በቀኝ ግዛት ለመግዛት ዝቅተኛ ተሳትፎ ያደረገችው ሀገር ማናት?
   ሀ. እስፔን  ለ. ፈረንሳይ  ሐ. ጀርመን  መ. ጣሊያን
4. የምዕራብ አፍሪካ ኢኮኖሚን ለማጠናከር የተመሰረተው ማህበር የቱ ነው?
   ሀ. የምስራቅ አፍሪካ በየነ መንግስታት (IGAD)
   ለ. የምዕራብ አፍሪካ የኢኮኖሚ ማህበር (ECOWS)
   ሐ. የምስራቅና ደቡብ አፍሪካ ሀገሮች የጋራ ገበያ (COMESA
   መ. የደቡብ አፍሪካ አገሮች የልማት ኮሚሽን (SADC)

5. የካሳብላንካ ቡድን በተመለከተ ትክክል የሆነው የቱ ነው?

ሀ. ከነፃነት በኋላ የአፍሪካ ሀገሮችን ማዋሃድና ጠንካራ መንግስት መመስረት

ለ. ለጊዜው ከቀኝ ገዢዎች ጋር ያለውን ግንኙነት ማስቀጠል

ሐ. ለጊዜው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት መመስረት

መ. መልስ አልተሰጠም

## III-አጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. ከምስራቅ አፍሪካ ሀገሮች ውስጥ በእንግሊዝ ቅኝ ግዛት ስር ከነበሩት ውስጥ ሦስቱን ፃፍ/ፊ
2. ከነፃነት በኋላ በአፍሪካ ሀገሮች ውስጥ ካሉት ችግሮች ውስጥ ሦስቱን ፃፉ/ፊ
3. ከሰሜን አፍሪካ ሀገራት ውስጥ የፈረንሳይ ቅኝ ግዛት የነበሩት ስንት ናቸው? ከእነሱ ውስጥ ሁነቱን ፃፉ
4. የምስራቅ አፍሪካ በየነ መንግስታት (IGAD) መቀመጫ የት ይገኛል?
5. 1960 ለምን የአፍሪካውያን ዘመን ተባለ?

# ምዕራፍ 6

# ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ

## ከዚህ ምዕራፍ የሚጠበቁ የትምህርቱ ውጤቶች፤

- ✓ ዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት አመሰራረት ትገነዘባለህ/ሽ፣
- ✓ የኢትዮጵያን ካርታ በማዘጋጀት በካረታው ላይ የረጅም ርቀት የንግድ መስመሮችን ታሳያልህ/ሽ፣
- ✓ የኢትዮጵያን ሉዓላዊነት ለማስከብር የተደረጉትን ትግሎች በማክበር ዋጋ ትሰጠዋለህ/ሽ፣
- ✓ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ታብራራለህ/ሽ።

### መግቢያ

ዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ ከ1855 ዓ.ም እ.አ.አ ጀምሮ ያለው ታሪክ ነው። ከዚህ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ያሉት ዘመናት ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ በመባል ይታወቃል። የዚህ ዘመን ታሪክ በአብዛኛው አንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግስት ለመመስረትና የውጭ ጠላቶችን ለመከላከል ካለው ውጣ ውረድ ጋር የተያያዘ ነው። ከትላልቅ የውጭ መንግስታት ማለትም እንደ ሱዳን፣ ጣልያን፣ ግብፅና ሶማሊያ ካሉት ጋር ግጭት የበዛበት ጊዜ ነበር። በመሆኑም ከነዚህ የውጭ ኃይሎች ጋር ትላልቅ ትግሎች የተደረጉበትና የተሳካ መከላከል የተመዘገበበት ዘመን ነው።

## 6.1. ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክና የመንግሥት አመሰራረት

**ተማሪዎች ቢያንስ ሊኖራቸው የሚገባቸው የትምህርት ብቃት፤**

- ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ መንግሥት አመሰራረትን ታብራራለህ/ሽ
- የኢትዮጵያን የረጅም ርቀት የንግድ መስመር በካርታ ላይ ታሳያለህ/ሽ
- በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነትን ትገልፃለህ/ሽ
- የኢትዮጵያ ህዝቦች የአገሪቱን ሉዓላዊነት ለማስከበር የከፈሉትን መስዋትነት ትገነዘባለህ/ሽ።

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ቀደም ብሎ ይጠራበት የነበርው ስም ማን ነው?
2. ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ወደ ስልጣን የመጣበት አካሄድ ምን እንደሚመስል ተወያዩበት?
3. ዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት አመሰራረት ውጣ ውረዶች የሚያሳዩ ክስተቶች ምን ምን ናቸው? በቡድን ተውያዩበት
4. ከ1855 ዓ.ም በፊትና ከ1868 ዓ.ም በኋላ ያለውን ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሐብታዊና ማህበረሰባዊ አወቃቀሮችን በማነፃፀር ተገንዘቡ።

### ሀ/ ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክና የመንግሥት አመሰራረት

ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት መመስረት ጅማሮ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን ቀደም ብሎ ሲሆን ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ በኋላ ግን ተጠናክሮ ሊካሄድ ችሏል። የኢትዮጵያ የመካከለኛው ክፍለ ዘመን መንግሥታት በአብዛኛው ቋሚ የሆነ ማዕከል አልነበራቸውም። በመሆኑም ከቦታ ቦታ በመዘዋወር የተለያዩ ጊዜያዊ ቤተመንግስታትን በመመስረት ያስተዳድሩ ነበር። በሌላ በኩል ደግሞ በደቡብ-ምዕራብና በደቡብ ኢትዮጵያ ያሉ ህዘቦች ማለትም እንደ አምስቱ የጊቤ መንግሥታት፣ ሌቃ-ቄለምና ሌቃ-ነቀምቴ

ያሉ መንግሥታት እራሳቸውን ችለው ይተዳደሩ ነበር። እንዲሁም ከፋና ወለይታ የመሳሰሉትም በራሳቸው መንግሥታት ሲተዳደሩ ነበር።

ዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት በግልፅ መመስረ የተጀመረው በዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን ነው። የዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ የቀድሞ ስሙ ካሳ ሐይሉ ይባላል፡፡ ከ1840ዎቹ ጀምሮ ካሳ ሐይሉ ኃይሉን ለማጠናከር የተለያዩ የክልል የጦር አለቆችን በውጊያ በቁጥጥሩ ስር ማድረግ ችሏል።. በተለይም በጎንደር መንግሥት ውስጥ ያሉትን ታዋቂ የጦር አለቆች ውስጥ እንደ ደጃች ጎሹ፣ ብሩና ውቤ የመሳሰሉትን ማሸነፉ እንዲፈራ አድርጎታል። በመጨረሻም የየጁ ንጉሥ የነበረውን ዳግማዊ ራስ አሊና የሸዋ ንጉሥ የሆነውን ዳግማዊ ሚኒሊክን በመማረክ ወደ ስልጣን ሊመጣ ችሏል።ዳግማዊው ንጉስ ቴዎድሮስ የተለያዩ ታዋቂ የጦር አበጋዞችን በተለያየ ጦር ሜዳ ድል የተቅዳጀበትን ክስተት ባጭሩ እንደሚከተለው ቀርቧል።

ሰንጠረዥ 6.1. ዳግማዊ አፄቴዎድሮስ የተለያዩ የጦር አለቆችን ያሸነፈበት ጦር ሜዳዎች

| ውጊያ የተካሄደበት ዓመት | ጦር ሜዳዎች | ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ጋር የተካሄደበት ውጊያ | የጦርነቱ አሸናፊ |
|---|---|---|---|
| በ1852 | ጉራ አምባ | ራስ ጎሹ ዘውዴ | ካሳ ሐይሉ (ዳግማዊ አፄቴዎድሮስ) |
| በ1853 | ጎርጎራ ቢቸን | የዳግማዊው ራስ አሊ ታዋቂ አራት ራሶች | ካሳ ሐይሉ (ዳግማዊ አፄቴዎድሮስ) |
| በ1853 | አይሻል | ዳግማዊ ራስ አሊ | ካሳ ሐይሉ (ዳግማዊ አፄቴዎድሮስ) |
| በ1855 | ደረስጌ | ደጃች ውቤ | ካሳ ሐይሉ (ዳግማዊ አፄቴዎድሮስ) |

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ወደ ስልጣን ከመጣ በኋላ ብዙ ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊና ማህበረሰባዊ ተሓድሶዎችን አድርጓል ። በፖለቲካው ዘርፍ አንድ ጠንካራ ማዕከላዊ መንግሥት ለመመስረት ትልቅ እንቅስቃሴ አድርጓል። በተመሳሳይ ሁኔታም የተለያዩትን የክልል አለቆችን ስልጣናቸውን በመግፈፍ በአንድ ንጉሥ ስር እንዲተዳደሩ አውጇል። በአጠቃላይም እሱ ያደረገው

ፖለቲካዊ ተሓድሶ ማዕከላዊ መንግስቱን ያጠናከረ ነበር።. በመሆኑም ይህ ፖለቲካዊ ተሓድሶ ሙሉ በሙሉ አንድ ማዕከላዊ አስተዳደር ያለው መንግሥት መመስረት ላይ ያተኮረ ነበር።

በተመሳሳይ ሁኔታም በማህበራዊና የተቀናጀ የመከላከያ ኃይል መመስረት በተመለከተም ብዙ ተሓድሶ ለማድረግ ሞክሯል። የተቀናጀ የጦር ኃይል መመስረትና ዘመናዊ የጦር መሳሪያ ለማስታጠቅ ትልቅ እንቅስቃሴ አድርጓል።ይህንንም ዓላማ ለማሳካትና የጦር ኃይሉን ለማዘመን ከአውሮፓዊያን ጋር ዲፕሎማሳዊ ግንኙነት ለመመስረት ሞክሮ ነበር። በዚህ መሰረትም በኢትዮጵያ ውስጥ ዘመናዊ ጦር መሳሪያ ለማምረት ትልቅ ሙከራ አድርጓል።



የሴፐስታፖል መድፍ

በመጨረሻም ጋፋት በሚባል ቦታ የዘመናዊ ጦር መሳሪያ ማምረቻ ማዕከል መስርቶ ነበር። ይህ ማዕከልም ሴፐስታፖል የሚባል መድፍ ሲያመርት በተጨማሪም ሌሎች ትናንሽ የጦር መሳሪያዎችን ማምረት ችሏል። ይሁን እንጂ ብቃት በሌላቸው ሰዎች ስለተሰራ ምርቱም ይሁን ማዕከሉ ውጤታማና የተሳካ አልነበሩም። .

በማህበራዊ ጉዳዮች የተደረገው ተሓድሶ የባሪያ ንግድን የማስቆምና ማህበረሰቡ በሽፍታና የታጠቁ ኃይሎች እንዳይዘረፍና እንዳይንገላታ ለማድረግ ተሞክሮአል። እንዲሁም ማህበረሰቡ ሁሉ ስራ ላይ ብቻ እንዲያተኩር ትልቅ ግፊት ሲደረግ ነበር። የንግድ ስራም በማህበረሰቡ መካከል በሰላም እንዲከናወን የንግድን ስራ የሚያስተጓጉሉ ዘራፊዎች እንዲቀጡ በአዋጅ ተነግሯል። ምጣኔ ሐብቱም የአንድ መንግሥት የአቅም መሰረት ስለሆነ

ግብር ወይም ቀረጥ እንደ ሸዋ፣ ወሎ፣ ጎጃምና ጎንደር ካሉት ክልሎች በግዳጅ ይሰበሰብ ነበር። ከዚህም ውጭ ኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ከያዘችው መሬት ላይ በመቀነስ በመንግሥት ቁጥጥር ስር በማስገባት እና የእምነቱን አገልጋዮች ብዛት በመቀነስ ተሓድሶ ተደርጓል።

ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ሀገሪቱ እንደ አውሮፓ የሰለጠነች እንድትሆን ፍላጎት ስለነበረው አውሮፓዊያንን የተለያዩ ባለሞያዎችና አዋቂዎችን እንዲልኩለት በተደጋጋሚ ሲጠይቅ ነበር። በስተ መጨረሻም ጥያቄው በቀላሉ በጎ ምላሽ ስላላገኘ በሀገሪቱ የነበሩትን አውሮፓውያን ሁሉንም ወደ እስር ቤት እንዲጓዙ ተደርጓል። በዚህ ምክንያት የተነሳም በአውሮፓውያንና በቴዎድሮስ መካከል አለመግባባቱ በጣም እየሰፋ ሄዶዋል። በመሆኑም በ1867 እ.አ.አ እንግሊዝ የጦር ሰራዊቷን ወደ ቀይ ባህር ለመላክ ተገዳለች። ይህ የእንግሊዝ ጦርም በ1868ዓም ባደረገው ዘመቻም በመቅደላ ጦርሜዳ በተደረገው ጦርነት ለዳግማዊ ቴዎድሮስ መሸነፍና መሞት ምክንያት ሆኗል። ይሁን እንጂ ለዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ መሰረት ሊጥል ችሏል።

## ለ/ የዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ መንግሥት ምስረታ መገባደድ

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. ከ1870 እስከ 1889 እ.አ.አ በኢትዮጵያ የግዛት መስፋፋት ምን እንደሚመስል ተወያዩበት?
2. በዘመናዊው የኢትዮጵያ ታሪክ መንግሥት ምስረታ መገባደድ ላይ ተወያዩበት
3. በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ “ክፉ ቀን!”ተብሎ የሚታወቀው ዘመን ያደረሰው ጉዳት በማገናዘብ ለክፍላችሁ አቅርቡ
4. የውጫሌው ስምምነት አንቀጽ 17 ምን እንደሚል በሰፊው ተወያዩበት፡፡

የኢትዮጵያ ነገሥታት አብዛኛዎቹ ዘመናዊውን የኢትዮጵያ መንግሥት ለመመስረት የተለያዩ እንቅስቃሴዎችን ሲያደርጉ ቆይተዋል። ይሁን እንጂ ከ1855-1900 እ.አ.አ መካከል የተደረጉት እንቅስቃሴዎች ለዘመናዊው የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ ትልቅ አስተዋጾ አበርክቷል። ዳግማዊ አፄ

ቴዎድሮስ ለዚህ ስራ ፈር ቀዳጅ ቢሆንም እሱ ያደረጋቸው ዘመናዊውን መንግሥት የመመስረት ተሓድሶዎች ሊሳኩለት አልቻሉም። ይሁን እንጂ ከሱ በመቀጠል ወደ ስልጣን ለመጡ ነገሥታት መንገድ በመክፈት ትልቅ የቤት ስራ እንዲሆናቸው አድርጓል።

በአፄ ዮሐንስ IVኛው (1872-1889) ጊዜ ዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ መንግሥት ምስረታ የቀጠለ ቢሆንም ኢትዮጵያ ከውጭ አገራት ጋር ጥሩ የሚባል ግንኙነት አልነበራትም። ስለዚህም አገሪቱ ከብዙ የውጭ አገራት ጋር ስትዋጋ ቆይታለች። እነሱም፤

- ከግብጽ ጋር (1875-1885 እ.አ.አ)
- ከጣልያን ጋር (1887-1889 እ.አ.አ) እና
- ከሱዳን ጋር (1886-1889እ.አ.አ) ከባድ አለመግባባትና ጦርነት ውስጥ ቆይታለች። በዚህም የተነሰ በ1889 አፄ ዮሐንስ IVኛው በሱዳኖች ሊገደል ችሏል።

በ1865 ዳግማዊ ሚኒሊክ ከመቅደላ እስር ቤት በመጥፋት ወደ ሸዋ ተመልሷል። ከዚያም ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በኋላ ለአፄ ዮሐንስ IVኛው እውቅና ላለመስጠት ትልቅ ሰጣ ገባ ውስጥ ሊቆዩ ችለዋል። እንዲሁም ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ እራሱን 'ንጉሰ ነገስት' በማለት አንግሷል። በዚህ መሰረትም በ1889 እአአ መተማ ላይ በተካሄደው ጦርነት አፄ ዮሐንስ IVኛው ህይወቱ ካለፈ በኋላ ዳግማዊ ሚኒሊክ እንደ ተመኘው በቀላሉ ወደ ስልጣን ሊመጣ ችሏል። ከዚህ በኋላ ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክም ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ. ማስቀጠል ችሏል። በመሆኑም በዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ዘመነ መንሥት (1889-1913) ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ መገባደድ ችሏል። ይህ ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ አካሄድ በተለያየ መንገድ የተከናወነ ነው። እነሱም፤

1ኛው የጦር ኃይል በመጠቀም (በጉልበት) ግዛት በማስፋፋት ነው። ይህ የጦር ኃይል መጠቀም አካሄድ የተፈጥሮ ሐብትንና የራሳቸውን አስተዳደር ያላቸውን ብዙ ህዝቦችን በግዛቱ ስር እንዲውል አድርጓል። እነሱም እንደ አርሲ፣ ሐረር ወለይታና ከፋ ናቸው። ከዚህም ውጭ እንደ ቤኒሻንጉልና ኦጋዴን የመሳሰሉትን ህዝቦች በግዛቱ ስር እንዲውል አድርጓል።

2ኛው በሰላማዊ መንገድ ብሔር ብሔረሰቦችን በማባበል ወይም በማደራደር

ዘዴ እጅ በማሰጠት ማስገበር ነው:: ይህም የተከናወነው በተለያየ ዘዴ ሲሆን በመሾም፣ በመሸለምና በጋብቻ ግንኙነት በማስተሳሰርና በመሳሰሉት ናቸው:: ይሁን እንጂ ይህ አካሄድ ብሔር ብሔረሰቦችን ያስኮረፈና ከፍተኛ መንገላታት ውስጥ ያስገባቸው ነበር::

እነዚህ ሁለት ዘዴዎች በመጠቀም ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ በሁሉም አቅጣጫዎች የግዛት ማስፋፋት አካሂዷል:: እንዲሁም ዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታና ኢኮኖሚ ማጠናከር የሚለውን እስትራቴጂን በመያዝ በተፈጥሮ ሐብትና በማዕድናት የበለጸጉ ቦታዎችን በብዛት በቁጥጥሩ ስር ማዋል ችሏል:: በተመሳሳይ ሁኔታም ከደቡብ-ምእራብ ኢትዮጵያ ተነስቶ ወደ ጎንደርና መተማ የሚዘልቀውን የንግድ መስመር ተቆጣትሮታል:: በመቀጠልም ከፋ አከባቢ በመነሳት ወደ ሐረር የሚዘልቀውንም የንግድ መስመር በራሱ አስተዳደር ስር አውሎታል::

በአጠቃላይም ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ለዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ አስተዋጽዖ አበርክቷል:: በሌላም በኩል እንደ ጣልያን፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ሌሎች የአውሮፓ ሀገራት ጋር ጠንካራ ግንኙነት ነበረው:: በዚህም የተነሳ የተለያዩ ቴክኖሎጂዎችና የምዕራባዊያንን ስልጣኔ ወደ አገሪቱ ለማስገባት ትልቅ ሙከራ አድርጓል::

## መልመጃ 6.1

### ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጭ

1. ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ከእንግሊዝ ሀገር ጋር ወደ ውጊያ ከገባበት ምክንያቶች ውስጥ ሁለቱን ግለጽ/ጪ
2. ዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ለዘመናዊ የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ ከግብ ለማድረስ የተጠቀመባቸው ዘዴዎችን ዘርዝር/ሪ
3. በ19ኛው ክ/ዘ ውስጥ ለዘመናዊውን የኢትዮጵያ መንግሥት ምስረታ ካካሄዱት ነገሥታት ውስጥ ትልቅ ሚና ከነበራቸውን ውስጥ ሶስቱን ዘርዝር/ሪ፡፡
4. በ1870ዎቹና በ1890ዎቹ ዓመታት መካከል ከኢትዮጵያ ጋር ከተዋጉ አገራት መካከል ሶስቱን ፃፍ/ፊ
5. ግብጽ በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን የወረረችበት ምክንያት ምንድነው
6. ከዳግማዊ አፄ ሚኒሊክ ጋር ሰላማዊ ግንኙነት ከነበራቸውን የአውሮፓ መንግሥታት መካከል ሶስቱን ፃፍ/ፊ፡፡

7. በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ወደ ኢትዮጵያ የገቡትን የተለያዩ ለውጦችና የውጭ ስልጣኔዎች ግለጽ?

## 6.2. የኢትዮጵያ የረጅም ርቀት ንግድና የንግድ መስመሮች

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. በእናንተ አከባቢ የግዥና ሽያጭ ሂደት ምን እንደሚመስል ከጓደኛህ/ሽ ጋር በመማከር ለክፍላችሁ ተማሪዎች ዘገባ አቅርቡ
2. ንግድ ለአንድ አገር ምጣኔ ሀብት ያለውን ጠቀሜታ በፊት ካለህ/ሽ ግንዛቤ በመነሳት ዘርዝር/ሪ
3. የኢትዮጵያንና የአፍሪካ ቀንድ ካርታን በመጠቀም የረጅም ርቀት የንግድ መስመሮች አቅጣጫዎችን አሳይ/ዩ

በንግድ ስርዓት ውስጥ የግዥና ሽያጭ ስራ በተለያዩና በብዙ አካላት መካከል ይፈጸማል። ይህም በአምራቾችና ተጠቃሚዎች መካከል ወይም በነጋዴዎችና በተጠቃሚዎች መካከል ሊካሄድ ይችላል። እንዲሁም የግዥና ሽያጭ ስራ በአንድ አከባቢ በሚገኙ ሰዎች መካከል ወይም በተለያዩ አከባቢዎች መካከል ሊከናወን ይችላል። በአንድ በተወሰነ አከባቢ በሚገኙ ማህብረተሰብ መካከል የሚካሄድ ንግድ የአከባቢ ንግድ ሲባል በተለያዩ አከባቢዎች መካከል የሚካሄደው ደግሞ የረጅም ርቀት ንግድ በመባል ይታወቃል።

በኢትዮጵያና በአፍሪካ ቀንድ አከባቢ የረጅም ርቀት የንግድ መስመር በጣም የተስፋፋው ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን በኋላ ነው። ከ19ኛው መቶ ክ/ዘመን በኋላ የንግድ ስራ ለመስፋፋቱ የተለያዩ ምክንያቶች አሉት። እነሱም፤

1ኛው በቀይ ባህርና በሰሜን አፍሪካ አከባቢ የፖለቲካና የሰላም መረጋጋት መኖር

2ኛው በአረቢያና የአፍሪካ ቀንድ አከባቢ የንግድ እቃዎችና ባሪያዎች የመግዛት ፍላጎት መጨመር

3ኛው የአውሮፓ አገራት የቀይ ባህርና የኤደን ባህረ ሰላጤ አከባቢዎችን ለመያዝ ያላቸው ፍላጎት እየጨመረ መምጣቱ ናቸው::

የረዥም ርቀት ንግድ የተለያዩ አከባቢ ህዝቦችንና የተለያዩ ነጋዴዎችን ሲያገናኝ ነበር። እነዚህ ነጋዴዎችም በባህላዊ የመጓጓዣ ዘዴዎች ለምሳሌ በቅሎ፣ ግመል እና የመሳሰሉትን በመጠቀም ረጃጅም የንግድ መስመሮችን በማቋረጥ ይነግዱ ነበር። በዚህ ሁኔታም ከውጭ አገር የሚገቡና ወደ ውጭ የሚሸጡትን የንግድ እቃዎች በማመላለስ የተለያዩ አከባቢዎች በንግድ እንዲገናኙ አድርገዋል። ስለዚህ የረጅም ርቀት ንግድ የውጭና የአገር ውስጥ ንግድን ያካተተ ነበር።





ሥዕል.6. 2. (ሀ) የረጅም ርቀት ነጋዴዎች ጉዞ

በረዥም ርቅት ንግድ ውስጥ የውጭ አገራትና የአገር ውስጥ ነጋዴዎች ተሳትፈዋል። ከውጭ አገራት ነጋዴዎች ውስጥ በቀይ ባህር አከባቢ የተሳተፉት አርመኖችና ህንዶች ነበሩ። በዚህ ንግድ ውስጥ ትልቅ ድርሻ የነበራቸው ኢትዮጵያን ሙስሊም ነጋዴዎችም አሉበት። ምክንያቱም እነዚህ ሙስሊም ጋዴዎች ከአረቦች ጋር የተሻለ ግንኙነት ስላላቸው ነው ተብሎ ይታመናል። ከዚህም ውጭ በአርሶ አደሩ ዘንድ የንግድ ስራ ባለመታወቁ እንደ ተራ የስራ መስክ ስለሚወሰድ ነበር።

የረጅም ርቀት ነጋዴዎች በቡድን የሚጓዙ ሲሆን መሪያቸውም " ነጋድራስ " በመባል ይታወቃል። ትርጉሙም የነጋዴዎች እራስ ማለት ነው። ይህ መሪም የተለያየ ኃላፊነት አለው። ለምሳሌ የነጋዴዎችን መንቀሳቀሻ የጊዜ


ሰሌዳ ማውጣት፣ የማደሪያ ቦታና መስፈሪያ ቦታ ማዘጋጀት እና ሌሎችንም ጉዳዮች በበላይነት መምራትና የመሳሰሉት ናቸው። የረጅም ርቀት ንግድ መስመር ነጋዴዎች በተለያየ ስም ይታወቃሉ። ከነዚህ ውስጥ በጣም የሚታወቁት ከዚህ በታች በተቀመጠው ሰንጠረዥ ውስጥ ተዘርዝረዋል።

ሰንጠረዥ 6.2. የ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነጋዴዎች የጋራ ስሞች

| የነጋዴዎች ስም | የመነሻቸው አከባቢዎች | የሚነግዱበት ማዕከላትና አከባቢዎች |
|---|---|---|
| ጀበርቲ | ሰሜን ኢትዮጵያ | እስከ ቀይ ባህር አከባቢ በመነገድ ይታወቃሉ |
| አፍካላ | ደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ | ደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያና ማዕከላዊ ኢትዮጵያ ውስጥ |
| ጀላባ | ሱዳን | መተማና የኢትዮ-ሱዳን ድንብር አከባቢዎች |

የረጅም ርቀት ነጋዴዎች ከውጭ ሀገር ወደ ሀገር ውስጥ የሚያስገቡት የንግድ ዕቃ አይነቶች ብዙ ናቸው። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ቅመማቅመም፣ ጨሌዎች፣ ጨርቃ ጨርቆች፣ የጦር መሳሪያዎች፣ መድሃኒቶች እና የመሳሰሉት ናቸው። ከሀገር ውስጥ ወደ ውጭ ሀገራት የሚላኩ ዕቃዎች ደግሞ የዝሆን ጥርስ፣ የእንስሳት ቆዳ፣ የተለያዩ እንስሳት እና ባሮች ናቸው። ወደ ውጭ ሀገራት የሚላኩ የንግድ ዕቃዎች በአብዛኛው ከደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያ አከባቢዎች የሚመጡ ናቸው።

ትላልቅ የረጅም ርቀት የንግድ መስመር አቅጣጫዎች ከደቡብ-ምዕራብ ኢትዮጵያ በመነሳት ወደ ተለያየ አቅጣጫዎች የሚሄዱ ናቸው።
በተለይም ወደ ሰሜን አቅጣጫ የሚጓዘው ከቀይ ባህርና ከኤደን ባህረ-ሰላጤ ጋር የሚያያዘው ዋነኛው መስመር ነው። የደቡብ ምዕራብ መስመር መነሻው ከፋ (ቦንጋ)ነው። ሁለተኛው የንግድ መስመር ከፋ (ቦንጋ) ተነስቶ ሰቃ፣ አሰንዳቦ፣ ጂሬን እና የመሳሰሉት ማዕከሎችን በማቋረጥ እስከ ዘይላና በርበራ ይዘልቃል፡፡ ከዚህ የንግድ መሰመር አከባቢ ባሮች፣ የእንስሳት ቆዳ፣ ወርቅና ቡና በብዛት ሲቀርቡ ቆይተዋል።




6.2(ለ) የ19ኛውን ክፍለ ዘመን የረጅም ርቀት የንግድ መስመሮች የሚያሳይ ካርታ

የረጅም ርቀት የንግድ ስራ ለብዙ ዓመታት እቃን በእቃ በመቀየር ዘዴ ሲከናወን የኖረ ነው። ይሁን እንጂ በሂደት ይህ አሰራር ወደ አሞሌን እንደ ገንዘብ መጠቀም ተሸጋግሯል። ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ አሞሌ በኢትዮጵያ ምጣኔ ሃብት ውስጥ ጉልህ ሚና ነበረው። በመሆኑም ለረጅም ጊዜ ግብር፣ ቀረጥ እና ደመወዝም ጭምር በአሞሌ መልክ ይከፈል ነበር። ይሁን እንጂ በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ አከባቢ‘ማርያቴሬሳ’ የሚባል የኦስትሪያ መንግሥት ገንዘብ አገልግሎት መስጠት ሲጀምር የአሞሌ ጠቀሜታ ቀንሷል።

በአጠቃላይም የረጅም ርቀት ንግድ በሀገር ውስጥ ብዙ ለውጦችን ማምጣት ችሏል። ከነዚህም ውስጥ የተለያዩ አከባቢዎችን በምጣኔ ሀብት ማስተሳሰር፣ የምጣኔ ሀብት ለውጥ እና ለተለያዩ ሙያዎች ዕድገት መሰረት ሊሆን ችሏል። የተለያዩ የንግድ ማዕከላትም ወደ ከተማነት በማደግ የአስተዳደር ማዕከላት በመሆን፣ የተለያየ ማህበራዊ አገልግሎት መስጪያ ማዕከላት መሆንና የተለያዩ ሙያዎች መስፋፋት መሰረት ሆኗል። በዚህም መሰረት በብሔር ብሔረሰቦች መካከል ግንኙነት በመፍጠር ለዘመናዊ ኢትዮጵያ መንግስት ምስረታ ጉልህ አስተዋጾ አበርክቷል።

## የማረጋገጫ ተግባር 6.2.

I. ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ

1. በረጅም ርቀት ንግድ ውስጥ ወደ ውጭ ሀገራት ይላኩ ከነበሩት ዕቃዎች ውስጥ አራቱን ፃፍ/ፊ
2. በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ የረጅም ርቀት ንግድ እንዲስፋፋ ካደረጉት ትላልቅ ምክንያቶች ውስጥ ሶስቱን ግለጽ/ጪ
3. የረጅም ርቀት ንግድ  መስመር ነጋዴዎች ለምን በቡድን በመሆን እንደሚጓዙ ግለጽ/ጪ
4. የኢትዮጵያ ካርታን በማንሳት በ19ኛው ክፍለ ዘመንና በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የረጅም ርቀት የንግድ መስመር አቅታጫዎችን የተለያዩ ቀለማት በመቀባት አሳይ/ዪ
5. የረጅም ርቀት ንግድ  መስመር ያቋርጧቸው ከነበሩት ከተሞች ውስጥ ሶስቱን ፃፍ/ፊ
6. የረጅም ርቀት ንግድ  መስመር መነሻ በአብዛኛው ከደቡብ-ምዕራብ ለምን ሊሆን ቻለ?

## 6.3. የኢትዮጵያና የውጭ ሀገራት ግንኙነት

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. በተለያዩ ሀገራት መካከል የፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሃብታዊ እና ማህበራዊ ግንኙነቶች መኖር ምን ጠቀሜታ አለው?
2. በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ኢትዮጵያ ከውጭ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት ምን ይመስል ነበር? ተወያዩበት
3. ከ1867-68 እንግሊዝ ለምን በኢትዮጵያ ላይ ልትዘምት ቻለች?

በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የኢትዮጵያ ነገስታት ከውጭ ሀገራት ጋር ብዙ የስምምነት ውል ሲፈራረሙ ቆይተዋል። በዚህም መሰረት ዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ በመጀመሪያ ከእንግሊዝ ሀገር ጋር ጥሩ የሚባል ግንኙነት

ነበረው። ነገር ግን ይህ ግንኙነት ወደ መጨረሻው አከባቢ ወደ ግጭት በመቀየር በ1868 ዓ.ም ጄኔራል ናፒየር በዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ላይ ሊዘምት ችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ አፄ ዮሐንስ IVኛውም በመጀመሪያ ላይ ከግብጽና ሱዳን ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ነበረው። ይህ የአፄ ዮሐንስ IVኛው ግንኙነት ግን በኋላ ላይ ወደ ጠላትነት በመቀየር ወደ ውጊያ ሊገቡ ችለዋል። በዚህም መሰረት በ1889 ዓም አፄ ዮሐንስ IVኛው ከሱዳኖች ጋር በመተማ ጦርሜዳ ባደረገው ጦርነት ህይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

ከ1870ዎቹ ጀምሮ ደግሞ ዳግማዊው አፄ ሚኒሊክ ከጣሊያን፣ ከፈረንሳይ እና ከእንግሊዝ ጋር የንግድ ስምምነት ግንኙነት መስርቶ ነበር። ይሁን እንጂ ኢትዮጵያና እነዚህ ስምምነት የተፈራረሙ ኃይሎች ፍላጎታቸው ሳይሟላ ሲቀር ወደ ግጭትና ጠላትነት ቀይራዋል። ለምሳሌም የውጫሌ ስምምነት በ1889 ዓ.ም በጣልያንና በኢትዮጵያ መካከል ከተፈረመው ውል በኋላ ወደ ጠላትነት በመቀየሩ ግጭትና ጦርነት ሊያስነሳት ችሏል።

በአጠቃላይም በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ኢትዮጵያ በአለም አቀፍ ደረጃ ከብዙ የውጭ ሀገራት ጋር ጥሩ የሆነ ግንኙነት ነበራት። ለምሳሌም በ1923 እ.አ.አ የአለም መንግሥታት ሊግ አባል በመሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ዕውቅና አግኝታለች። እንዲሁም በ1945 እ.አ.አ የተባበሩት መንግስታት ድርጅት (UNO) አባል በመሆን ትታወቃለች። በተጨማሪም የአለም አቀፍ የሰው ልጅ መብት አዋጅ (UDHR 1948) በመቀበል ከአለም ሀገራት ጋር ያላትን ግንኙነት ማጠናከር ችላለች።

## የማረጋገጫ ተግባር 6.3.

I. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክል የሆኑትን 'እውነት' ትክክል ያልሆኑትን ደግሞ 'ሐሰት' በማለት መልስ ስጥ/ጪ

1. ኢትዮጵያ የምትገኝበት ቦታ ከውጭ ሀገራት ጋር ግንኙነት እንዲኖራት አድርጓታል
2. የኢትዮጵያ ማህበረሰብ ባህል ከሌሎች ሀገራት ማህበረሰቦች ባህል ጋር ግንኙነት የለውም
3. በአለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ ሁሉም ሀገራት ለየራሳቸው ብሔራዊ ፍላጎት ቅድሚያ ይሰጣሉ

4. ከአፍሪካ ሀገራት ውስጥ ኢትዮጵያ ለመጀመሪያ ጊዜ የአለም መንግሥታት ሊግ አባል የሆነች ሀገር ናት
5. የውጫሌ ስምምነት የኢትዮጵያና የጣልያንን ግንኙነት አጠናክሯል፡፡

II. ከዚህ በታች ለቀረቡትን ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ

5. ከሚከተሉት ሀገራት መካከል ለመጀመሪያ ጊዜ የአለም መንግሥታት ሊግ አባል የሆነችው የትኛዋ ናት?

   ሀ/ ሱዳን

   ለ/ ጇቡቲ

   ሐ/ ኬኒያ

   መ/ ኢትዮጵያ

6. የአለም አቀፍ የሰው ልጅ መብት አዋጅ (UDHR) ዓላማ ምን ነበር?

   ሀ/ የምጣኔ ሃብት እኩልነት ማረጋገጥ

   ለ/ የቅኝ አገዛዝ ስርዓትን መቃወም

   ሐ/ የሰው ልጅ እኩልነት ማረጋገጥ

   መ/ የሀገራትን ልዓዋላዊነትን ማወጅ

## 6.4.የኢትዮጵያ ህዝቦች በአንድነት ዳር ድንበርና ሉዓላዊነትን ለማስከበር ያደረጉት ትግል

በታሪክ ሂደት ውስጥ የኢትዮጵያ ህዝቦች በጋራ በመሆን የሀገራቸውን ሉዓላዊነት በማስከበር ይታወቃሉ። በመሆኑም በተለያየ ጊዜ በውጭ ወራሪዎች ሲደረግ የነበረውን የሀገሪቱን ሉዓላዊነት ለመዳፈር የተደረጉትን ሙከራዎች ለማክሸፍ በጋራ በመሆን እርምጃ እየወሰዱበት ዛሬ ደርሰዋል። በዚሁም መሰረት በዘመናዊ የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ትላልቅ ጦርነቶችን አካሂደዋል። እነዚህም የግብጽ ወረራ(1875-1884)፣ የመሐዲስቶች ወረራ(1882-1889)፣ የጣሊያኖች ወረራ (1885-1896ና 1935-1941)፣ የሶማሊያ መንግሥት ወረራ (1977-1978) እና የመሳሰሉት ናቸው።ይሁን እንጂ ሁሉም ወራሪዎች ተሳክቶላቸው ኢትዮጵያን መያዝ አልቻሉም። ይህም ሊሆን የቻለበት ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ ህዝቦች ብሔሮችና ብሔረሰቦች በአንድነት በመቆማቸው ነው።

## ሀ/ የግብጽ ወረራ ከ1875-1885

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የኢትዮጵያ ህዝቦች የሀገራቸውን ሉዓላዊነት ለማስከበር ምን ያህል ዋጋ ሲከፍሉ እንደ ነበር በአከባቢያችሁ የሚገኙትን አዛውንቶች በመጠየቅ ሪፖርት አቅርብ/ቢ
2. የግብጽ መንግሥት ኢትዮጵያን የወረረበት ምክንያቶችን በመዘርዘር ተወያዩበት
3. ኢትዮጵያ በጉንደትና ጉራ ጦርነቶች ላይ እንዴት ልታሸንፍ እንደ ቻለች ለክፍልህ/ሽ ዘገባ አቅርብ/ቢ
4. በሒወት ስምምነት ጠቀሜታና ጉዳት ላይ ክርክር አድርጉ፡፡

የኢትዮጵያ መንግሥታት ከግብጽ ጋር ለረጅም ዘመናት መልካም ግንኙነት ነበራቸው። በተለይም ከ4ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ከክርስትና ሀይማኖት መምጣት በኋላ ኢትዮጵያ ከግብጽ ጋር ያላት ግንኙነት በጣም ጠንካራ ነበር። ከዚህም ውጭ በንግዱ ዘርፍም ግብጽ በአፍሪካ ቀንድ አከባቢ ሀገራት በተለይም ከኢትዮጵያ ጋር ለረጅም ዘመናት ጠንካራ ግንኙነት መስርታ ነበር።

ይሁን እንጂ ይህ ግንኙነት ከ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጀመሪያ አከባቢ ጀምሮ ወደ ግጭት ተቀይሯል። በተለይም ሞሃመድ አሊ(1805) ወደ ስልጣን ከመጣበት ዘመን በኋላ ግብጽ እንደ ኢትዮጵያ ካሉት አጎራባች ሀገራት ጋር ወደ ግጭት ገብታለች። በዚሁም መሰረት ኢትዩጵያ በ1848 እ.አ.አ በደባርቅ ጦር ሜዳ ስትሸነፍ፣ ከ1875-76 በጉንደትና ጉራ ጦርሜዳዎች ላይ ደግሞ ከግብጽ ጋር በመዋጋት ማሸነፍ ችላለች። ይሁን እንጂ ከ1875-1885 መካከል ግብጽ የሐረርን ከተማ በመያዝ ልታስተዳድር ችላለች። በመጨረሻ ግን በሒወት ስምምነት ጊዜያዊ ሰላም ሊሰፍን ችሏል።

## ለ/ የመሐዲስቶች ወረራ (1880-1889)

### የሙከራ ጥያቄዎች

1. በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሱዳን ኢትዮጵያን ልትወር የቻለችበት ምክንያቶች ምንድናቸው
2. በ19ኛው ክፍለ ዘመን ሱዳን ኢትዮጵያን ለመያዝ የተጠቀመችባቸው ዘዴዎች ምን ምን እንደነበሩ በመገንዘብ ገለጽ/ጪ.
3. በመተማ ጦርሜዳ ላይ ኢትዮጵያ እንዴት ልትሸነፍ ቻለች? ዋና ዋና ምክንያቶችን ዘርዝር/ሪ፡፡

በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል የነበረው መልካም ግንኙነት መሻከር የጀመረው ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ ነው። በ1880ዎቹ አከባቢ እስከ ነጆ (ወለጋ) በመዝለቅ ወረራ በመፈጸም በጉቴ ዲሊ ጦር ሜዳ ላይ መሀዲስቶች ተሸንፈዋል። ይሁን እንጂ በሱዳንና በኢትዮጵያ መካከል ያለው አለመግባባት ወደ ከፍተኛ ግጭት የተሸጋገረው ከሒወት ስምምነት (1884) በኋላ ነበር።

የሒወት ስምምነት በኢትዮጵያና በግብጽ መካከል የተደረገ ስምምነት ነው። የስምምነቱ ዋናው ይዘት ከ10,000 በላይ የሚሆኑትና በሱዳኖች ተከበው የነበሩትን የእንግሊዝ ሰራዊት ኢትዮጵያ በመርዳት በምጽዋ በኩል እንድታስወጣ የሚል ነበር። በዚሁም መስረት አፄ ዮሐንስ IVኛው የጦር ኃይሉን ወደ ሱዳን በመላክ በኩፊት ጦርሜዳ (1885) ከሱዳኖች ጋር ተዋግቷል። በዚህም ጦር ሜዳ ኢትዮጵያኖች በማሸነፍ የእንግሊዝን ጦር ኃይል ከሱዳኖች አስለቅቀው በምጽዋ በኩል በሰላም ሸኝተዋቸዋል። በመሆኑም ሱዳኖችን እልህ ውስጥ እንዲገቡና ለብቀላ እንዲዘጋጁ አድርጓቸዋል።

በዚህ መሰረት በምዕራብ በኩል በተደጋጋሚ ኢትዮጵያን ወረዋል። በ1887 በሳርውሃ ጦርሜዳ ከጎጃም መሪ ከነበሩት ንጉሥ ተክለ ሃይማኖት ጋር ባደረጉት ጦርነት ማሸነፍ ችለዋል። በዚህም ድል በመነሳሳት እስከ ጎንደር ከተማ ድረስ በመዝለቅ የጎንደርን ከተማ መዝረፍና ማቃጠል ችለዋል። በመጨረሻም አፄ ዮሐንስ IVኛው ይህን ቂም ለመበቀል በ1889 እ.አ.አ ወደ ሱዳን ዘምቶ መተማ ላይ ሊሞት ችሏል።

## ሐ/ የጣልያን ወረራ (1885-1896)

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. ጣልያን የኢትዮጵያን መሬት የያዘችበት አካሄድ እንዴት እንደነበረ ተወያዩበት
2. ኢትዮጵያ ጣልያንን ያሸነፈችበትን ጦርሜዳዎች በመለየት ያሸነፈችበትን ምክንያቶች ላይ ክርክር አድርጉ
3. ከአደዋ ጦርነት በኋላ በተገኘው ውጤት ላይ ሪፖርት በማዘጋጀት ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ

እንደሚታወቀው የጣልያን መንግሥት በአፄ ዮሐንስ IVኛው ዘመነ መንግሥት በምጽዋ አከባቢ ሊስፋፋ ችሏል። በተለይም ከ1885 ዓ.ም በኋል ከምጽዋ በመነሳት ወደ ኤርትራ ተስፋፍቷል። በዚሁም መሰረት የጣልያን መንግሥት ከምጽዋ ወደ ኣይሌት፣ ዊአ፣ ሰአቲ፣ ዶጋሊ እና አስመራ በቅደም ተከተል በመስፋፋት መቆጣጠር ችሏል። በዚህን ጊዜ ከዳግማዊው ምኒሊክ ጋር ጣልያኖች የነበራቸው ግንኙነት መልካም ነበር። በመሆኑም ይህ መልካም ግንኙነት በማደጉ የተነሳ የውጫሌን ስምምነት እስከ መፈራረም ድረስ ደርሷል።

ይሁን እንጂ ከጊዜ በኋላ የውጫሌው ስምምነት ችግር ስለፈጠረ የዳግማዊ ምኒሊክና የጣልያኖች ግንኙነት ወደ ጠላትነት ተቀይሯል። በዚህም መሰረት የኢትዮጵያ መንግሥት የውጫሌ ውል ያለውን ስህተት እንዲስተካከልና እንዲታረም ቢጠይቅም ሊስተካከል አልቻለም። በተለይም በውጫሌው ውል አንቀጽ 17 በጣልያንኛ የተፃፈው ትርጉም ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ በጣልያን መንግሥት ቁጥጥር ስር ያዋለ ነበር። ከዚህም የተነሳ ቀስ በቀስ አለመግባባቱ እያደገ በመምጣቱ ከ1895 ዓ ም ጀምሮ ወደ ጦርነት ሊሸጋገር ችሏል። አለመግባባቱ በመካረሩ በ1896 የኢትዮጵያ ብሔር ብሔለሰቦች በአንድነት በመቆም በአደዋ ጦርሜዳ በጣልያን ላይ አንጸባራቂ ድል ሊጎናጸፉ ችለዋል።

## መ/ የሶማሊያ ወረራ (1977-1978)

**የሙከራ ጥያቄዎች**

1. የሶማሊያ መንግሥት ኢትዮጵያን ሊወር የቻለበት ዋና ዋና ምክንያቶች ምን ነበሩ? ተወያዩበት
2. በሶማሊያ ወረራ ጊዜ የኢትዮጵያ መንግሥት ፖለቲዊና ምጣኔ ሀብታዊ ሁኔታ ምን ይመስል ነበር?
3. በ1977-1978ቱ የሶማሊያ መንግሥት ወረራ ኢትዮጵያ እንዴት ልታሸንፍ እንደ ቻለች በማቀነባበር ለክፍልህ/ሽ አቅርብ/ቢ?

በኢትዮጵያ መንግሥትና በሶማሊያ መንግሥት መካከል አበይት ግጭቶች የነበሩት በቀዳማዊው ንጉሥ ኃይለስላሴና በመንግሥቱ ኃይለማሪያም ዘመናት ነበር። ጉልህ የሆነ የግጭቶቹ ምክንያትም የሶማሊያ መንግሥት ግዛት የማስፋፋት ፍላጎት ማየል ነው። ይህ በቀዳማዊው ኃይለስላሴ የጀመረው ግጭትም እስከ ደርግ ዘመን መጨረሻ አከባቢ ሊዘልቅ ችሏል።

ጉልህ የሆነውና ከፍተኛው የሶማሊያ መንግሥት ወረራ በ1977-1978 ዓ.ም እ.አ.አ መካከል በመሃመድ ሰይድ ባሬ የተካሔደው ወረራ ነው። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች መተባበርና በኮሚዩኒስት ርዕዮተ አለም አራማጅ ሀገራት ድጋፍ በወራሪው ላይ በካራማራ ጦርሜዳ ድል ተጎናጽፈዋል። ድጋፍ ካደረጉት የኮሚኒዩስት ሀገራት መካከል ራሽያና ኩባ በቀጥታ የስልጠናና የተለያዩ አቅርቦቶች ድጋፍ ያደረጉ ሀገራት ናቸው።

በአጠቃላይ ኢትዮጵያ የውጭ ወራሪ ኃይሎችን በመከላከል ሉዓላዋላዊነቷን አስከብራ ዛሬ ላይ የደረሰች ሀገር ናት። ስለዚህም በአሁኑ ጊዜ ኢትዮጵያ ነፃነቷን በማስከበሯ ለተቀሩት የአፍሪካ ቀንድ ሀገራት በምሳሌነት ስሟ እየተነሳ ያለች ሀገር ናት።

# ማጠቃለያ

የኢትዮጵያ የመካከለኛው ዘመን መንግሥት የተጠናቀቀው በ1855 ዓ.ም ነው ። ከመካከለኛው ዘመን መንግሥት መጨረሻ ቀጥሎ የመጣው የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና መንግሥት ምስረታ መጀመር ነው። በመሆኑም ከዳግማዊ አፄ ቴዎድሮስ ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና መንግሥት ምስረታ እንቅስቃሴዎች ሲካሄዱ ቆይተዋል። የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና መንግሥት ምስረታ እንቅስቃሴዎች በሚካሄዱበት ጊዜ የውጭ ሀገራት ኢትዮጵያን በኃይል ለመያዝ ሲንቀሳቀሱ ነበር። እነዚህም ሀገራት እንደ ግብጽ፣ ሱዳን፣ ጣልያን እና ሶማሊያ የመሳሰሉት ናቸው።

የኢትዮጵያ ዘመናዊ ታሪክና መንግሥት ምስረታን ከገጠሙት ችግሮች መካከል ዋነኛው የውጭ ጠላትን የመከላከል ስራ ነበር። በዚሁም መሰረት ኢትዮጵያ የግብጽን (1839-1885) ፣ የሱዳንን (1880-1889) ፣ የጣልያንንና (1885-1896) የሶማሊያ መንግሥታትን ወረራዎች በተሳካ ሁኔታ ስትከላከል ኖራለች። ይህም ሊሆን የቻለበት ዋናው ምክንያት የኢትዮጵያ ብሔሮችና ብሔረሰቦች ለረጅም ዘመናት በጋራ በመሆን የውጭ ወራሪዎችን መመከት በመቻላቸው ነው።

## የምዕራፍ 6 የማጠቃለያ ጥያቄዎች

I. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በማንበብ ትክክለኛ የሆነውን "እውነት" ትክክል ያልሆነውን ደግሞ "ሐሰት" በማለት መልስ/ሺ

1. በ19ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ውስጥ ጣልያን ኢትዮጵያን በመውረር ለመያዝ ሞክራ ነበር
2. የሒወት ስምምነት ለውጭ ወራሪዎች በር የከፈተ ነው
3. ጣልያን የከፋፍለህ ግዛ መርህ በመከተል ኢትዮጵያን ማሸነፍ አልቻለችም
4. ኢትዮጵያ የረዥም ዘመን የነፃነት ታሪክ ያላት ሀገር ናት
5. ኢትዮጵያ ሶማሊያን ያሸነፈችው በአሜሪካን መንግሥት እርዳታ ነበር

II. ለሚከተሉት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ/ጪ.

1. በ1935 ጣልያን ኢትዮጵያን የወረረችበት ቅፅበታዊ ምክንያት የቱ ነው?

   ሀ/ የውጫሌው ስምምነት

   ለ/ የሒወት ስምምነት

   ሐ/ የወልወል ግጭት

   መ/ ሀ እና ለ መልስ ናቸው

2. ኢትዮጵያ ግብጽን ያሸነፈችበት ጦርሜዳ የቱ ነው?

   ሀ/ አድዋ   ሐ/ ጉራ

   ለ/ ማይጨው   መ/ መተማ

3. በአድዋው ጦርሜዳ ላይ ትልቅ አስተዋፅዎ ያላት  የትንኛዋ ናት?

   ሀ/ እቴጌ ጣይቱ

   ለ/ ባቲድል ወንበራ

   ሐ/ እቴጌ ምንትዋብ

   መ/ እቴጌ ዘውዲቱ

4. በ1875 ዓ.ም ኢትዮጵያን በሁለት አቅጣጫዎች የወረረች ሀገር የቷ ናት?

   ሀ/ ጣልያን   ሐ/ ሱዳን

   ለ/ ግብጽ   መ/ እንግሊዝ

III. በሚከተሉት ጦር ሜዳዎች ላይ ኢትዮጵያ ያሸነፉቻቸውን ሀገራት በቅደም ተከተላቸው መሰረት ፃፍ/ፊ

1. ጉንደት
2. ጉራ
3. አድዋ
4. ካራማራ
5. ዶጋሊ

# ምዕራፍ 7

# ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች

## ከምዕራፉ ትምህርት የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ምዕራፍ ትምህርት በ%ላ፤

- ✓ የአየር ለውጥ በሰው ልጅና በሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ
- ✓ የሚያደርሰውን ጉዳት ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- ✓ ህብረተሰቡ አገር በቀል እወቀቶችን በመጠቀም ለተፈጥሮ ሃብቶች
- ✓ የሚያደርገውን እንክብካቤዎችን ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- ✓ የተፈጥሮ ሃብት እንክብካቤ ላይ የሚሰሩ ሰዎችንና ተቋማትን ታደንቃለህ፡፡

## መግቢያ

ሰባተኛ ክፍል ውስጥ ትኩረት የሚሹ ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች ስር የተለያዩ ፅንሰ ሃሳቦችን መማራችሁን ይታወቃል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ስርም ዋና ዋና የአለም ጉዳዮች የሆኑትን እንደ የአየር ንብረት፣ በአየር ንብረት ምክንያት ሊደርሱ የሚችሉ ጉዳቶች እንዲሁም ለአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት የሚሆኑትን ምክንያቶች እንዴት መቀነስ እንደሚቻል ትማራለህ/ሽ ፡፡

## ተማሪዎች ሊደርሱበት የሚገባ የመማር ብቃቶች፤

- የአየር ለውጥ መነሻና በአካባቢው እንዲሁም በሰው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ትገነዘባለህ/ሽ፡፡
- የአየር ለውጥ በሰውና በአካባቢው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቀነስ የህብረተሰቡን ተሳትፎ ምን እንደሆነ ትገልፃለህ/ሽ፡፡
- የአየር መበከልና የሚያመጣውን ጉዳት ትገልጻለህ/ሽ፡፡
- በውሃ እጥረት ምክንያት የሚመጡትን ችግሮች ታብራራለህ/ሽ፡፡
- በደን መመንጠር ምክንያት የሚፈጠሩ ጉዳቶችን ትለያለህ/ሽ፡፡
- አካባቢን ለመንከባከብ የግለሰቦችንና የህብረተሰቡን ተሳትፎ ታደንቃለህ/ሽ፡፡

## 7.1 የአየር ንብረት ለውጥ

### አየር ሁኔታ

የአየር ሁኔታ ማለት በአንድ ቦታና ጊዜ ውስጥ የሚከሰት የአየር ክስተት ማለት ነው፡፡ የአየር ሁኔታ በአከባቢያችን ውስጥ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ፤ በየቀኑ፤ በየሳምንቱ፤በወርና ዓመት ውስጥ የሚከሰት የአየር ሁኔታ ነው፡፡ በሌላ በኩል የአየር ሁኔታ ማለት የሙቀትና ቅዝቃዜ፤ ዝናብ፤ የአየር ግፊት፤ ትነት፤ ንፋስ፤ የፀይ ብርሃንና የመሳሰሉት በተወሰነ ጊዜና ቦታ መከሰትን ወይንም መታየትን ያመለክታል፡፡

ስለ አየር ሁኔታን የሚያጠና ሳይንስ ሚትሮሎጂ የሚባል ሲሆን ሳይንቲስቶቹ ደግሞ ሜትሮሎጂስት ይባላሉ፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች የየቀኑን የአየር ሁኔታን፤ የሙቀት ወይንም ቅዝቃዜ፤ የዝናብ መጠንና ሌሎችንም በመመዝገብ ለተለያዩ አገልግሎቶች ያውላሉ፡፡ የአየር ሁኔታ ከቦታ ቦታ ይለያያል፡፡ በአንድ አካባቢ የአየሩ ሁኔታ ቀኑ ቀዝቃዛ፤ ደረቅ፤ ፀሓያማና ሌላም ሊሆን ይችላል፡፡ በሌላ አካባቢ ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ሆኖ እናገኛለን፡፡

### አየር ንብረት

አየር ንብረት ማለት አማካይ አየር ሁኔታ ማለት ነው፡፡ አየር ንብረት የከባቢ አየር ሁኔታ ሆኖ በውስጡ ያሉት ይዘቶች፤ እንደ ሙቀት፤ቅዝቃዜ፤ ዝናብና

ሌሎችም በተመሳሳይ ሁኔታ ሳይቀያየሩ ለረጅም ጊዜ (በአማካይ ለ35 ዓመታት) በአንድ ቦታ ላይ የሚቆይ የከባቢ አየር ክስተት ማለት ነው፡፡ አየር ንብረትና አየር ሁኔታ መካከል ያለው ልዩነት የመቆያ ገዜ ብቻ ነው፡፡

የአየር ንብረትን የሚያጠና ሳይንስ ክላይማቶሎጂ ይባላል፡፡ የዚህ ሳይንስ አጥኚዎች ደግሞ ክላይማቶሎጂስቶች ይባላሉ፡፡

## መልመጃ 7.1

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ/ሺ

1. የአየር ሁኔታ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የአየር ንብረት ይዘቶችን ዘረዝር/ሪ፡፡
3. የአየር ንብረትን በአጭሩ ግለፅ/ጪ፡፡
4. የአየር ንብረትና አየር ሁኔታ መመሳሰልና ልዩነት ምንድነው?

## 7.1.1. የአየር ንብረት ለውጥ ፅንሰ ሃሳብ

የግምገማ ጥያቄዎች

1. የአየር ንብረት ለውጥ ማለት ምን ማለት ?

የአየር ንብረት ለውጥ በተጨባጭ ሙቀት፤ የቅዝቃዜ፤ የዝናብ፣የዳመና፣ የፀሓይ ብርሃንና የሌሎችንም የአየር ንብረት ይዘቶች መቀየርን የሚያመለክት ነው፡፡ ይህ የአየር ንብረት ለውጥ በተወሰነ ቦታ ወይንም በአለም ሙሉ ሊከሰት ይችላል፡፡

የአየር ንብረት ለውጥ ከአመት አመት የሚታይ ሊሆን ይችላል፡፡ በዓመት ውስጥ አየሩ ሳይታወቅ በድንገት ቀዝቃዛ ወይንም ሞቃታማ እንዲሁም ቀዝቃዛና እርጥበታማ ሊሆን ይችላል፡፡ ይህ ግን የአየር ንብረት ለውጥ ሊባል አይችልም፡፡ ምክንያቱም የአየር ንብረት ለውጥ ቀስ በቀስ ከረጅም ጊዜ በኋላ ከነበረበት ሁኔታ ወደ አዲስና ያልተለመደ የአየር ሁኔታ ሲቀየር ነው፡፡

**መልመጃ 7.2**

ለሚከተሉት ጥያቄዎች አጭር መልስ ስጥ/ጪ፡፡

1. የአየር ንብረት ለውጥ ማለት ምን ማለት ነው?እንዴት መረዳት ይቻላል?
2. በተፈጥሮ በየዓመቱ የሚቀያየረው የአየር ሁኔታ የአየር ንብረት ለውጥ ማለት እንችላለን? ለምን?

## 7.1.2 የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶችና ጉዳቶቹ

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የአየር ንብረት ለውጥ ምክንያቶች ምንድን ናቸው?
2. የአየር ንብረት ለውጥ ምን አይነት ጉዳት ያመጣል?

የዓለም አየር ንብረት ሁል ገዜ የማያቋርፅ ለውጥ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ ለውጥ በተፈጥሮ ዑደት ሂደት የሚፈጠር ክስተት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የሰው ልጅ ይህን የዓለም አየር ንብረት ለውጥን እያፋጠነ ያለው የሰው ልጅ ድርጊት ነው፡፡ የአየር ንብረት ተመራማሪዎች እንደሚገልፁት ምንጩ በሁለት ይከፍላሉ፡፡ እነሱም ተፈሮአዊና ሰው ሰራሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

**ሀ. ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች**

በተፈጥሮ ምክንያት የሚፈጠሩ የአየር ለውጥ ምክንያቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የእሳተ ገሞራ ፍንዳተ፤ የአየር አቅጣጫ መቀየር ፤የውቅያኖስ ማዕበልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

**የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ** የእሳተ ገሞራ ፍንዳታ ሲከሰት $SO_2$፤ የውሃ ትነት፤ $Co_2$፤ አቧራና የመሳሰሉት ነገሮች ይፈጠራሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ ከባቢ አየር ጋር ሲቀላቀሉ ስስ የነበረው ከባቢ አየር ጥቅጥቅ እንዲሆን ስለሚያደረጉ መሬት ከፀሃይ አግኝታ ወደ ከባቢ አየር የምታንፀባርቀውን ሙቀት ታፍኖ እንዲቆይ ያደርጋሉ፡፡ በዚህ የተነሳ የከባቢ አየር ሙቀት ይጨምራል ማለት ነው፡፡

**የባህር ሞገድ** የባህር ሞገድ የሚነሳው ከውቅያኖሶችና ከባህሮች ላይ ሲሆን ሙቀት፤ቅዝቃዜ ወይንም እርጥበት ይዘው ወደ የብስ/ደረቁ የመሬት አካል ያደርሳሉ፡፡ እነዚህ ደግሞ በየብስ ላይ ያለውን የአየር ሁኔታን ይቀይራሉ ማለት ነው፡፡

## ለ. ሰው ሰራሽ ምክንያቶች

በአሁኑ ወቅት ካለፉት አመታት የበለጠ የአለም ሙቀት እየጨመረ መጥቷል፡፡ ይህ የአለም ሙቀት መጨመር ዋናው ምክንያት ደግሞ የሰው ልጅ አስተዋፅዖ መሆኑን የአለም ሳይንቲስቶችም ይስማሙበታል፡፡ የሙቀት መጨመር ምክንያቶች ግሪን ሃዉስ ጋሶች (Green house gases) ወደ ከባቢ አየር ስለሚቀላቀሉ ነው፡፡ የአለም ሙቀት ካለፉት 50 ዓመታት የበለጠ የጨመረው በሰው ሰራሽ ምክንያቶች ነው፡፡

### የግሪን ሃውስ ጋሶችና ምንጫቸው

ግሪን ሃውስ ጋሶች የሚባሉት መሬትን እንደ ብርድ ልብስ ሸፍኖ ካሉት ጋሶች ዋናዎቹ ናቸው፡፡ እነዚህ ጋሶች የከባቢን አየር ሙቀት እንዲጨምር የሚያደርጉ ሲሆኑ እነሱም $CO_2$፣ $CH_4$፣ $N_2O$ እና CFC ናቸው፡፡

ሠንጠረዥ 7.1 ግሪን ሃዉስ ጋሶች ምንጭና የሚያደርሱት ተፅዕኖ

| ተቁ | ወካይ | ሥም | ምንጭ | የሚያደርሰው ተፅዕኖ |
|---|---|---|---|---|
| 1 | $CO_2$ | ካርቦንዳይ ኦክሳይዲ | ከመሬት አጠቃቀም፣ደን መመንጠር፣እርሻ መሬት ማቃጠልና ነዳጅ መቃጠልና ሌሎችም ናቸው፡፡ | በመጀመሪያ ደረጃ የከባቢን አየር ሙቀት እዲጨምር ያደርጋል፡፡ |
| 2 | $CH_4$ | ሚቴን | የእርሻ ተረፈ ምርት፣የሚያመነዥጉ ከብቶች፣ተፈጥሮ ጋስ | ሁለተኛ ደረጃ |
| 3 | $N_2O$ | ናይተረስ ኦክሳይድ | ፋብሪካዎች፣ ነዳጅ የሃይል ምንጮና ሰው ሰራሽ ማዳበሪያዎች | $O_3$ን በማፍረስ ይታወቃል |
| 4 | CFC | ክሎሮፈሎሮ ካርቦን | ተፈጥሮ ምንጭ የለውም፣ ሰው ሰራሽ የሆኑ እንደ ፍሪጅ ፣በካይ ጋሶችና የፅዳት መበጥበጫዎች ናቸው፡፡ | $O_3$ን በማፍረስ ይታወቃል |

# የአየር ንብረት ለውጥ ተፅዕኖዎች

የግምገማ ጥያቄዎች

1. በአየር ንብረት ለውጥ የሚከሰቱ ጉዳቶች ወይንም ተፅዕኖዎች ምንድናቸው? ዘርዝር/ሪ።
2. የበረሃማነት መስፋፋት በአየር ንብረት ላይ የሚያመጣው ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው?
3. የንፋስ አቅጣጫ መቀየር በአየር ንብረት ላይ ያለው ተፅዕኖዎች ምንድን ናቸው?

የአየር ንብረት ለውጥ በተፈጥሮ ሃብት ላይ ሊያደርስ የሚችለው ተፅዕኖዎች ብዙ ናቸው። ከእነዚህም ወስጥ ዋና ዋናዎቹ የአለም ሙቀት መጨመር፤ የበረሃማነት መስፋፋት፤ የድርቅ መከሰት፤የባህር ውሃ መጠን መጨመር፤ የንፍስ አቅጣጫ መቀየር፤ የበረሀማ አካባቢ በሽታዎች መስፋፋት፤ አንዳንድ ህይወት ያላቸው ነገሮች ዘርያ መቀነስ ወይንም መጥፋትና የመሳሰሉት ናቸው።

## የአለም ሙቀት መጨመር

የአለም ሙቀት መጨመር ሲባል በአሁኑ ጊዜ የመሬት ገፅ ወይንም ከባቢ አየር የታችኛው ክፍል ሙቀት መጨመር ማለት ነው። የአለም ሙቀት መጨመር ምክንያት የግሪን ሃውስ ጋሶች በከባቢ አየር ውስጥ መጨመር ነው።

## የበረሃማነት መስፋፋት

የበረሃማነት መስፋፋት ሲባል በሙቀት መጨመርና በዝናብ ማነስ ምክንያት የብስ እየደረቀና እፅዋቶች መብቀል በማይችሉበት ደረጃ ሲደርሱ ነው። በረሃማነት እየተስፋፋ ሲሄድ እንስሳትና የእርሻ ስራም እየቀነሰ ይሄዳል።

## ድርቅ

ድርቅ በከፍተኛ የዝናብ እጥረት የተነሳ እፅዋቶችና እንስሳት በቂ ውሃ ማግኘት የማይችሉበት ደረጃ ሲደርሱ ነው። በድርቅ ወቅት እፅዋቶችና እንስሳቶች ሁሉ ይጎዳሉ።

## የባህርና የውቅያኖስ ውሃ መጠን መጨመር

የባህርና የውቅያኖስ ውሃ መጠን መጨመር ምክንያት የአለም ሙቀት መጨመር ነው፡፡ በአለም ሙቀት መጨመር የተነሳ በዋልታዎች አካባቢ የሚገኝ በረዶ ይቀልጣል፡፡ ይህ ደግሞ የባህርና የውቅያኖስ ውሃ መጨመር ያስከትላል፡፡ በዚህ ምክንያት አንዳንድ ደሴቶችም በውሃ የመሸፈን እድል ይገጥማቸዋል፡፡ በተጨማሪም በሚሊዮን የሚቆጠር ህዝቦች ለአደጋ ሊጋለጡ ይችላሉ፡፡ ጨዋማ ውሃም በየብስ ላይ በመፍሰስ የንፁህ/ መጠጥ ውሃ እጥረት እንዲከሰት ምክንያት ይሆናል፡፡

## የዓለም የንፋስ አቅጣጫ መለወጥ

ንፋስ ከከባድ የአየር ግፊት ወደ አነስተኛ የአየር ግፊት የሚንቀሳቀስ አየር ነው፡ ፡ በአየር ግፊት ላይ ተፅዕኖ ከሚያደርሱ ነገሮች አንዱ ሙቀት ነው፡፡ በአማካይ የአለም ሙቀት እየጨመረ ሲሄድ ንፋስ በፊት ከሚነፍስበት አቅጣጫ ወደ ሌላ አቅጣጫ ይነፍሳል፡፡ የንፋስ አቅጣጫ ሲለወጥ የዝናብም ስርጭት እንዲሁም ለአየር ንብረት መለወጥ ምክንያት ይሆናል፡፡

## የበረሃ በሽታዎች መስፋፋት

ቀደም ሲል ያልነበሩ በሽታዎች የአለም ሙቀት መጨመር ምክንያት የሚፈጠር ነው፡፡ ይህም ሊሆን የቻለው የተለያዩ የመሬት አቀማመጥ ያላቸው የአየር ሁኔታ ስለተቀየረ ነው፡፡ የነበራቸው የአየር ሁኔታ በፊት ደጋ የነበረው ወደ ወይና ደጋ፤ ወይና ደጋ የነበረው ደግሞ ወደ በረሃማነት በመቀየሩ ነው፡፡ ለምሳል ኢትዮጵያ ውስጥ የወባ በሽታ ከቆላማው የአገሪቷ ክፍል ወደ ደጋማውና ወይና ደጋው ክፍል እየተስፋፋ ነው፡፡

## ህይወት ያላቸው ነገሮች ዝርያ መጥፋት

የአለም የአየር ንብረት ለውጥ ለአንዳንድ ህይወት ያላቸው ነገሮች መቀነስ ወይንም መጥፋት ምክንያት ይሆናል፡፡ የነበረው ሙቀትና ዝናብ መጠን ስለ ተቀየረ የአንዳንድ እፅዋቶችና እንስሳት ዝርያ እየጠፉ ይሄዳሉ፡፡ አንዳንዶቹ ስነ-ህይወት ለአየር ንብረት ለውጥ ቶሎ ራሳቸውን ሲያላምዱ ሌሎች ደግሞ ለመጥፋት ይጋለጣሉ፡፡ የአለም ሙቀት በ 2°c የሚጨምር ቢሆን ህይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ ችግር ላይ እንደሚወድቁ ተመራማሪዎች ይናገራሉ፡፡

መልመጃ 7.3

I. ቀጥሎ የተሰጡትን ዐ/ነገሮች ትክክል የሆነውን እውነት ትክክል ያልሆነውን ደግሞ ሐሰት በማለት መልስ/ሺ

1. የአየር ንብረት ለውጥ በተወሰነ አካባቢ ላይ ብቻ በተፈጥሮ የሚከሰት ነው።
2. የአለም ሙቀት እየጨመረ ከሄደ የዝናብ መጠን ይጨምራል። የባህር ውሃ መጠን ግን ይቀንሳል።

II. "ለ" ሥር ካሉት ውስጥ በመምረጥ "ሀ"ሥር ካሉት ጋር አዘምድ/ጂ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| 1. $CO_2$ | ሀ. በከብቶች ማመንዠግ ምክንያት የሚፈጠር |
| 2. $N_2O$ | ለ. ከሁሉ የበለጠ አየርን የሚበክል |
| 3. CFC | ሐ. ከማዳበሪያ የሚፈጠር |
| 4. $CH_4$ | መ. ተፈጥሮአዊ ባህርይ የለውም |

III. ቀጥሎ ለተሰጡት ጥያቄዎች የትክክለኛውን መልስ ፊደል መርጠህ/ሽ ፃፍ/ፊ

1. ቀጥሎ ከተሰጡት ውስጥ ሰው ሰራሽ የአየር ለውጥ ምክንያት ያልሆነው የቱ ነው?
   ሀ. እሳተ ገሞራ ፍንዳታ　　ለ. የመሬት እንቅስቃሴ
   ሐ. $CO_2$　　መ. ሁሉም
2. ቀጥሎ ካሉት ገሪን ሃውስ ጋሶች ውስጥ ይበልጥ ከባቢአየርን የሚበክል የቱ ነው?
   ሀ. $CH_4$　　ለ. $SO_2$　　ሐ. $CO_2$　　መ. የውሃ ትነት

IV. ጥያቄዎችን በአጭሩ መልስ/ሺ

1. በአየር ንብረት ለውጥ ምክንያት ከሚመጡ ጉዳቶች ውስጥ ሶስት ፃፍ/ፊ

## 7.1.3. አየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል እየተከናወኑ ያሉ ሥራዎች

**የግምገማ ጥያቄዎች**

1. የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር ጥሩ ሥራ የሰሩ የምታውቀውን / ቂውን ሰዎች ስም ዘርዝር/ሪ።

የአለም ህዝቦች የአየር ንብረት ለውጥን ለመቆጣጠር የተለያዩ ሥራዎችን እየሰሩና አሁንም በመሥራት ላይ ናቸው። እየተሰሩ ካሉ ሥራዎች ውስጥ የተወሰኑት እፅዋቶችን መትከል፤ የግሪን ሃዉስ ጋሶችን መቀነስ፤ደን ማልማት፤ ራሳቸውን የሚተኩ የሀይል ምንጮችን መጠቀም የመሳሰሉት ናቸው። አገራችን የህንን ዕቅድ በመቀበል መርሃ ግብርን በመንደፍ ወደ ሥራ ገብታለች። ለምሳሌ እንደ በአውሮፓውያን አቆጣጠር በ2004 የኬንያ ዜጋ የሆነቸውና ተከታታይ እድገት፤ዲሞክራሲና ሰላም በሚባል ተቋም ውስጥ ኖቤል ተሸላሚ ዋንጋሪ ማታይ ዋና ስራዋ የነበረው የደን መመንጠር በገጠሩ ድሃ ሴቶች ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ለመቅረፍ እቅድ በማውጣት ስትሰራ ነበር። ማታይ የሴቶች አረንጓዴ ቀለበት በሚል ስም የሴቶች ንቅናቂ በማድረግ በብዙ ሚሊዮን የሚቆጠሩ የዛፍ ችግኞችን በተመሳሳይ መልኩ የቀድሞ የኢትዮጵያ ፐሬዝዳንት የነበሩ አቶ ግርማ ወ/ጊዮርጊስ  አንድ ሰው በአመት አንድ ዛፍ መትከል አለበት በሚል መርህ ፤ ዛፎች እንዲተከሉና እንክብካቤ እንዲደረግላቸው በማለት የአረንጓዴ ክበብ አቋቁመዋል። ይህም ኢትዮጵያ በአለም ታዋቂ እንድትሆን አድርጓታል። የአካባቢ እንክብካቤ ላይ የሚሰሩ እንደ GTZ, ATA, የአካባቢ ጥበቃና እንክብካቤ ሌሎችም ናቸው።




ሥዕል 7.1. ዋንጋሪ ማታና ግርማ ወ/ግዮርግስ

የተማሪው ተግባር

1. በአካባቢያችሁ የአየር ንብረት ለውጥን ለማስቀረት የተሰሩ ስራዎችን በመጎብኘት ለክፍላችሁ ጓደኞች ዘገባን አቅርቡ፡፡

## 7.1.4. የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ በየአካባቢው የሚሰሩ ስራዎች ላይ የተደረጉ ወቅታዊ ጥናት

በአለም ላይ የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ በየአካባበው የሚሰሩ ስራዎች እንደየ አካባቢው ሁኔታ ይለያያል፡፡ በተመሳሳይ መልኩ በአገራችንም ይህ ተግባር እንደየአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ እንደየ አየሩ ንብረት ልዩነት ይኖረዋል፡፡

እንደ ኦሮሚያ ክልል የአየር ንብረት ለውጥን ለመከላከል የሚሰሩ ስራዎች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- አንድ ሰው አንድ ዛፍ ይትከል የሚል እቅድ መተግበር
- የአረንገጓዴን አሻራን ወስዶ ሥራ ላይ ማዋል
- የደንን መመንጠርን መቀነስ
- ራሳቸውን የሚተኩ የኃይል ምንጭ እንደ ውሃ፤ንፋስ፤ከርሰ ምድር እንፋሎት የመሳሰሉትን መጠቀም፡፡
- ለምግብነት የሚውሉ ዛፎችን መትከልና የመሳሰሉት ናቸው፡፡


## 7.1.5. የአየር መበከል

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. አየርን የሚበክሉ ነገሮች ምንድን ናቸው?
2. በአየር መበከል ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶች ምንድን ናቸው ?
3. በእናንተ አካባቢ አየርን የሚበክሉ ነገሮች ምን እንደሆኑ ለክፍል ተማሪዎች ግለፅ/ጪ

የአየር መበከል ማለት በካዮች በሚባሉት እንደ በካይ ጋሶች፣ ማዕድናት፣ ሞሎኪዩሎች፣ጥቃቅን ነፍሳቶችና የመሳሰሉት ወደ አየር ሲቀላቀሉና በሰው ልጅና ሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት ሲያደርሱ ነው፡፡ በሌላ አባባል የአየር መበከል ሲባል የፊዚካላዊ፣ባዮሎጂካላዊና ኬሚካላዊ ለውጦች ወይንም ሂደት ውጤት ከባቢ አየር ውስጥ ሲገቡ ነው፡፡ በዚህን ጊዜ ንፁህ የነበረው አየር መበከል ይገጥመዋል፡፡ የአየር መበከል ጎጂ የሆኑ መርዛማ ጋሶች፣ አቧራ እንዲሁም ጭስ የሰውና የእንስሶችን ጤንነት ለአደጋ ሲያጋልጡ ነው፡፡

በከባቢ አየር ውስጥ ያሉ የተለያዩ ጋሶች በመቶኛ ውስን ናቸው፡፡ የከባቢ አየር ይዘቶች በመጠን መጨመር ወይንም መቀነስ ህይወት ያላቸው ነገሮች ላይ ጉዳት አላቸው፡፡ በአጠቃላይ የከባቢ አየር ጋሶች መጠን መለወጥ የሙቀት መጨመርን ያስከትላል፡፡ይህ ደግሞ የአለምን ሙቀት መጨመር ያመጣል ማለት ነው፡




:

ሥዕል 7.2. የአየር መበከል ምክንይቶች

## የአየር በካይ ጋስ ዓይነቶች

አየርን የሚበክሉ ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ከባቢ አየርን የሚበክሉ ነገሮች የተለያየ ደረጃ አላቸው፡፡ እነሱም አንደኛ ደረጃና ሁለተኛ ደረጃ ናቸው፡፡ የተወሰኑት በከፍተኛ ደረጃ ከባቢ አየርን ይበክላሉ፡፡ አንደኛ ደረጃ የሚባሉት ከባቢ አየርን በቀጥታ በመበከል የሚታወቁ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ካርቦንዳይኦክሳድ(CO2) ና ሰልፈሪክ ኦክሳይድ ( $SO_2$) ናቸው፡፡

ሁለተኛ ደረጃ በካዮች የሚባሉት ደግሞ ከአንደኛ ደረጃ በካዮች ጋር በመወሃድ ከፍተኛ ጉዳት ማምጣት የሚችሉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ N20 እና CFC ናቸው፡፡

## በአየር ብክለት ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶች

በአየር ብክለት ምክንያት የሚከሰቱ ጉዳቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የመተንፈሻ አካላት በሽታዎች፤ ሙቀት መጨመር፤ የመርዛማ ዝናብ መከሰት፤ የኦዞን ንብርብር መሸንቆር እና ሌሎችም ናቸው፡፡

## የአየር ብክለት መቆጣጠሪያ ዘዴዎች

የአየር ብክለትን ለመቆጣጠር የሚከተሉትን እርምጃዎችን መውሰድ አስፈላጊ ነው፡፡

- ✓ አካባቢን የሚበክሉ የትራንስፖርት ዓይነቶችን መቀነስ
- ✓ የማገዶ እሳትን መጠቀም መቀነስ
- ✓ አካባቢያችንን በደን መሸፈን
- ✓ በካይ ጋሶች(ገሪን ሃውስ ጋሶችን) መቀነስና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## መልመጃ 7.4

I. ቀጥሎ ያሉትን ዐ/ነገሮች ትክክል የሆኑትን እውነት ትክክል ያልሆኑትን ሐሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. አቧራ ከአየር በካዮች ውስጥ አንዱ ነው፡፡
2. የአየር ብክለት ሰውና የዱር አራዊቶችን እንጂ እፅዋቶችን ሊጎዳ አይችልም፡፡

II. የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ/ሺ

1. የአየር በካይ አይነቶችን ምሳሌ በመውሰድ ግለፅ/ጪ፡፡
2. በአየር ብክለት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ጉዳቶች ውስጥ ሶስቱን ጻፍ/ፊ፡፡

## 7.2 የውሃ እጥረት

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. የውሃ እጥረት ምንድነው? እንዴትስ ሊፈጠር ይችላል?
2. አንተ/ቺ የምታውቀው/ቂው የውሃ እጥረት ጉዳት አለ? ከጓደኛ ጋር ተወያዩበት፡፡
3. በውሃ እጥረትና የውሃ ብክለት መካከል ያለውን ልዩነት ግለፅ/ጪ፡፡
4. በአካባቢያችሁ የውሃ እጥረት ለመቀነስ የሚሰሩ ሥራዎችን ጥቀስ/ሺ ፡፡

እጥረት ማለት ሳይዳረስ ሲቀር ወይንም የአቅርቦት ማነስ ማለት ነው፡፡ የውሃ እጥረት ሃሳብ ደግሞ የሚገልፀው የአቅርቦትና ፍላጎት አለመመጣጠንን ነው፡ ፡ ውሃ በጣም አስፈላጊ የሆነ የተፈጥሮ ሃብት ነው፡፡ የውሃ እጥረት ሁሉንም ነገር ይጎዳል፡፡ ውሃ ለመጠጥ፤ንፅህናን ለመጠበቅ፤ ምግብ ለማዘጋጀትና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች ይውላል፡፡
በአጠቃላይ የውሃ ጠቀሜታ በዚህ በሳለፍነው አንድ መቶ ዓመታት ውስጥ በእጥፍ ጨምሯል፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት በፍጥነት በሚጨምረው የህዝብ ቁጥር ምክንያት ነው፡፡

ጥናቶች እንደሚያሳዩት በአሁኑ ወቅት የሰው ልጅ ለመጠጥ፤ንፅህናን ለመጠበቅ፤ ምግብ ለማዘጋጀት በየቀኑ የሚያስፈልገው የውሃ መጠን ሃምሳ ሊተር (50ሊ) ነው፡፡ ይሁን እንጂ ብዙ አገሮች ይህን ለማሳካት እየተቸገሩ ነው፡፡

በአጠቃላይ ለውሃ እጥረት ምክንያት የሆኑ ነገሮች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዚህም ውስጥ ውሃን ያለ ቁጠባ መጠቀም ፤ ግጭት፤ የውሃ ብክለት፤ ርቀት፤ ድርቅ፤ የአቅርቦት ማነስ፤ የሙቀት መጨመር፤ ተፈጥሮኣዊ ችግሮች፤ የሰው ቁጥር መጨመር፤ የፋብሪካዎች መስፋፋትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### የውሃ እጥረት የሚያስከትለው ተፅዕኖዎች

በውሃ እጥረት ምክንያት ሊመጡ የሚችሉ ጉዳቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ የመጠጥ ውሃ እጥረት፤ ረሃብ፤ የንፅህና ችግሮች፤ የበሽታዎች መስፋፋት፤ የድህነት መስፋፋት፤ ስደት፤ የተፈጥሮ ስነ ምህዳር መረበሽ፤ህይወት ያላቸው ነገሮች መጥፋትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

### የውሃ እጥረትን ለመቀነስ የሚረዱ ዘዴዎች

የውሃ እጥረትን ለመቀነስ የሚያገለግሉ ዘዴዎች፤ ውሃን በቁጠባ መጠቀም፤ ህዝብን ማስተማር፤ መልሶ በማጣራት መጠቀም፤ የተለያዩ ውሃን ለመቆጠብ የሚያገለግሉ ቴክኖሎጂዎችን መጠቀም፤ ኋላ ቀር የመስኖ አጠቃቀምን ማሻሻል፤ውሃ ላይ የሚሰሩ ተቋማትን ማበረታታትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡.

## 7.3. የደን መመንጠር

### የግምገማ ጥያቄዎች

1. የደን መመንጠር ማለት ምን ማለት ነው?
2. በደን መመንጠር ምክንያት የሚመጡ ጉዳቶች ምን ምን እንደሆኑ የምታውቀውን/ውቂውን ያህል ለክፍል ጓደኞቻችሁ ዘግቡ፡፡
3. ለደን መመንጠር ምክንያት ሊሆኑ የሚችሉትን ዘርዝር/ሪ፡፡
4. ደንን ለመንከባከብ የሚሰሩ ተቋማት፤ መሥሪያ ቤቶች፤ ክልሎችና ግለሰቦች ከሰሩት ጥሩ ሥራዎች ውስጥ የምታውቀውን/ቂውን ለክፍልህ/ሽ ጓደኞች ግለፅ/ጪ፡፡

የደን መመንጠር ማለት በተፋጥሮ ወይንም በሰው ሰራሽ ምክንያቶች በተከታታይ የሚከናወን የደን መቀነስ ማለት ነው፡፡ ሰዎች ህጋዊ ባልሆነ ወይንም ከመጠን በላይ ዛፎችን ሲቆርጡ የደን መመንጠር ይባላል፡፡ የደን መመንጠር የሚያስከትለው ጉዳቶች ብዙ ናቸው፡፡ ከነዘህ ውስጥ ጥቂቶቹ፤ ህይወት ያላቸው ነገሮች መጥፋት፤የሥነ ምህዳር መቃወስ፤የዱር እንስሳት መሰደድ፤ የውሃ ዑደት መፋለስ፡ የዓለም ሙቀት መጨመርና የአየር ንብረት ለውጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡



ሥዕል 7.3 የደን መመንጠር

## የደን መመንጠር ምክንያቶች

የደን መመንጠር ምክንያቶች ብዙ ናቸው፡፡ በአጠቃላይ የደን መመንጠር ምክንያቶች በሁለት ይከፈላሉ፡፡እነሱም

1. ሰው ሰራሽ ምክንያቶችና 2. የተፈጥሮ ሂደቶች ምክንክቶች ናቸው

**ሰው ሰራሽ ምክንያቶች** ለደን መመንጠር ምክንያት ዋናው የሰው ልጅ ትክክል ባልሆነ መንገድ በደን መጠቀም ነው፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ፤

- የእርሻ ሥራን ለማስፋፋት
- ያለአግባብ ዛፎችን መቆረጥ
- የማዕድን ማውጣት ሥራ መስፋፋት
- የከተሞች መስፋፋት
- በዛፎችና ዛፎች ውጤቶች መጠቀም ፍላጎት ማደግ
- ማህበራዊ አገልግሎቶችን ከዕቅድና ከምክክር ውጪ ማስፋፋት

## ተፈጥሮአዊ ምክንያቶች

ለደን መመንጠር ምክንያት ተፈጥሮም የራሱ የሆነ ትልቅ አስተዋፅዖ አለው፡፡ ይሁን እንጂ አሳሳቢ የሆነውና የተፈጥሮውንም ምክንያቶች ያፋጠነው ትክክል ያልሆነ የሰው ልጅ የደን ሃብት አጠቃቀም ናቸው፡፡ ከተፈጥሮአዊ ምክንያቶች ውስጥ የተወሰኑት የሚከተሉት ናቸው፡፡

- ድርቅ፤ ጎርፍና የመሬት መንሸራተት

- ሰደድ እሳት፤ የደረቁ ዛፎች ሲፋተጉ የሚፈጠር እሳት
- በባክቴሪያ ወይንም በጥገኛ ነፍሳቶች አማካይነት የሚመጡ በሽታዎችና የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## የደን መመንጠር መቆጣጠሪያ ዘዴዎች

ደን ሲመነጠር በአካባቢ፤ በውሃ፤ በአፈር፤ በመኖርያ አካባቢና ሁሉም ህይወት ባላቸው ላይ ትልቅ ጉዳት ይደርሳል፡፡ ይህንን ችግር ለማስቀረት መንግስት፤ የተለያዩ ተቋማት እና ግለሰቦች የራሳቸውን ኃላፊነት መወጣት አለባቸው፡፡

## የመንግስት ሚና

መንግስት የደንን መመንጠር ለመቀነስ የተለያዩ መመሪያዎችን በመውጣት መተግበር አለበት፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ፤

- ሕጋዊ ያልሆነ የደን ምንጠራ ላይ ጠንካራ ቁጥጥርና ክትትል ማድረግ፤
- በመንግስት ቁጥጥር ሥር ያሉ የመንግስት ደን አካባቢዎችን ማስፋፋትና ጥበቃ ማድረግ፤
- የተለያዩ የማህበራዊ አገልግሎቶችን ስናለማ በእቅድ በመመራትና የደንን መመንጠር መቀነስ ያስፈልጋል፤
- የተፈጥሮ ደንን የሚተካና የተለያዩ ጥቅሞችን የሚሰጥ ሰው ሰራሽ ደን ማልማት
- በተመነጠረው ወይንም በተቆረጠው ደን ምትክ  መልሶ መትከል
- በአጭር ጊዜ ደርሰው ለአገልግሎት የሚበቁ ዛፎች  እንዲተከሉ ባለሃብቶችን ማበረታታት ናቸው፡፡

## የግለሰቦች ሚና

ማንኛውም ሰው የሚኖርበትን አካባቢ የመንከባከብ ሃላፊነት አለበት፡፡ ይሁን እንጂ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ሰዎች አካባቢያቸውን ከመንከባከብ ይልቅ ሲያወድሙ ይታያል፡፡ ይህ ሁኔታ እንዳይቀጥል ህብረተሰቡን ማስተማር አስፈላጊ ነው፡ ፡ አንድ ሰው ቢያንስ በህይወቱ ውስጥ ቀጥሎ የተሰጡትን ህጎች መተግበር አለበት፡፡ እነሱም፡

- መቀነስ  በእቅድና በቁጠባ መጠቀም
- መልሶ መጠቀም  ጥቅሙን ከጨረሰ በኋላ መልሶ በማምረት ወይንም በመጠገን አገልግሎት እንዲሰጥ ማድረግ ናቸው፡፡

## የተለያዩ የልማት ተቋማት

የተለያዩ የልማት ተቋማት የደን መመንጠርን ለማስቀረት የተለያዩ ስራዎችን ያከናውናሉ፡፡

- በደን ልማት ላይ የሚሳተፉትን የተለያዩ አካላትን መርዳት፤
- የህብረተሰቡንና የመንግስት አካላትን ግንዛቤ ማሳደግ፤
- የተለያዩ ችግኞችን ከማፍላት ጀምሮ እስኪያድጉ ድረስ መከታተልና አስፈላጊውን እንክብካቤ ማድረግ፡፡

### መልመጃ 7.5

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በአጭሩ መልስ/ሺ

1. በደን መመንጠር ምክንያት የሚመጡትን ጉዳቶች ዘርዝር/ሪ፡፡
2. አንድ ሰው በህይወቱ ውስጥ ማከናወን ካለበት ህጎች ውስጥ ሶስቱን ፃፍ/ፊ፡፡

# ማጠቃለያ

በአሁኑ ጊዜ የአየር ንብረት እየተለወጠ ነው፡፡ ይህ የአየር ንብረት ለውጥ ከመጠን በላይ የሙቀት መጠን መጨመርን አስከትሏል፡፡

የአየር ሁኔታ ማለት በከባቢ አየር ውስጥ ያሉ ይዘቶች በተወሰነ ጊዜና ቦታ መቀያየር ማለት ነው፡፡ ይህም ከአጭር ጊዜ ሰዓት፣ቀን፣ሳምንት፣ወርና እስከ ዓመት ድረስ በየጊዜው የሙቀት፣ ንፋስ፣ የፀሐይ ብርሃንና ሌሎችም መቀያየር ማለት ነው፡፡

የአየር ንብረት ማለት ደግሞ አማካይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡የአየር ንብረት በአንድ በተወሰነ ቦታ ለረጅም ጊዜ ሳይቀየር የሚታይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡ ለረጅም ገዜ (በአማካይ ለ35 ዓመታት) በተመሳሳይ የሚታይ የአየር ንብረት ይዘት ነው፡፡ የአየርን ሁኔታ የሚያጠና ሳይንስ ሜትሮሎጂ ሲሆን ስለ አየር ንብረት የሚያጠና ሳይንስ ደግሞ ክላይማቶሎጂ ይባላል፡፡

የአለም አየር ንብረት ሁልጊዜ በማያቋርጥ ለውጥ ውስጥ ይገኛል፡፡ ይህ ሁኔታ የሚከናወነው በተፈጥሮ ሲሆን የአየር ለውጡ የሚፋጠነው ደግሞ በሰው ልጅ በተሳሳቱ ዲርጊቶች አማካይነት ነው፡፡ በአጠቃላይ የአየር ንብረት ለውጥ ተፈጥሮአዊና ሰው ሰራሽ ምንጮች በመባል በሁለት ይከፈላሉ፡፡

ግሪን ሃዉስ ጋሶች የሚባሉት እንደ $CO_2$, $CH_4$, $N_2O$, CFC, የውሃ ትነትና የመሳሰሉት ናቸው፡፡የዚህ ሂደት ውጤቶች ደግሞ የድርቅ መፈጠር፣ የሙቀት መጠን መጨመር፣በረሃማነት መስፋፋት፣ህይወት ያላቸው ነገሮች መጥፋት ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የአየር ንብረት ለውጥን ለመቀነስ እየተሰሩ ካሉት ነገሮች ውስጥ የተወሰኑት ፤እፅዋትን መትከል፣ግሪን ሃዉስ ጋሶችን መቀነስ ፤ደን መትከልና ራሳቸውን የሚተኩ የተፈጥሮ ሃብቶችን መጠቀም ናቸው፡፡

የአየር ብክለት የሚያመጡ በካይ ጋሶች፣ ማዕድናት፣ ሞሎኪዩሎችና ሌሎች ህይወት ያላቸው ነገሮች ወደ ከባቢ አየር ሲቀለቀሉ ነው፡፡ እነዚህ በካዮች በሰው ልጆች ጤንነትና አካባቢ ላይ ጉዳት ያደርሳሉ፡፡

## የምዕራፍ 7 መጨረሻ ጥያቄዎች

### ክፍል I. ቀጥሎ ያሉትን ዐ/ነገሮቸ ትክክል ከሆኑ እውነት ትክክል ካልሆኑ ሐሰት በማለት መልስ/ሺ፡፡

1. አየር ንብረት ማለት ለአጭር ጊዜ ከስድስት ወር የማይበልጥ በአንድ ቦታ የሚቆይ የአየር ሁኔታ ነው፡፡
2. የአየር ብክለትን መቀነስ ይቻላል፤ ነገር ግን ጭራሽ ማጥፋት አይቻልም፡፡
3. ካርቦንዳይኦክሰይድ ከበካይ ጋሶች ውስጥ ቀዳሚው ጋስ ነው፡፡

### ክፍል II ቀጥሎ ላሉት ጥያቄዎች ከተሰጡት ምርጫዎች ውስጥ ትክክለኛውን መልስ የያዘውን ፊደል ምረጥ/ጪ

1. ከግሪን ሃዉስ ጋሶች በብዛት በከባቢ አየር ውስጥ የሚገኘው የቱ ነው?
   ሀ. የውሃ ትነት ለ. CFC ሐ. $CO_2$ መ. $SO_2$
2. በአየር ንብረት መለወጥ ምክንያት የማይመጣው ተፅዕኖ የትኛው ነው?
   ሀ. ድርቅ ሐ. የበረሃማነት መስፋፋት
   ለ. የደን መመንጠር
   መ. አንዳንድ ህይወት ያላቸው ነገሮች ዝርያ መጥፋት
3. በውሃ እጥረት ምክንያት የማይመጣው ጉዳት የቱ ነው
   ሀ. ረሃብ ሐ. ህብረተሰብን ማስተማር
   ለ. ስደት መ. የበሽታዎች መስፋፋት

### ክፍል IV የሚከተሉትን ጥያቄዎቸ በአጭሩ መልስ/ሺ

1. በሰው ልጅ የደን መመንጠር የሚፋጠንበትን መንገዶች ውስጥ ሶስቱን ፃፍ/ፊ፡፡
2. የግሪን ሃውስ ጋሶችና ጉዳቶች ከምንጫቸው ጋር ግለፅ/ጪ፡፡

# የቃላት ፍቺ

| | |
|---|---|
| አሰሳ | አንድን የማይታወቅ ቦታ ወይም ሀገር በፍለጋ ማግኘት |
| አይዲዮሎጂ | የአንድ ሀገር ውይም ቡድን አመለካከት ወይም የአካሄድ አቋም |
| ማብጠልጠል | የስም ማጥፋት  ወይም ማጥላላት ዘመቻ |
| ተቃራኒ | የተቃውሞ ሐሳብ |
| ፍረጃ | የአንድ ቡድን አባል እንደሆነ መመደብ ወይም ጎራ ማስያዝ |
| ብጥብጥ | ያለመረጋጋትና ግጭት |
| ኢንዱስቲሪ | የፋብሪካዎች ቅንጅት ወይም ስብስብ |
| ካፒታሊስቶች | የካፒታሊስት ስርዓት ደጋፊዎችና ከፍተኛ ባለሃብቶች |
| ኮሎኒያሊስቶች | ሀገራትን በቅኝ ግዛት ስርዓት ስር የሚያስተዳድሩ ሀገራት ወይም ቡድኖች |
| ኮሎኒ | በቅኝ ግዛት ስርዓት ስር የሚተዳድሩ ሀገራት |
| ቅኝ ግዛት | አንድ ሀገር በሌላ ሀገር ላይ ያለው ፖለቲካዊ፣ ምጣኔ ሐብታዊና ማህበራዊ የበላይነት |
| ኮሚኒስቶች | የኮሚኒዝምን ስርዓት ማህብር የሚደግፉና የሚያደንቁ የህብረተሰብ ቡድኖች |
| እንደ ዋዛ | በቀላሉ የማከናወን ሂደት |
| ቤተመንግሥት | ንጉሥ(ንጉሣን) ሀገርን የሚመሩበት የህንፃ(የቤት) ማዕከል |
| ንጉስ | የአንድ ሀገር ወይም ህዝብ ቤተሰባዊ መሪ |
| ራስ ቢትወደድ | በመካከለኛው የኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የጦር አበጋዞች ለመያዝ ሲጣሉበት የነበረ ከፈተኛ ስልጣን |
| ህዳሴ | የአንድ ሀገር ወይም ቡድን(ህዝብ) ተመልሶ ማበብ(መበልፀግ) |
| ተሓድሶ | የካቶሊክን ሃይማኖት አካሄድ ለመቃወም የተካሄደ እንቅስቃሴ ወይም ማንኛውም የለውጥ እንቅስቃሴ |

| | |
|---|---|
| UNESCO(ዩኔስኮ) | በተባበሩት ድርጅት ውስጥ የትምህርት፣ የሳይንስና የባህል መዋቅር |
| አብዮት | ለጠቅላላ መሰረታዊ ለውጥ የሚደረግ ህዝባዊ ትግል |
| ፋብሪካ | በተለያዩ ማሽኖች ሸቀጣሸቀጦችን ወይም ምርቶችን የሚያመርት ድርጅት |